# ሕይወት ስትመዘን

## ከእግዚአብሔር እይታ አኳያ
## ሕይወት የምትመዘንባቸው 17 መንገዶች


በዌስሌይ ኤል ዱዌል

ትርጉም፡- ደረጀ በቀለ

አርትኦት

ጳውሎስ ፈቃዱ



ራዕይ አሳታሚ

አዲስ አበባ 2001 ዓ.ም.

# ሕይወት ስትመዘን

## ይህ መጽሐፍ የተተረጎመው

## Measure Your Life

## ከሚለው መጽሐፍ ነው::

By Wesley L.Duewel

ይህንን መጽሐፍ ያለ አሳታሚው ፈቃድ ማባዛት ወይም
እንደገና ማሳተም በሕግ የተከለከለ ነው::

ራዕይ አሳታሚ
የፖ. ሳ. ቁ 2332
አዲስ አበባ

RPTR-28 3M

**ማውጫ**

1. እግዚአብሔር ሊሸልምህ ይጓጓል......6
2. ሕይወትህ የእግዚአብሔር ስጦታ ናት......15
3. መንግስተ ሰማይ፣ ግን......28
4. ተመልክቶ የሚመዝን አምላክ......38
5. ሕይወትህን ከፍቅር አንጻር መዝነው......46
6. ከእግዚአብሔር ጋር ባለህ ሕብረት፤ ሕይወትህን መዝን......62
7. በምልጃ ፀሎትህ ሕይወትህን መዝን......74
8. በውስጣዊ ደስታህ፤ ሕይወትህን መዝን......88
9. በእምነትህ፤ ሕይወትህን መዝን......99
10. በትህትናህ፤ ሕይወትህን መዝን......113
11. በመታዘዝህ፤ ሕይወትህን መዝን......126
12. ከእግዚአብሔር ዘንድ በምትቀበለው ምሪት፤ ሕይወትህን መዝን......142
13. በምትናገራቸው ቃላት፤ ሕይወትህን መዝን......156
14. በውስጥህ ባሉት አስተሳሰቦችህ፤ ሕይወትህን መዝን......169
15. በምትዘራው ዘር ሕይወትህን መዝን......180
16. ለፍጥረት መዳን ባለህ መሻት፤ ሕይወትህን መዝን......194
17. በመስዋእትነትህ፤ ሕይወትህን መዝን......207
18. እግዚአብሔርን ባከበርክበት መጠን፤ ሕይወትህን መዝን......224
19. ባለፍክበት የመስቀሉ መንገድ፤ ሕይወትህን መዝን......238
20. በአንተ ውስጥ ባለው የእግዚአብሔር መንፈስ ህይወትህን መዝን......252
21. በራዕይህ፤ ሕይወትህን መዝን......267

## መቅድም

በሕይወት የሩጫ ውድድር የመጀመሪያዎቹን መቶ ሜትሮች ማንም ሰው ሮጦ ሊያጠናቅቃቸው ይችላል:: ወድድሩን እስከ መጨረሻው ሮጦ ሊያጠናቅቅ የሚችለው ግን ህያው የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ በውስጡ የሚኖርና በመንፈስ ቅዱስ የተሞላ የተለየ ሰው ነው::

ኢሪክ ሊዴል የተባለው የኦሎምፒክ ሩጫ ተወዳዳሪ እሁድ የጌታ ቀን በመሆኑ ምክንያት ለመወዳደር ፈቃደኛ ሳይሆን ቀረ:: እርሱ ህይወቱን የመዘነው ታላቅ ከሆነው የህይወቱ ሩጫ ፍጻሜ አኳያ ነበር:: አዎን አንድ ቀን፤ የኦሎምፒክ ሜዳሊያውን አጥልቆ ክፎቶግራፍ አንሺዎች ፊት ሳይሆን የሚቆመው ከእዳኙ ፊት እንደሆነ ተረድቷል::

የመጀመሪዎቹን መቶ ሜትሮች ሳይሆን ፍፃሜውን እያስብኩ ውሳኔ መስጠት እንድችል፤ ቤተሰቦቼ፣ መንፈሳዊ አሳዳጊዎቼና ጌታም ህይወቴን መመዘን እንዳስብኝ ስላስተማሩኝ፤ ራሴን የምቆጥረው እንደ እድለኛ ሰው ነው:: እንዲህ አይነቱ አመለካከት የተሻለውን የእግዚአብሔር ነገር ላለማድረግ በማመቻመች፤ ተራ እና ከዚህ ሲከፋም ሃጢያት የሆነውን ነገር እንዳላደርግ ምን ያህል ጊዜ እንዳገዘኝ መቁጠር አልችልም::

እናም፤ የዶክተር ዊስሌይ ዱዌልን ሕይወት ስትመዘን የምትለዋን መጽሐፍ እንድታነቡ የምጋብዘው በደስታ ነው:: ዶክተር ዱዌልን ለረዥም ጊዜ የማወቅ እድል ስለነበረኝ፤ ፍጹም በሆነ እርግጠኝነት ለማሸነፍ የሚሮጥ ሰው መሆኑን መናገር እችላለሁ::

በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ዶክተር ዱዌል ሕይወት የሚመዝንበትንና የሚኖርበትን አስራ ስባት መመዘኛዎች አቅርቧል:: ምንም እንኳን ሀሣቦቹን ደብልጥ ለማብራራት እጅግ ታዋቂ በሆኑ የእግዚአብሔር አገልጋዮች ስራ ታሪክ ውስጥ ቢያራምደንም፣ የሰጣቸው እያንዳንዱ አስገራሚ መግለጫዎች ከራሱ የሕይወት ልምምድ መወሰዳቸው ጥያቄ የሌለበት ነው::

ዊስሌይ ዱዌል እጅግ የተከበረ ሚስዮናዊ መሪና አይኖቹን በሽልማቶቹ ላይ ተክሎ ክርስቲያናዊ ሩጫውን የሚሮጥ የተለየ መንፈሳዊ ደረጃ ያለው ሰው ነው:: በእውነት እንደዚህ ያለውን ጽናት አደንቃለሁ! በእነኝህ ሁሉ ዓመታት ለእኔና ለሌሎች እጅግ ብዙ ሰዎች በመጸለይ ዓለምን መንካት መቻሉን በማወቁ እግዚአብሔርን ላመስግን እፈልጋለሁ::

ይህ መጽሐፍ መሪ መሆንና ብዙዎችን ማስከተል በሚችል የተጻፈ በመሆኑ፤ ፈጥነን የእኛ ልናደርገው የሚገባ የከበረ መጽሐፍ ነው:: የዶክተር ዱዌል መጽሀፍ ዛሬ እንዲያጽናናችሁ በተግዳሮታዊ ሃሣቦቹ እንዲመዝናችሁ እግዚአብሔርን ጠይቁ:: የተመዘነ ክርስቲያናዊ ሕይወት መኖር ዘላለማዊ ሽልማት አለው::



ዶክተር ሉዊስ ፓሉ
የሉዊስ ፓሉ ወንጌላዊ ማህበር
ፕሬዚዳንት

ከዚህ በመቀጠል ደግሞ ወደ ሌሎች ሀገሮች ወጥተው ወንጌልን ለመስበክ ሙሉ ጊዜያቸውን ለወንጌል አገልግሎት መስጠት የሚፈልጉትን ጠየቀ:: እነዚህ የጉባኤ ተሳታፊዎች የመጡት የንግድ ማዕከል ከሆነችው ከቶኪዮ ነበር:: በጉባኤው አዳራሽ ምድር ላይ የነበሩት ወደፊት መጡ:: ቀጥሎ ደግሞ ከፎቁ ላይ የነበሩት ቁልቁል ወርደው መጡ:: ቀና ብዬ ሳይ በፎቁ ላይ ከነበሩት መካከል አንድ ወጣት እየተንደረደረ ከህንፃው ላይ ሲወርድ ተመለከትኩ:: ወደ መድረኩ አካባቢ ስደርስም "ዘግይቼ ይሆን እንዴ?" በሚል በታላቅ ስጋት ስለነበር መሮጥ ጀመረ:: ወደ መድረኩ ከቀረቡት ጋር ለመቀላቀል ደረጃዎቹን በታላቅ ፍጥነት እየዘለለ ነበር የተጠጋው::

ይህን ሳይ አይኖቼ በእንባ ተሞሉ:: ኦ.ኤም.ኤስ የተሰኘው የዚህ ቤተእምነት መሥራች ቻርልስ ኮውማን በ1901 እ.ኤ.አ የጃፓንን ምድር ሲረግጥ ይህ ይከሰታል ብሎ ጥቂት እንኳን ገምቶ ይሆን? በጃፓን ለሚገኙ ነፍሣት በማሰብ ይህንን አገልግሎት በማቀዱና ነፍሱን በማፍሰሱ ዛሬ በመንግስተ ሰማይ ሆኖ፤ ምን ያህል ደስተኛ ይሆን?

ቀጥሎ ደግሞ የዚሁ የቻርልስ ኮውማን የአገልግሎት ውጤት ከሆነ ሌላ ታዋቂ ወንጌላዊ ቤተእምነት የሆኑ አራት ወጣቶች በፕሮግራሙ ማብቂያ ላይ አገኙኝና ሰማይ ጠቀስ በሆነ ህንፃ ላይ ወደሚገኝ ምግብ ቤት ወሰዱኝ:: በደስታና በፍቅር የተሞሉ ይመስላሉ:: ምግብ አዘዙ፤ ፈጥኖም መቅረብ ጀመረ:: እነዚያ ጣፋጭ የሆኑ የጃፓን ምግቦች አንዳቸው ሌላውን እየተከተሉ መጉረፍ ጀመሩ:: እኔም ደግሞ ቀጣዩ ምን አይነት ይሆን እያልኩ እጠይቃቸው ጀመር:: በደስታ ከትከት ብለው ሳቁ:: እና እንደገና



ሌላው ደግሞ ቀጠለ:: በመጨረሻው ከብዛቱ የተነሳ ቁጥሩን እንኳን ረሳሁ፤ ነገር ግን አሥራ ሰባት አይነት ጣፋጭ ምግቦችን እንደቀመስኩ ይመስለኛል::

አብረን ባሳለፍነው ጊዜ በፊታቸው ላይ ፍቅራቸውንና ደስታቸውን ማየት ችያለሁ:: እቅዳቸውን ለእኔ በሚገልጡበት ጊዜ የሚታየውን ድንገት የሚያጥለቀልቃቸውን ደስታ ከዚህ በፊት በሌላ ሰው ላይ አይቼው አላውቅም:: አንደኛውን አስደናቂ ነገር ጨርሰው ሌላውን ደግሞ ሲጀምሩ ደስታቸው ወሰን አልነበረውም:: እጅግ ከመሸ በኋላ ከመካከላቸው አንዱ ከቶኪዮ ወደ ኦ.ኤም.ኤስ. የመጽሐፍ ቅዱስ ኮሌጅ መልሶ ሸኘኝ::

ጌ እንግዲህ ኢየሱስ ክርስቶስ በዘላለም ሕይወት ውስጥ አንዱን ቅዱስና አስደሳች ደስታ ሽልማት ሰጥቶህ ሌላውን ደግሞ ሲያስከትልልህ በፊቱ ላይ የሚበራውን ደስታ በጥቂቱ ብቻ የሚያሣይ ምስል ነው:: ልብ በል ይህ ሽልማት ለጥቂት ሰዓታት ብቻ የሚቆይ አይደለም:: ለዘላለም ቀጣይ ነው:: ከቶውንም ማለቂያ በሌለው የዘላለም አመታት ውስጥ አዲስ ነገር ይሆናል፤ የማይለወጥ ውበት፣ የማይሰለች የተቀደሰ አስደናቂ ክስተት! ግን ይህ ሁሉ ለምን? ምክንያቱም የእግዚአብሔር ፍቅርና ፀጋ አንተን ደስ ለማሰኘት ሊባርክህ፣ ሊያስደንቅህና ከዘላለም እስከዘላለም የሚኖር ሽልማት ሲሸልምህ አቅዷል:: እየቀረበ ያለውን ይህን ሊለካና ሊነገር የማይችል ደስታ መረዳት ብትችል፤ ዛሬ ታላቅ በሆነው የሕይወት ጥረትህ ያገኘኸውን ነገር ሁሉ በማንኛውም መንገድ በዘላለም ሕይወት ጉዳይ ላይ ልትዘራው ትጀምር ነበር::

## አስደናቂውን የእግዚአብሔር እቅድ አስብ

ሰብአዊ የሆነው ፍጡር የተፈጠረው ማቀድ እንዲችል ተደርጎ ነው:: ሳይንቲስቶች ሰብአዊ የሆነውን አእምሮ አስደናቂ ችሎታ ገና መረዳት መጀመራቸው ነው:: ይሁን እንጂ አእምሯችን መጠቀም የጀመርነው ከችሎታው ኢምንት ያህሉን ብቻ ነው:: አዳምና ሄዋን ሀጢያትን ባያደርጉ ኖሮ፣ የዚህ ዓለም ህዝብ ዛሬ ምን አይነት አስደናቂ እድገት ላይ ይገኝ ነበር!

እግዚአብሔር አንድን ነገር የመፍጠርና የማቀድን ችሎታ አካፍሎናል:: ምክንያቱ ደግሞ አብዝቶ ስለወደደን ነው:: እርሱ ከእለከ የማይባል ፈጣሪና ከሁሉ በላይ አቃጅ ነው:: ታዲያ እግዚአብሐር ለዛሬ ያለው እቅድ ምንድን ነው? ትልልቅ የሆኑት እቅዶቹ በምድር ያሉትን ነገሮች ማስተካከል አይደለም:: ትልልቆቹ እቅዶቹ ያተኮሩት ድንቀኛ ስለሆነው የወደፊት ጊዜ ላይ ነው:: ማናቸውም ዛሬ ካለችው አለማችን ጋር የተያያዙ ነገሮች ሁሉ ጊዜያዊ ናቸው፤ የዘላለም ህይወትን የሚመለከቱ ጉዳዮች ብቻ ዘላለማውያን ናቸው::

ይህንን አድምጥ! "ለእናንተ የማስባትን አሣብ እኔ አውቃለሁ" እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፤ "ፍጻሜና ተስፋ እሰጣችሁ ዘንድ የሰላም አሣብ ነው እንጂ የክፉ ነገር አይደለም" (ኤር 29፥11):: "አቤቱ አምላኬ ያደረግኸው ተዓምራት ብዙ ነው፤ አሳብህንም ምንም የሚመስለው የለም:: ባወራም ብናገርም ከቁጥር ሁሉ በዛ" (መዝ 40፥5):: እግዚአብሔር አስቀድሞ ያደረጋቸው መልካም ነገሮች፤ ለእኛ ሊያደርግ ካለው ሀሳቡ ጋር ሲነፃፀሩ እጅግ ኢምንቶች ብቻ ናቸው:: "ሰማይ ከምድር ከፍ እንደሚል፤ እንዲሁ



መንገዴ ከመንገዳችሁ አሳቤም ከአሣባችሁ ከፍ ያለ ነው" (ኢሳ 55፥9):: አይን ያላየችው፤ ጆሮም ያልሰማው፤ በሰውም ልብ ያልታሰበው እግዚአብሔር ለሚወዱት ያዘጋጀው . . . " (1ቆሮ 2፥9):: እግዚአብሔር ለአንተና ለእኔ እንዲህ እያለን እኮ ነው፤ "አ! ለእናንተ ያሰብኩላችሁን ደስታ፣ አስደናቂ ልምምዶችና ሽልማቶች ብታውቁ ኖሮ!"

## ከምትገምተው ሁሉ በላይ

"እነሆ አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር እፈጥራለሁ:: የቀደሙትም አይታሰቡም፤ ወደ ልብም አይገቡም:: ነገር ግን በፈጠርኩት ደስ ይበላችሁ ... እኔም ... ሀሴት አደርጋለሁ፤ በህዝቤም ደስ ይለኛል" (ኢሣ 65፥17-19)::

በፊትህ የሚጠብቅህ እግዚአብሔር ለአንተ ያዘጋጀው እቅድ አስደናቂ እና በበረከት የተሞላ ከመሆኑ የተነሣ ዛሬ በህይወትህ ያጋጠሙህን ችግሮች፣ ፈተናዎችና ግራ መጋባቶችህን ሁሉ እስክትረሳ ድረስ የሚያረካ ይሆናል:: ስለዚህም እያደረግህ ያለው ማንኛውም ጥረት፤ እየተቋቋምክ ያለኸውን ማንኛውም ግፊት፤ እግዚአብሔርን ለመታዘዝና ታላቅ የሆነውን ፈቃዱን ለማድረግ በመምረጥህ የምትከፍለው ዋጋ ሁሉ እጅግ የከበረና ረብ ያለው ነው::

መቼም ቢሆን እግዚአብሔር የማንም ባለ ዕዳ አይሆንም:: ማናችንም ብንሆን ከምንጠብቀውና ከምንችለውም በላይ ይሸልመናል:: የተትረፈረፈውን ደስታና ሽልማት በአንተ ላይ ማፍሰስ ለእርሱ ታላቅ ደስታ ነው::

"ቀላል የጊዜው መከራችን የክብርን የዘላለም ብዛት ከሁሉ መጠን ይልቅ ያደርግልናልና" (2ቆሮ 4፥17):: በዚህ የምድር ጨለማ፣ ሕይወታችን ምናልባት ለጊዜው የለቅሶ ሊሆን ይችላል:: ይሁን እንጂ የእግዚአብሔር ንጋት ሲመጣ ዘላለማዊ ደስታ ተከትሎ ይመጣል (መዝ 30፥5)::

"ለእኛም ይገለጥ ዘንድ ካለው ክብር ጋር ቢመዛዘን፣ የአሁኑ ዘመን ስቃይ ምንም እንዳይደለ እሰባለሁ፤ የፍጥረት ናፍቆት የእግዚአብሔርን ልጆች መገለጥ ይጠባበቃልና" (ሮሜ 8፥18-19):: ፍጥረት ሁሉ እግዚአብሔር ለእኛ ያዘጋጀውን እቅድ መገለጥ ለማየት የሚጠባበቅ ይመስላል:: መላእክት እግዚአብሔር ለእኔና ለአንተ ያዘጋጀው ሁሉ ሲገለጥ ለማየት ቸኩለው ሲጠባበቁ እስኪ እሰበው፤ ክብሩ በተገለጠ ጊዜም ይህንን እብረን እንካፈላለን (1ጴጥ 5፥1):: ጴጥሮስ ስለዚህ በመንግስተ ሰማይ ስላለ ሽልማት ሲናገር "በመጨረሻው ዘመን ሊገለጥ ዘንድ ለተዘጋጀ መዳን... " በማለት ይናገራል (1ጴጥ 1፥5):: እንዲሁ ደግሞ አሁን ያለው እምነታችንና ታማኝነታችን አስመልክቶ፣ "የተፈተነ እምነታችሁ ኢየሱስ ክርስቶስ ሲገለጥ ለምስጋና፣ ለክብርና ለውዳሴ ይገኝ ዘንድ" ይላል (1ጴጥ 1፥7)::

## ሽልማትህ ዘላለማዊነትን ያካትታል

እግዚአብሔር ያቀደልህን ነገሮች ሁሉ ለመለማመድ ዘላለምን ይፈልጋል:: ይሁን እንጂ የእግዚብሔር ሽልማትና ክብር የሚወሰነው የዛሬ ሕይወትህን እንዴት እንደምትኖረው ባለው እውነት ላይ ተመስርቶ ነው:: ሽልማት እንደ ሕይወትህ አይነት ነው:: ዛሬ የምትኖረው ሕይወት፤ እግዚአብሔር በደስታ ሊሰጥህ



ባለው ሽልማት ላይ በተወሰነ መልኩ ተጽእኖ የሚያሳድር ነው:: ከዘራኸው ሁሉ በላይ ታጭዳለህ፤ ይሁን እንጂ የምታጭደው እንደ ዘራኸው ዓይነት ነው::

ይህ እውነት በምድር ላይ ለምንኖረው ሕይወት እጅግ ጠቃሚ የሆነ መረዳትን ያመጣልናል:: እንደገናም ደግሞ እግዚአብሔር እኛን ሚመዝንበት መመዘኛ ልኬት ሕይወታችንን የመመዘንን ጠቃሚነት ያሳየናል:: ሕይወትህ ምንድን ናት?

## ሕይወት የተገነባችው በቅጽበት ነው

ሕይወት የተገነባችው የምናልፍበትን የዕድሜ ጉዞ እያቋረጡ ከሚከንፉ እጅግ አጭር ከሆኑ አመታት፣ ሣምንታት፣ ቀኖች፣ ሰዓቶችና ደቂቃዎች ነው:: ገናም እንደተቀበልናቸው ፈጥነው ይጠፉና ወደ ዘላለማቸው ይጣደፋሉ:: ሕይወት የተሠራችው ከቅጽበት ነውና!

ሕይወት የተገነባችው ከጥቃቅን ነገሮች ነው! ለሚያስተውል ሰው ሕይወት የመኸርን ፍሬ መስጠት እንደምትችል ዘር መልካም እድል ናት:: ፈጥና የምትበረው የሕይወት እያንዳንዷ ደቂቃ በውስጧ ዘላለምን እርግዛለች:: በእውነትም ህይወት ከጥቃቅን ነገሮች የተገነባች ናት::

ሕይወት የተገነባቸው፤ ከማያቋርጥ ምርጫ ነው! የእያንዳንዱ ቀን ምርጫችን በቀላሉ የሚታይ ቢመስል እንኳን እግዚአብሔር ሁሉንም መዝግቦ ይይዛል:: ለጌታ የምናደርገው እያንዳንዱ ነገር ዘላለማዊ ሽልማትን ያስገኝልናል:: በእርግጥም ሕይወት የተገነባችው ከማያቋርጥ ምርጫ ነው::

በሕይወትህ ትንንሽ የሚባሉ ነገሮች የሉም። ሁሉም ለዘላለም ሀይወትህ ዘርን እንድትዘራ የተፈጠሩልህ አጋጣሚዎች ናቸው።

የምታደርገው ማንኛውም ነገር ከምትገምተው በላይ ዋጋ ያለው ነው። ሀይወትም እልፍ የምታፈራ ዘር ናት። በእርግጥም በሀይወትህ ትንሽ የሚባል ነገር የለም።

ለእግዚአብሔር የተሰጠ ሀይወት የጠፋ አይደለም! ዛሬ ለእግዚአብሔር ያደረግኸውን ሁሉ፤ በአገልግሎት የምትደክምበትን፣ የምትሠጠውን፣ የምትፀልየውን፣ በመንግስተ ሰማይ ደጅ ላይ የምትዘራውን ዘር ሁሉ! በእጥፍ ታጭደዋለህ። በእርግጥ ለእግዚአብሔር የተሰጠ ሕይወት የጠፋ ሕይወት አይደለም።



# 2
# ሕይወትህ የእግዚአብሔር ስጦታ ናት

ሕይወትህ ከእግዚአብሔር የተሰጠችህ መልካም ስጦታ ናት። ዛሬ በምንም አይነት አስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ብትሆንም እንኳን፤ ሕይወትህ እስከ አሁን ከተገነዘብከው በላይ ወደፊት ሊያድግ የሚችል ብቃት አላት። ሕይወትህ እኮ ገና መጀመሩ ነው። ይህ ደግሞ መልካም አጋጣሚ ነው። በዚህ ፀጋ ላይ ዘርን መዝራት የአንተ ድርሻ ነው። እስከ ዛሬ ከተገነዘብከው በላይ የበለጠ ታላላቅ ነገሮችን በሕይወትህ ልታከናውን ትችላለህ፤ ይህ መጽሐፍ የተጻፈውም እንዴት አድርገህ በጥበብ መዝራት እንደምትችል ለማሳየት ነው። ዕድሜህ በየትኛውም ክልል ይሁን፤ ለዘላለም ሕይወት በማቀድና ዘርን ለመዝራት በጭራሽ ገና አልረፈደም።

የተፈጠርኸው ለሕይወት ነው። በራስህ መኖርህን ወደ ፍፃሜ ልታመጣው ከቶ አትችልም። አንድ ጊዜ ከተፈጠረ በኋላ የትኛውም ሰብአዊ ፍጡር ከህልውናው ማምለጥ አይቻለውም። እዚህጋ የሚነሣው ጥያቄ ግን የተፈጠርነው ለህልውና ሲባል ብቻ ነው? የሚል ይሆናል። ወይም ደግሞ፤ ሕይወት እንደቃሉ ሀሣብ ሙሉና እጅግ አስደናቂ ሊሆን ይችላልን? የሚል ነው። የሕይወት ጉዳይ የመንግስተ ሰማይና የሲኦል ጥያቄ ጉዳይ ብቻ አይደለም። ይልቁን በመንግስተ ሰማይ የሚከተቱትን ነገሮች ሁሉ የሚመለከት ጥያቄ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ በመንግስተ ሰማይ ሽልማቶች መካከል ብዙ ልዩነት እንዳለ ይጠቁማል። አሁን አንተ ልትገነዘበው ከምትችለው በላይ፤ የመጭው ሽልማትህ ምንነትና አይነት የምትወስነው አንተ ነህ። የየዕለቱ ምርጫዎችህ ከዘላለም ሕይወት

ጋር የተያያዙ ናቸው፤ ይሁንና እግዚአብሔር አንተን ወክሎ አይመርጥልህም:: አንተ ራስህ በማስተዋል ልትመርጥ ይገባል::

## እግዚአብሔር ለአንተ አስደናቂ እቅድ አለው

ኢየሱስ ክርስቶስ የመጣው ሕይወትህ አስደናቂ ይሆን ዘንድ ነው፤ "እኔ ህይወት . . . እንዲበዛላችሁ መጣሁ" (ዮሐ 10፥10):: ጥሩ የሚባል ህይወት ቢኖርህም እንኳን ኢየሱስ የበለጠ ጥሩ ሊያደርገው ይፈልጋል:: አመርቂ ሕይወት ቢኖርህ እንኳን ኢየሱስ መጭ ሕይወትህን የበለጠ አመርቂ ሊያደርገው ይፈልጋል:: እግዚአብሔር ሁልጊዜም ለአንተ ታላቅ እቅድ አለው:: "ለእናንተ የማስባትን አሳብ እኔ አውቃለሁ፤ ፍፃሜና ተስፋ እሰጣችሁ ዘንድ የሰላም ሃሳብ ነው እንጂ የክፉ ነገር አይደለም:: እናንተም ትጠሩኛላችሁ፤ ሄዳችሁም ወደ እኔ ትጸልያላችሁ፤ እኔም እሰማችኋለሁ:: እናንተ ትሹኛላችሁ በፍጹም ልባችሁም ከሻችሁኝ ታገኙኛላችሁ:: ከእናንተም ዘንድ እገኛለሁ ይላል እግዚአብሔር:: ምርኳችሁንም እመልሣለሁ፤ ከአህዛብም ሁሉ ዘንድ እናንተንም ካሣደድኩበት ስፍራ ሁሉ እሰበስባችኋለሁ፤ ይላል እግዚአብሔር:: እናንተንም ለምርኮ ወዳፈለስኩበት ስፍራ እመልሳችኋለሁ" (ኤር 29፥11-14) የሚለውን ቃል እስኪ እንደገና ላስታውስህ::

እግዚአብሔር በሰማይ እንዳለ ምንም ጥርጥር የሌለበት ነገር እንደሆነ ሁሉ፤ እስከ ዛሬ ከተገነዘብከው ይልቅ ለነገህ የተሻለ እቅድ አለው:: ጥያቄው ግን፤ ነገህን የተሻለና የሚደረስበት ለማድረግ ዛሬህን እየተጠቀምክበት ነው? እግዚአብሔር ለነገህ ያለውን ሙሉ እቅዱን በሕይወትህ ይተገብረው ዘንድ ዛሬ ትክክለኛ ውሳኔ



እየወሰንክና ሕይወትህን በአግባቡ እየተጠቀምክበት ነው? የሚል ነው::

## ሕይወትህ ገና መጀመሩ ነው

በምድር ያለው ሕይወትህ ምንም ያህል ርዝመት ይኑረው፤ ፈጽሞ ማብቂያ ከሌለው ህልውናህ ኢምንት ያህሉን ክፍል ብቻ ነው የኖርከው:: በምድር ከምታሳልፈው ከእያንዳንዱ ቀን ቀጥሎ ቢሊዮን እንደገና ቢሊዮን ደግሞ እንደገናም ቢሊዮን ዓመታት በሰልፍ ይጠብቁሃል:: በእነዚህ ሁሉ ውስጥ የምታጭደው ግን ዛሬ የምትዘራውን ነው:: ዘርን መዝራትንም ይሁን ማጨድን አልፈሃቸው መሄድ የምትችላቸው አይደሉም::

ዛሬ የምትኖረው ሕይወት ምንም ያህል አስደናቂ ወይንም ችግሮች የሞሉበት ይሁን፣ መልካምነትን ለተሞላው ነገህ ዛሬ መዘጋጀት ትችላለህ ፈቃድኝነቱ ካለህ ልትፈጽመው ትችላለህ:: ብትዘራበት ወይም እንዲያው ጦም ብታሳድረው፤ ህይወት ከመጭ ዘመንህ ጋር የተያያዘ ጉዳይ ነው:: ነገህ እየቀረበ እየመጣ ነው:: በመንገድ ላይ ነው:: አንተም በእያንዳንዱ ቀን ይህን መንገድ እያዘጋጀህ ነው:: ይህን ቸል ብለህ ልታሳልፈው አትችልም:: ልታመልጠውም አትችልም ለአንተ ህይወት እኮ ገና መጀመሩ ነው:: ደግሞም ከዘላለም እስከ ለዘላለም ያለማቋረጥ ይቀጥላል::

## ሕይወትህ የተፈጠረው ለምርጫ ነው

ህይወት የተፈጠረው ለምርጫ ነው:: ይህ ማለት ደግሞ ህይወት የተፈጠረው ለዘላለም ሕይወት ይዘጋጅ ዘንድ ነው:: የዘላለም ሕይወት እየመጣ በመሆኑ፤ እያንዳንዱ ሰው ደግሞ በጥቂት በጥቂቱ ወደዚህ ግብ እያዘገመ ነው:: ዛሬ አንተ አንድ ቀን ወደዘላለም ህይወት ተቃርበሃል:: በእያንዳንዱም ቀን በዘላለም

ህይወት ላይ ተፅእኖ ያለውን ውሣኔ እየወሰንክ ትጓዛለህ። መወሰን የመቻል ብቃት እግዚአብሔርን የመምሰል ስጦታ ነው። ይህ መወሰን የመቻልን ባህሪ እውነት ያደርገዋል፤ በመሆኑም ለእግዚአብሔር ብንኖርና እርሱንም ብናገለግለው እግዚብሔር የገባልን የፀጋው ተስፋ ሽልማት እውነት ይሆናል። የምትወስነው የትኛውም ትክክለኛ ውሳኔ፣ እግዚአብሔርን ለማስደሰትና ለመውደድ የምታደርገው ማንኛውም ነገር ወይም ደግሞ እግዚአብሔርን ማገልገልህና ሌሎችን መባረክህ፣ በዘላለም ሕይወት ሽልማትህ ላይ የሚጨምረው ነገር አለ። የዘላለም ሕይወት፤ መጠነ ሰፊ የሆነና ማብቂያ የሌለው ሽልማትህን እንድትቀበል እግዚአብሔር ያዘጋጀው እቅድ፣ የሚፈጸምበት ስፍራና ጊዜ ነው።

## በመንግስተ ሰማይ ነጥብህ እየተቆጠረ ነው

እግዚአብሔር ጥቅል የሆነ፣ ሙሉና ፍጹም ትክክለኛነት ያለው የህይወት እንቅስቃሴህን የሚያሳይ ዘገባ እንዲኖር እቅድ አለው። እግዚአብሔር የሚይዘውን የተሟላ ዘገባ ደረጃ የሚመወዳደር የተጠናቀቀ ዘገባ ፤ በዚህ ምድር ላይ ማንም የለውም። ያለ ምንም ጥርጥር በመንግስተ ሰማይ ነጥብህን የሚመዘግቡት መላእክት ናቸው። በትንቢተ ዳንኤል 4፥17 ጠባቂዎች የሚለው በዕብራይስጡ ቋንቋ መላእክትን የሚያመለክት ነው። ማንኛውም ክርስቲያን ብቻውን አይደለም፤ የእግዚአብሔር መላእክት ሁልጊዜም በአጠገቡ ናቸው (ማቴ 18፥10፤ መዝ 34፥7፤ ዕብ 1፥14)። አጠገብህ የሚሆኑት አንተን ለመርዳት ብቻ ሳይሆን፤ የህይወት እንቅስቃሴህን ለመመዝገብ የእግዚአብሔር ፀሀፊዎች ስለሆኑ ነው። በሽልማትህ ላይ ተጨማሪ ሽልማት የሚያስገኙ



ነጥቦችህን በሚመዘግቡበት ጊዜ መላእክቱ እንዴት ደስተኞች ናቸው!

በመንግስተ ሰማይ የእያንዳንዱ አማኝ ስም የተመዘገበበት የበጉ የህይወት መጽሐፍ አለ። ይህ ደግሞ በመጽሀፍ ቅዱስ ውስጥ ከስምንት ጊዜ በላይ ተጠቅሶ ይገኛል (ዘጸ 32፥32-33፤ መዝ 69፥28፤ ዳን 12፥1፤ ሉቃስ 10፥20፤ ፊልጵ 4፥3፤ ራዕይ 20፥12፤ 21፤ 27)። የእያንዳንዱን ህይወት ሙሉ የሆነ ዘገባ የያዙ ሌሎች መጻህፍትም ደግሞ አሉ። (መዝ 87፥6፤ ዳን 7፥10፤ ራዕይ 20፥12)። "የዚያን ጊዜ እግዚአብሔርን የሚፈሩ እርስ በእርሳቸው ተነጋገሩ፤ እግዚአብሔርም አደመጠ፤ ሰማም፤ እግዚአብሔርንም ለሚፈሩ፤ ስሙንም ለሚያስቡ የመታሰቢያ መጽሐፍ በፊቱ ተፃፈ። እኔ በምሠራበት ቀን እነርሱ የእኔ ገንዘብ ይሆናሉ፣ ይላል የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር። ሰውም የሚያገለግለውን ልጁን እንደሚምር እንዲሁ እምራቸዋለሁ። ተመልሳችሁም በጻድቁና በሀጢያተኛው መካከል ትለያላችሁ" (ሚል 3፥16-18)።

በመንግስተ ሰማይ በህይወት እንቅስቃሴ ዘገባ መዝገብ ላይ የሚመዘገቡ ጉዳዮች እንዴት ያሉ ናቸው? መጽሐፍ ቅዱስ ብዙ አስተያየቶችን ይሰጠናል።

| | |
|---|---|
| **ሙሉው የህይወት እንቅስቃሴህ** | ሮሜ 14፥10-12፤ 1ቆሮ 3፥11-15፤ 2ቆሮ 5፥10፤ 1ጴጥ 4፥5 |
| **የአፍህ ቃል** | መዝ 19፥14፤ ሚል 3፥16፤ ማቴ 12፥36-37 |
| **አስተሳሰብህ** | ምሣ 15፥26፤ 19፥14፤ |

| | |
|---|---|
| | መዝ 94፥11፤ 139፥2፤ 23፤ ኢሣ 55፥7፤ ማቴ 9፥4፤ 15፥9፤ ሮሜ 2፤ 15-16፤ ዕብ 4፥12 |
| **ሚስጥሮችህ** | መክ 12፥14፤ ሮሜ 2፥16 |
| **የድርጊትህ ምክንያቶች (ሰበበ ነገር)** | ምሣ 16፥2፤ 1ቆሮ 4፥5 |
| **እንባህ** | መዝ 56፥8 |
| **ፀሎቶችህ** | ራዕ 5፥8፤ 8፥3-4 |
| **ለእግዚአብሔር የምትሰጠው ስጦታ** | ፊልጵ 4፥17-18፤ ዕብ 13፥16 |
| **ለሌሎች የምታደርገው እገዛ** | ማቴ 25፥34-40 |
| **እርዳታህን የሚፈልጉትን የምትጎበኘው ጉብኝት** | ማቴ 25፥34-40 |

አነዚህ ከላይ የተዘረዘሩት ለናሙና ያህል ብቻ የቀረቡ ናቸው። የሰማያዊው መዝገብ ዝርዝር አንተ ከምትገምተው በላይ ረቂቅ ነው። ለእግዚአብሔር የምትኖር ከሆነ፤ ሌሎችን ለመውደድ የትኛውንም አጋጣሚ ፈልግ፤ የተባረከ ለመሆን፤ እግዚአብሔርን ለመውደድ፤ ለሌሎች ለመጸለይና ከአንተ ህይወት ለሌሎች የሚተርፍ የመጽናናት ምንጭ መፍለቅ የሚችል ከሆነ (ዮሐ 7፥38)፤ ምናልባትም ከእነዚህ ነገሮች ስለ ጥቂቶቹ እንኳን እግዚአብሔር አንድ ቀን እንደሚሸልምህ ልታስታውስ ያስፈልግሃል።



አንዳንድ ጊዜ እግዚአብሔር ከአመታት በፊት ተናግረናቸው ወይም አድርገናቸው የረሣናቸውን ነገሮች እንዴት እንደተጠቀመባቸው በማስታወስ ያስደንቀናል። ከአንድ መቶ ዓመት በፊት፤ አስጢፋኖስ ገርላት የተባለ ሰው አንድ ቀን እጅግ ጥቅጥቅ ያለ ደን ወዳለበት የአሜሪካ ግዛት ለስብከት እንዲወጣ ምሪት ይቀበላል። ያ ደግሞ ሲቋቋመው ያልቻለ የመንፈስ ቅዱስ አስቸኳይ የሆነ አመራር ነበር። ምሪቱን ተቀብሎ በደን ውስጥ ወዳለው የእንጨት መሰንጠቂያ ካምፕ በደረሰ ጊዜ፤ ወደ ሌላ ስፍራ ተንቀሳቅሰው መሄዳቸውንና የመኖሪያ ጎጆዎቻቸውም ባዶ መሆኑን ተረዳ። ይሁን እንጂ እግዚአብሔር እንደላከው ፍጹም እርግጠኛ በመሆኑ፤ ወደ ባዶዎቹ ጎጆዎች በመሄድ እግዚአብሔር በልቡ ያስቀመጠውን መልዕክት ለግድግዳዎቹ ሰበከ። ከዚያ በኋላ ወደ ቤቱ ተመለሰ። ለባዶ ጎጆዎች ለመስበክ እግዚአብሔር ለምን እንደላከው ከቶውንም ሊገባው አልቻለም።

ከብዙ ዓመታት በኋላ በኢንግላንድ አገር ውስጥ፤ በሎንደን ድልድይ ላይ እየተንጎራደደ ሣለ አንድ ሰው ከንዱን ለቀም አድርጎ ያዘውና፤ “እስይ በመጨረሻው አገኘሁህ” አለው። እስጢፋኖስም፤ “እንደተሳሳትክ ይመስለኛል” ሲል መለሰ። ሰውየውም፤ “በጭራሽ ከአመታት በፊት በአሜሪካ ጥቅጥቅ ደኖች ውስጥ ለባዶ ጎጆዎች የሰበከኸው አንተ አይደለህምን?” ሲል ጠየቀው። “አዎን” ሲል አመነ ሰባኪው። “ነገር ግን በዚያ አኮ ማንም አልነበረም”። “በእንጨት መሰንጠቂያው ካምፕ ውስጥ ለሚሠሩት ሠራተኞች አለቃቸው ነበርኩ”። እንግዳው ሰውየ ማብራሪያውን መስጠት ጀመረ፤ “ወደሌላ ስፍራ ተንቀሳቅሰን ነበር። ይሁን እንጂ በወቅቱ

አንዱን የሥራ መሣሪያየን በካምፑ ውስጥ ጥየው መሄዴን አላስተዋልኩም:: ያንን መሣሪያ ለመውሰድ ተመልሼ በመጣሁ ጊዜ ከባዶዎቹ ጎጆዎች በአንደኛው ድምፅ ሰማሁ:: በሰንጣቃው መካከል አጮልቄ ስመለከት አንተን አየሁህ:: አንተ አላየኸኝም ነበር፤ እኔ ግን ቀሪውን ስብከትህን በጥሞና ተከታተልኩ:: እግዚአብሔር ልቤን ነካው፤ በሀጢያቴም በእጅጉ ተፀፀትኩ:: ከጥቂት ጊዜያት በኋላም መጽሐፍ ቅዱስ ገዛሁ፤ ሀጢያቴንም ተናዘዝኩ እናም ክርስቲያን ሆንኩ:: ከዚያ በኋላ ደግሞ በእኔ ሥር የነበሩ ሰራተኞችን ወደ ጌታ መምራት ጀመርኩ:: ያ የአንተ ስብከት ቢያንስ ቢያንስ በሺዎች የሚቆጠሩ ሰዎችን ወደ ጌታ መርቷል፤ ከነዚህ ሠራተኞች ሦስቱ ደግሞ አሁን የወንጌል አገልጋዮች ሆነዋል!"

እንደነዚህ አይነቶቹን አስደናቂ ጉዳዮች ነው መንግስተ ሰማይ አሁንም አሁንም ተደጋግመው መገለጣቸው አይቀርም::

በ1987 ዓ.ም በብራዚል የነበረኝን አገልግሎት ፈጽሜ ስመለስ በፍሎሪዳ ግዛት በምትገኘው በኦርላንድ አረፍ አልኩ:: ምክንያቴ ደግሞ በዚያ በሚካሄደው የሚስዮናዊ አገልግሎት መሪዎች ጉባኤ ላይ ለመካፈል ነበር:: የመጀመሪያው ክፍለ ጊዜ ከተጠናቀቀ በኋላ በአዳራሹ አንድ ምሰሶ አጠገብ ቆሜ ሳለ፤ የአንድ የወንጌል ተልዕኮ መሪ የሆነ ከዚህ በፊት አይቼው የማላውቀው ሰው በድንገት እጆቹን ወደ እኔ ዘርግቶ፤ "ወንድሜ" ሲል ደስታ የተሞላበት ሰላምታ ሰጠኝ "እርግጠኛ ነኝ በዚህ የተገኘሁት አንተን ለማግኘት መሆን አለበት!" አለ ጨምሮ::

"ለምን? ግን አንተ ማነህ?" አልኩት::



"በፀሎትህ ዓለምን ንካት" በሚለው መጽሐፍህ ውስጥ፤ በሁለተኛው የዓለም ጦርነት አንድ ሌሊት፤ ግራፍ ስፒ የተሰኘች መርከብ ሰርጓጅ የጦር መርከብ፤ አንዲት የመንገደኞች ማመላለሻ መርከብን ለማጥቃት በተቃረበች ጊዜ፤ የዚች መርከብ እንቅስቃሴ እንዲገታ ስትፀልይ እግዚአብሔር ተግተህ እንድትማልድ ሸክም እንደሰጠህ አነበብኩ:: (በዚች መርከብ ሰርጓጅ የጦር መርከብ አማካኝነት በርካታ የመንገደኛ ማመላለሻ መርከቦች ጥቃት ደርሶባቸው በብዙ መቶ የሚቆጠሩ መንገደኞች ከነህይወታቸው በባህር ውስጥ ሰጥመዋል) በዚያው ምሽት ያች የመንገደኞች ማመላለሻ መርከብ ባልታወቀ ሃይል ተገፍታ ወደ ሞንትቬዶ የባህር ወደብ በሰላም እንደደረሰችም በዚሁ መጽሐፍህ ውስጥ ጠቅሰሃል::

የሚስቴ አባት የእንግሊዝ ዜግነት ያላቸው ሀኪም ሲሆኑ ነዋሪነታቸውም በደቡብ አሜሪካ ውስጥ ነበር:: የሁለተኛው ዓለም ጦርነት በተጀመረ ጊዜ ሰላማዊ ሥፍራ ነው ብሎ ወደገመተው ወደ እንግሊዝ አገር ቤተሰቡን ይዞ ተመለሰ:: በዚያ ጊዜ ሴት ልጁ ከአንድ አርጀንቲናዊ ወጣት ጋር ፍቅር ጀምራ ነበር:: ከጥቂት ወራት በኋላ እንደገና ወደ ደቡብ አሜሪካ በመመለስ ይህንኑ ሰው ለማግባት ወሰነች:: በዚያች አንተ የምልጃ ፀሎት ባደረክባት ሌሊት የእኔ እናት የእንግሊዝ ንብረት በሆነች በዚያች የመንገደኞች ማመላለሻ መርከብ ውስጥ በሞንትቬዶ የባህር ወደብ ነበረች:: ያን ጊዜ ተግተህ ባትፀልይ ኖሮ፤ መርከብ ሰርጓጇ ግራፍ ስፒ ያችን የመንገደኞች ማመላለሻ መርከብ ባጠቃቻት፤ እናቴም ከመርከቧ ጋር ሰጥማ በቀረች ነበር:: እናም አባቴን ማግባት አትችልም እኔም ተወልጄ ወደዚህ ዓለም አልመጣም ነበር:: ዛሬ በሕይወት ያለሁትና እግዚአብሔርን የማገለግለው ከአንተ የተነሳ ነው::

ወዲያውኑ፤ "ግን እኮ ምናልባትም በሺህ የሚቆጠሩ ሌሎች ሰዎችም በዚያው ሰዓት ፀልየው ሊሆን ይችላል" ስል መለስኩለት::

"በሺህ ስለሚቆጠሩት ሰዎች የማውቀው ነገር የለም፤ አንድ ነገር ግን አውቃለሁ፤ እግዚአብሔር ያንን ሽክም ለአንተ ሰጥቶህ ነበር እናም ፀልየሃል:: ዛሬ እግዚአብሔርን የማገለግለው ከአንተ የተነሣ ነው" ሲል መለሰልኝ::

ያ ሰው ዶ/ር ሊዮስ ቡህ ሲሆን፤ ክጥቂት ዓምንታትም በኋላ የመጀመሪያው የመላው ላቲን አሜሪካን አገሮች የአለም አቀፍ የወንጌል አገልግሎት ጉባኤ ሊቀመንበር የሆነ ሰው ነው:: ይህ ድርጅት ጽህፈት ቤቱን በብራዚል ውስጥ በሳኦፖሎ ከተማ ያደረገ ነው:: በተጨማሪም የአለም ዓቀፍ ፓርትነርስ ታላቁ የወንጌል ማህበረሰብ ከፍተኛ መሪም ነው:: ክብሩን ሁሉ እግዚአብሄር ይውሰድና እግዚአብሔር እንዴት እኔን እንደተጠቀመ ሳስበው ታላቅ ድንጋጤ ይሰማኛል:: መንግስተ ሰማይ እንዲህ አይነቱን አስደናቂ ክስተቶች ለእኛ እንደያዘች ተስፋ አታደርግም? እግዚአብሔር እንዴት ፀሎቶቻችንን እንደመለሳቸው፤ ለመንግስቱ መስፋት ያፈሰስነው ገንዘብና መታዘዛችንን እንዴት እንደተጠቀመ ስናውቅ ደግሞ ደጋግመን መገረማችን አይቀሬ ነው::

ሌሎችን ለመባረክ ንቁ መሆን ለአንተ ለራስህ ምን ያህል ጠቃሚ እንደሆነ ተረዳህ? ለእግዚአብሔር መኖርህስ? በመንግስተ ሰማይ በሚኖርህ ሽልማት ላይ ተጨማሪ ብድራት ማስገኘት በሚችል በምን አይነት እንቅስቃሴ ላይ ነው ያለኸው? ወደፊት ለሚጠብቅህ ሽልማት በእያንዳንዱ ቀን ዘርን ዝራ:: አሁን አንተ ሕይወትህን እየመዘንክ ያለኸው እግዚአብሔር ነገሮችን በሚመዝንበት ሚዛን ነውን?



## እግዚአብሔር ሕይወትህን የሚመዝነው እንዴት ነው?

እግዚአብሔር ሕይወትን የሚመዝነው እንዴት ነው? አንተንስ እየመዘንህ ያለው እንዴት ነው? እግዚአብሔር የሚመዝነው በጊዜ ቅደም ተከተል እንዳልሆነ ግልጽ ነው:: "እናንተ ግን ወዳጆች ሆይ፤ በጌታ ዘንድ አንድ ቀን እንደ ሺህ ዓመት፤ ሺህ ዓመትም አንደ አንድ ቀን እንደሆነ ይህን አንድ ነገር አትርሱ" (2ጴጥ 3፥8):: ሕይወት ማለት ከቀናት፤ ከዓምንታት ከዓመታትም በላይ ነው:: እግዚአብሔር ስለ ሕይወት ያለው እይታ እኛ ሰዎች ካለን የአመለካከት ዘይቤ እጅግ የተለየ ነው::

እጅግ ትልቅ የሆነ ሕይወት የግድ ረዥም፤ ውጥረት የበዛበትና እጅግ ዝነኛ የሆነ ሕይወት መሆን የለበትም:: በምድር ላይ እጅግ ጀግኖች የነበሩ የአንዳንድ ሰዎች ሕይወት በእግዚአብሔር እና በመንግስተ ሰማይ ሚዛን ሲለካ ምጥ የበዛበት ሕይወት ነው:: ምናልባትም እጅግ ታላላቆች የሆኑ በመንግስተ ሰማይ ሚዛን ሲገመገሙ በሰው ልጆች ታሪክ ውስጥ ያላቸው ድርሻ ኢምንት ያህል ብቻ ነው::

እግዚአብሔር "ይህን አንድ ነገር አትርሉ" ሲል (2ጴጥ 3፥8) ታላቁን እደጋ እያመላከተን ነው:: ሙሉ በሙሉ ዓለማዊ በሆነ ባህል የተከበብን መሆኑን ካልተገነዘብን ሰዎችን፤ እንቅስቃሴዎችን፤ ህይወትን ራሷን እንኳን በዚያው ዓለማዊ በሆነ ልኬት መገምገም እንጀምራለን:: ሕይወታችንንና ክርስቲያናዊ አኗኗራችንን በእግዚአብሔር እተያይ ማየት ያስፈልገናል::

አንዲትን ቀን ለእግዚአብሔር መኖር ለአንድ ሽህ ዓመታት ከተጠራቀመ የሕይወት ዋጋ እኩል እሴት ሊኖረው ይችላል:: ጊዜ

በእግዚአብሔር ነገር ላይ የተዘራ ከሆነ በእግዚአብሔር ዘንድ ዋጋ አለው፡፡ የባከነ ጊዜ ግን ዘላለማዊ ኪሣራ ነው፡፡ በሽህ ዓመታት መካከል የባከነ ጊዜ በእግዚአብሔር እይታ የአንዲትን ቀን ያህል ዋጋ ያለው አይደለም፡፡ ጆን ዊስሌይ ለሰባኪዎቹ እንዲህ አለ፤ "በጭራሽ ሥራ ፈቶች አትሁኑ፤ እርባና ቢስ ሠራተኞችም አትሁኑ"፡፡

እግዚአብሔር ሕይወትን የሚመዝነው በዙሪያህ ባሉ በተጨናነቅህባቸው ነገሮች ይሆን? ይህ የሚወሰነው ባጨናነቁህ ነገሮች ምንነት ነው፡፡ ምናልባትም ብዙው ጊዜህ እንዲያው ባክኖ ሊሆን ይችላል - ይህ ዘላለማዊ ኪሣራ ነው፡፡ ይሁንና አንዳንድ ምርጫዎችህና እንቅስቃሴዎችህ በእግዚአብሔር እይታ ታላቅ ዋጋ የሚሰጣቸው ናቸው፡፡ በእግዚአብሔር የሚዛን ልኬት ህይወትን የመመዘን አስፈላጊነትን እየተገነዘብክ ነውን?

ዛሬ ሃያላን ተብለው ነገ ግን እንደሞኝ ከሚቆጠሩት እንዳትሆን ልብ በል፡፡ በቤተሰቦችህ፣ በምትኖርበት ማህበረሰብ ወይም በቤተክርስቲያን ውስጥ በሰዎች እይታ ታላቅ ስትሆንም ልብ በል፡፡ ድነትን ያገኘ ሰው ሆኖ በእግዚአብሔር እይታ ዘላለማዊ ሞኝ መሆን ይቻላልና፡፡ ድነትን ካገኘህ በኋላ በሕይወትህ የሠራኸው ሁሉ እጅግ ታላቅ የሆነ ከዘላለም ህይወት ጋር የተሣሰረ ጉዳይ ነው (1ቆሮ 3፥11-15)፡፡



## ዋጋ ያለው ህይወት

ዋጋ ያለው እውነተኛ ሕይወት የሚባለው ለእግዚአብሔር የተኖረ ህይወት ነው፡፡ ሌላው ሁሉ ግን ትርፍና ተራ በጌታም ዘንድ ተቀባይነትን ያላገኘ ሕይወት ነው፡፡ ያልጠፋ የሚባለው እውነተኛ የሆነ ሕይወት እግዚአብሔርን ደስ ለማሰኘት የተኖረ ሕይወት ነው፡፡ ጊዜዎቹ ፈጥነው የሚፈተለኩ በመሆናቸው እድሎችህም እንዲሁ ፈጥነው ያልፋሉ፡፡ የምታገኛቸው አጋጣሚዎችህ ዘላለም ቆመው የሚጠብቁህ አይደሉም፡፡ ያለህ ብቸኛ ጊዜ አሁን፤ ያለህም ምትክ የሌላት ቀን ዛሬ ናት፡፡ ትላንት ፈጽሞ ተመልሶ እንደማይመጣ፣ ሕይወትህ አንድ ጊዜ ካለፈች ዳግመኛ አትመለስም፡፡

በምድር ላይ የምትሰፋበትን ነገር ሁሉ ከሞት በኋላ እዚሁ ጥለኸው ታልፋለህ፤ የሞትህ ቀን በቀረበ ጊዜ ሁሉን ተሰናብተህ ትጓዛለህ፡፡ በምድር ላይ ስለ እግዚአብሔር ብለህ የዘራኸው ዘር ግን ለዘላለም ሕይወት ቋጥረህ ያስቀመጥከው ጥሪትህ ነው፡፡ በዚያ ከጌታ ጋር ፊት ለፊት በተገናኘህ ጊዜ ሁሉንም ታገኘዋለህ፤ ፍሬ አፍርቶም ታየዋለህ፡፡

እና በመንግስተ ሰማይ ደግመህ ለማታገኘው ነገር አጭር የሆነ የእድሜህን ጊዜ ሁሉ መዝራት ምንኛ ሞኝነት ነው? አ! ጊዜህን ሁሉ፣ ፀሎትህን፣ ፍቅርህንም ጭምር በዘላለም ሕይወትና በሰማይ ለሚጠብቅህ ሽልማት መዝራት ምንኛ ብልህነት ነው!

ዊስሊይ ዱዌል

# 3

## በመንግስተ ሰማይ፤ ግን . . .

በሚሊዮን የሚቆጠሩ ክርስቲያኖች፣ ከዘላለም እስከ ዘላለም ድረስ ከእግዚአብሔር ጋር በሰላም ተጠብቀው ለዘላለሙ በመንግስተ ሰማይ እንደሚኖሩ እየተረዱ መጥተዋል:: ነገር ግን እጅግ ብዙ የህይወት አጋጣሚዎቻቸውን ሳይጠቀሙ አጥተዋቸዋል:: ማንም ሰው ምስጋናን ከእግዚአብሔር እንደሚቀበል ሁሉ እነርሱም ከእግዚአብሔር ምስጋናን ይቀበላሉ (1ቆሮ 4፥5):: ነገር ግን የህይወታቸው ምን ያህሉ ክፍል በከንቱ እንደ ባከነ ከታላቅ ድንጋጤ ጋር ይረዱታል::

ከዘላለም ህይወት ክስተቶች ሁሉ ለብዙ ክርስቲያኖችና ለአልዳኑት ሰዎች አስደናቂ የሚሆነው በኢየሱስ የፍርድ ዙፋን ፊት መቆማቸው ነው:: እያንዳንዱ ክርስቲያን በዚያ ይገኛል:: እግዚአብሔር ሁሉንም. ክርስቲያኖች የህይወት ዘመናቸውን ስለጨረሱበት መንገድ ይጠይቃቸዋል:: የታላቅ ደስታ ቀን ይሆናል:: ነገር ግን እጅግ የመደነቅም ቀን ሊሆን ይችላል::

አንድ ጊዜ አንድ ክርስቲያን ሰመሞት እያጣጠረ ሳለ፣ በድንገትም "ጠፋሁ! ጠፋሁ! ጠፋሁ!" እያለ መጮህ ጀመር:: ከቤተሰቦቹ እንደኛዋ በዚህ ሰው ጩኸት እጅግ ደንግጣ ፈጠን በማለት ወደ እርሱ ቀረበች:: ምናልባትም ይህ ሰው በደካማ ሥጋው ሁኔታ ውስጥ የድነት ዋስትናውን ያጣና ሰይጣንም እየከሰሰው ይሆናል ስትል አሰበች:: እርሱ ግን "እ! በጭራሽ እንደሱ አይደለም፣ ነገር ግን የጊዜየንና የህይወቴን አብዛኛውን ክፍል አባክኜ ጨርሼዋለሁ:: በእግዚአብሔር ፀጋ ድኛለሁ፤ ነገር ግን ለእግዚአብሔር እጅግ አብዝቼ፣ እብልጨም ብኖርለት ኖሮ ላገኝ የሚገባኝን ሽልማት አጥቻለሁ!" ሲል መለሰ::

መጽሐፍ ቅዱስ ሕይወታችንን በኢየሱስ ክርስቶስ መሠረት ላይ ቋሚነት ባላቸው የከበሩ መንፈሳዊ ወይም ዘላቂነትና ዋጋም በሌላቸው ነገሮች መገንባት እንደምንችል ያስተምረናል (1ቆሮ 3፥11-15):: እንደነዚህ ያሉት የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባቦች የተፃፉት ለክርስቲያኖችም ጭምር ነው:: በመሆኑም ታላቅ ትኩረት ሰጥተሮ ሊያስተውሏቸው ይገባል:: ጳውሎስ እየተናገረ ያለው የፍርድ ቀን፤ ክርስቲያኖች ድነትን ከተቀበልን በኋላ እኔና አንተ በሕይወታችን ምን እንደሠራን የምንገመግምበት ቀን መሆኑን ነው::

ሐዋርያው ሕይወትህን በክርስቶስ ላይ ልትገነባ እንደምትችል ይገልፃል (ቊ 14) (ያ ማለት እውነተኛ ክርስቲያን መሆን ትችላለህ ማለት ነው):: ይሁን እንጂ አብዛኛው ግንባታህ ከወርቅ፣ ከብርና ከከበረ ድንጋይ ይልቅ በእንጨት፣ በሣር ወይም በአገዳ የተገነባ ሊሆን ይችላል:: ዛሬ እየሠራሃቸው ካሉ ነገሮች ከወርቅ ይልቅ በመንግስተ ሰማይ ምን ያህሉቹ አገዳዎች ናቸው? ጳውሎስ በህይወትህ ውስጥ የጨመርካቸው አገዳ የሆኑ ነገሮች ሁሉ ዘላለማዊ ኪሣራዎች እንደሆኑ ይናገራል:: የሚቃጠሉም ናቸው::

በእኔና በአንተ ሕይወት ውስጥ አንዳንድ ነገሮች ብዙውን ጊዜያችንን የሚፈጁ ቢሆኑም ዘላቂ የሆነ ዋጋ የላቸውም፤ አካላዊ ጤንነትን፣ አይምሯዊ ጤንነትን ወይም ጥበብን አይጨምሩንልም:: አካላዊና ገንዘብ ነክ የሆኑ ፍላጎቶቻችንን ሰማሟላትም ረብ ያላቸው ነገሮች አይደሉም:: ሌሎችንም ቢሆን አይባርኩም፤ አይጠቅሙም::

ከሀሉትህንም ለመጨመር ጠቀሜታ የላቸውም። አንተን ምርታማ ለማድረግ የሚያበረክቱት አስተዋፅኦ የለም።

ጊሮላሞ ሳቮናሮላ (ከ1452-1498 የኖረ) የተባለው ኢጣልያዊ የተሃድሶና የመነቃቃት ሰው፤ እግዚአብሔር ከተሃድሶው ዘመን በፊት እጅግ ታላቅ በሆነ መንገድ የተጠቀመበት ሰው ከመሆኑም በላይ፤ ከእንጨት የተሠራ ማማ ላይ በእሣት ተቃጥሎ ሰማእትነትን የተቀበለ ሰው ነው። ይህ ሰው ሲሰብክ፤ "ያደግከው በዓፅም ውስጥ ነው? ሌሎች ላይ ሲስቁ እና ሲደስቱ አንተ የግድ ጠንክረህ ሥራ። ሌሎች አስቸጋሪ ነው ብለው የሚገምቱትን ነገር ለማድረግ መሻቱ አለህን? ሕይወትን ህላፊነትን ለሚያስከትል ነገር የግድ መስጠት ይኖርብሃል። ሥነ ምግባራዊና አካላዊ በሆነው ነገር መጠንክር ትፈልጋለህ? ፈተናን መቋቋም የግድ ነው። ለእነዚህ መልካም ነገሮች ብድራትህ በቅድሚያ ልትቀበል ትችላለህ። አንድ ነገር ግን ልብ ብለህ አስተውል፤ የስዕሉ ሌላኛው ገጽታ ማለትም የክፉ ሥራዎች ዋጋ ግን የሚከፈለው በኋላ ነው"።

የትኞቹም ንስህ የገባንባቸው ህጢያቶች፤ ዳግም ላንጠየቅባቸው በመስቀሉ ላይ ተፈርዶባቸዋል (ዕብ 8፥12)። አሁን ጥያቄው የህጢያት ጉዳይ አይደለም። የክርስቶስ የፍርድ ዙፋን ለክርስቲያኖች ሽልማታቸውን ይቀበሉ ዘንድ ህይወታቸው የሚመዘንበትና የሚመረመርበት ነው። ራሳችንን ደግመን ደጋግመን ልንጠይቃቸው የሚገቡ ጥያቄዎች አሉ። እንቅስቃሴዎቻችን፣ የጊዜ አጠቃቀማችንና የገንዘብ አወጣጣችን፤ በእግዚአብሐር የፍርድ ወንበር ፊት ህይወታችንን በወርቅ፣ በብር፣ በከበሩ ድንጋዮች ወይስ በእንጨት፣ በገለባ፣ በአገዳ (1ቆሮ 3፥12) እየገነባን ነው? እነዚህ ነገሮቻችን በእግዚአብሔር የፍርድ እሳት ፊት ተፈትነው የሚፀኑ



ናቸውን? የክርስትና ደቀ መዛሙርት እንደመሆናችን መጠን በዚህ ዘላለማዊነት ውስጥ ጨምረን ማሣየት የምንችለው ነገር የለምን? ወይም ደግሞ እነዚህ ለዘላለም ህይወት የምንዘራቸው ዘሮች ፍቅር የተሞላውንና ቅዱስ የሆነውን ክርስቶስን ደስ የሚያሰኙ፤ በመጨረሻውም ተጠቃሚ የሚያደርጉንና መልካምን የሚያሳጭዱን ናቸውን? የሚለውን ነው።

በሌላ አገላለጽ፤ ጊዜዬ፣ ልዩ ተሰጥኦዬ፣ የገንዘብ አወጣጤ በማስተዋል የሚደረግና ህይወቴን ትርፋማ በሚያደርግ መንገድ እየተዘሩ ነውን? ወይስ ይህ ለአንዳንዶቻችን በክርስቶስ መንግስት ውስጥ ማድረግ የሚገባንን ነገር ማድረግ ባለመቻላችን ዘላለማዊ ኪሣራ ይሆን? በክርስቶስ ዙፋን ፊት በምቆምበት ጊዜ በምድር የዘራሁት ዘር ስለእኔ ምን ይመሰክርልኝ ይሆን? መልካም ነገርን ወይስ ህፍረትን?

በምድር የኖርኩት ኑሮ አርሱን በማገልገሌ በኢየሱስ ፊት ሞገስንና ምስጋናን ያስገኝልን ይሆን (ማቴ 25፥35-39)? "መቼ ነው እንዲህ ያገለገልኩህ" እያልኩ በመደነቅ ስጠይቀው፤ ረዥም ጊዜ የሆናቸውንና ፈጽሞ የረሣኋቸውን ነገሮች እያስታወሰ፤ "የራስህን ፍላጎት ክደህ ጊዜህን በፀሎት ባጠፋህበት በዚያ ጊዜ ወይም ሌሎችን በባረክበት ጊዜ ያን ጊዜ እኔን ባርከኸኛል" ይለኝ ይሆን? ወይስ ምናልባትም ጌታ "ያችን አስራ አምስት ደቂቃ፤ ቴሌቪዥን ስትመለከት ያጠፋሃት ያች ጊዜ፤ በፀሎት ዘርን በመዝራት ብታጠፋት ኖሮ አንድ ሌላ ሰው የመንግስተ ሰማይን መንገድ ማግኘ ት በቻለ ነበር፡፤ እንዲያው በከንቱ ለራስህ ያጠፋኸው ያ ገንዘብ መንግስቴን ሊያስፋ የሚችል ነበር፣ በጣም ነው ያዘንኩብህ፤ ለእኔም

ለሌሎችም አልሆንክም። የዘላለም ሕይወትን ታገኝ ዘንድ ድነሀል፤ ይሁን እንጂ አንተ ታገኘው ዘንድ ያዘጋጀኋቸውን ሁሉንም ሽልማቶች ልትቀበል አትችልም" ይለኝ ይሆን?

## ሕይወት ባለቤት አላት

"በዋጋ ተገዝታችኋልና የራሳችሁ አይደላችሁም፤ ስለዚህ በሥጋችሁ እግዚብሔርን አክብሩ" (1ቆሮ 6፥19-20)። ሥጋችን የእኛ አይደለም። የኢየሱስ ነው። ማስተዋል በጎደለውና ከንቱ በሆነ መንገድ ብዙ በመብላትና ጎጂ በሆኑ ሱሶች በመጠመድ ልናበላሸው መብት የለንም። በልዩ ልዩ ሱሶችና ለውነታችንን አስፓርታዊ እንቅስቃሴ ባለማስለመድ ሕይወታችንን ልናሣጥር መብት የለንም። ስጋችንና ሕይወታችን (ይህ ማለት ጊዜያችን ነው) በክርስቶስ ኢየሱስ በዋጋ የተገዙ ናቸው።

ኢየሱስ የራሱ ያደረገን ስለፈጠረን ነው፤ ይህም ብቻ አይደለም በመስቀል ላይ የደሙን ዋጋ ስለከፈለልን ነው። ሥጋችንን፣ እእምሯችንን፣ ልዩ ተሰጥአዋችንን ወይም ጊዜያችንን በከንቱ ማባከን እነኝሀን ነገሮች ከክርስቶስ እጅ ላይ በሀይል እንደመቀማት ይቆጠራል። ይህ ደግሞ አሥራታችንን ለእግዚአብሔር ባልሰጠን ጊዜ እግዚአብሔርን እንደሰረቅነው እንደሚቆጠረው ነው (ሚል 3፥8-9)። ፍጹም በእርግጠኝነት ጊዜያችንን፣ ሀይላችንን ወይም ልዩ ተሰጥአዎቻችንን ያለ አግባብ ማባከን የሀይወታችንን የተወሰነ አካል ከእግዚአብሔር ላይ መስረቅ ነው። እኛ የእግዚአብሔር ነን (ሮሜ 14፥8)። በሀይወት ቢሆን በሞታችን ጌታን ከፍ ልናደርገው ይገባል (ፊልጵ 1፥20)።



በጌታ መኖር

በጌታ መኖር ማለት ለጌታ መኖር ማለት ነው። ጳውሎስ እንዲህ ይላል፤ "ለእኔ ሀይወት ክርስቶስ ነው" (ፊልጵ 1፥21)። በእርግጠኝነት ይህ ማለት ደግሞ በቅድስና መኖር፣ በፍቅር መኖር፣ ከክርስቶስ ጋር ሀብረት ያለው ኑሮ መኖር፣ የመንፈስ ቅዱስ ሀልውና እየተለማን መኖርና በድርጊታችን ሁሉ ጌታን ደስ ለማሰኘ ት እየፈለግን መኖር ማለት ነው። ይህም የኢየሱስን እመራር ለጭነት (ጌትነት) በየትኛውም የሕይወታችን አቅጣጫ እምኖ መቀበል ማለት ነው። ማንኛውም ክርስቲያን፤ እድሜ፣ ሥራ ወይም ጾታ ሳይወስነው ለክርስቶስ ሊኖር ይገባዋል።

ለክርስቶስ መኖር ወይም በክርስቶስ መኖር በሕግ በደንብ የሚተበተበን አይደለም። ከሥራ ሃላፊነቶች፤ ለቤታችን ካለብን ግዴታዎች ወይም ከቤተሰባችን ጋር ላለን ግንኙነት ከሰጠነው ጊዜ ጋር አይጋጭም። ወይም ደግሞ አግባብነት ላለውና ለጤናችን አስፈላጊ ለሆነው እረፍት ከመደብነው ጊዜ ጋር የሚጣረስ አይደለም። ለክርስቶስ እየኖርን ለሌሎች ለዎች ጥሩ ወዳጅ ወይም መልካም ጎረቤት መሆን እንችላለን። በቅጡ የያዝናቸው ማህበራዊ ግንኙነቶቻችንም መልካምና አስደሳች ይሆኑልናል።

ይሁን እንጂ ለክርስቶስ መኖር፤ "ጊዜ ማሣለፊያ" የተባሉ ዋጋቢስ ውይይቶችን ሀሜትንና ትችት የምንለነዝርባቸውን ጊዜያት በአጭር የሚቀጭ ነው። እንዲህ አይነቱ የአኗኗር ዘይቤ ለሌሎች በመፀለይ፣ ሌሎችን በመባረክና የታመሙትንና በእድሜ የገፉትን በመጠየቅ ሊተካ ይገባዋል። ከአንዱ ጉዳይ ወደሌላኛው የሚበር "ማኅበራዊ ቢራቢሮ" ከመሆን ይልቅ፤ አስፈላጊነት ያላቸውን ተቋሞች ለመርዳት ጊዜውን ወደሚሰጥ፣ ቤተክርስቲያንን

የሚጎበኙና አላማ ባለው መንገድ የክርስቶስን የማዳን ሥራ ወደሚተርክ ማንነት መለወጥ የግድ ነው::

በክርስቶስ መኖር ማለት፤ ትምህርታዊ ያልሆኑና መንፈሳዊ ሕይወታችንን የማያንጹ የቴሌቪዥን ፕሮግራሞችን ለመመልከት ሰዓታትን ከማባከን ወይም ጥቃቅን ጉዳዮችን ከመከታተል ይልቅ፤ መጽሀፍ ቅዱስ ማንበብን፣ ከክርስቶስ ጋር የፍቅር ህብረትን ለማድረግ፣ የምልጃ ጸሎት ለማካሄድ ቅድሚያ መስጠትን የሚጠይቅ ነው:: በክርስቶስ መኖር፤ በየትኛውም ዓይነት የሕይወታችን አቅጣጫዎች ሥነ ሥርዓት የተሞላ አኗኗርን ያመጣል፤ ለራሳችን የምንመድበውን ገንዘብ የአጠቃቀም ሁኔታ ይወስናል፤ ጊዜ የሚፈጁና ውጤት አልባ የሆኑ ልማዶቻችን ላይ መስተካከሎችን ያስከትላል::

ብዙዎቻችን፤ አስፈላጊነት በሌላቸውና ተራ በሆኑ ጉዳዮች ላይ ደቂቃዎችን ምናልባትም ሰዓታትን በከንቱ እናሳልፋለን፤ እነዚህ ነገሮች ደግሞ በሁለንተናዊ ደህንነታችንና በሕይወታችን ላይ አንዳች በጎ ነገር የማይጨምሩ ናቸው:: ከማይረባ እንቅስቃሴ የዋጀሃትን ሃያ ደቂቃ በፀሎት ላይ ብትዘራ፣ በክርስቶስ ኢየሱስ ስም መልካም ነገር ብታደርግባት፤ ምናልባትም ይህች የሃያ ደቂቃ ዘር በሚቀጥሉት ሃያ አመታት ውስጥ መልካምን ነገር የምታሳጭድህ ልትሆን ትችላለች:: ከዚህም በላይ ደግሞ በዘላለም ሕይወትህ ያልገመትካቸውን ሽልማቶች ከዘላለም እስከ ዘላለም ታመጣልህ ይሆናል:: ሃያ ደቂቃ አንዳንድ ጊዜ በዘላለም ሕይወት ታላቅ የሆነ ልዩነት ልታመጣ ትችላላች:: በጊዜ፣ በገንዘብና በተሰጥኦዎችን ላይ ግዴለሾች በመሆናችን ምንኛ ሞኞች ሆነናል!



በሌላ አገላለጽ፤ ለጌታ መኖር ማለት ለኢየሱስ መኖር፣ ለመንግስቱ መስፋት መኖር፣ ዘላለም ላይ ትኩረት በማድረግ መኖር ማለት ነው:: ይህም ማለት ማስተዋል በሞላበት የህይወት ምልልስ፣ በፀሎትና ሌሎችን በመርዳት መኖር ማለት ነው:: ይህም በተራው በተቻለ መጠን ሁሉ ሌሎችን ለመባረክ መፈለግን፣ የክርስቶስን መንግስት ለማስፋት አስፈላጊ የሆነውን ማንኛውንም የገንዘብ ዘር ለመዝራት መፈለግንና የተቸገሩ ሰዎችን ለመርዳት መፈለግን ያካተተ ነው:: ይህ ማለት ጊዜያችንን፣ ገንዘባችንንና ልዩ ተሰጥኦዎችንን በክርስቶስ ላይ ባለን እምነት በመንፈስ ቅዱስ ምሪት መዝራት ማለት ነው:: ይህ በጆን ዌስሌ አገላለጽ፤ "የቻልከውን ያህል ሰብስብ፤ የቻልከውንም ያህል አከማች፤ የቻልከውንም ያህል ስጥ":: እንግዲህ ይህ ነው ህይወትን ሌሎችን ለመጠበቅ የተሰጠች የሚያደርጋት::

እስኪ አሁን ደግሞ ራሳችንን በክርስቶስና በዘላለም ህይወት ላይ እንዴት መዝራት እንደምንችል ይረዱን ዘንድ፤ እግዚአብሔር እኛን የሚመዝንባቸውን መንገዶች እንመልከት:: ሕይወታችንን እግዚአብሔር የሚጠቀምባቸውን መለኪያዎች በመጠቀም ብንመዝን ዘላለማዊ ዋጋ ለማግኘት ይረዳናል:: ዛሬ እግዚአብሔር ሕይወታችንን የሚመዝንባቸው ነገሮች ላይ ሙሉ ትኩረት ማድረግ ከቻልን ደግመንና ደጋግመን ልናመሰግነው እንበቃለን::

## ሕይወት በከንቱ ልናባክናት የማትገባ አጭር ቅጽበት ነች

ከማለዳ እስከ ፀሀይ መጥለቅ ባለች አጭር ቅጽበት በሕይወት መድረክ ላይ አቆራርጠን እንጓዛለን:: መሠራት የሚገባቸውን አስፈላጊ ነገሮች በጨረፍታ እናያለን:: ማድረግ የሚገባንን ለማድረግና በለለጠንነበት መስክ ውጤታሞች ለመሆን አቅድን እንተልማለን:: ራዕያችን ተፈጽሞ ህልማችን እውነት ሆኖና ተሳክቶ ልናይ ተስፋን እንሰንቃለን:: ግን ግን የህይወትን አጭር መንገድ ጀምረው ገና በህይወታቸው እኩለ ቀን ቀኑ የመሸባቸው ስንቶች ናቸው? ሁኔታዎች በተመቻቸላቸው የህይወታቸው ደማቅ ሰዓት፣ ሥራቸውን፣ ልጆቻቸውን፣ ቤቶቻቸውንና ሚስቶቻቸውን ትተው የሞት እስረኞች ሆነው ስንቶች ሁሉን ትተው ነጉደዋል?

በሕይወታቸው ያቀዱት ህልም ሊሣካላቸው ትንሽ የቀረ ሲመስል፣ በዚህ ምድር ላይ ሰው ሙት እንጂ ህያው አለመሆኑን ድንገት ተረድተው፣ እቅዳቸውን የጣሉ ስንቶች ናቸው?

ረጅም ግብን አልመው፣ ሊጨብጡት በታላቅ ጉጉት ሆነው ሣሉ፣ የህይወታቸው ፀሀይ በመጥለቋ ምክንያት በአጭር የቀሩት ስንቶች ናቸው?

ከህይወት አንዷን ቀን አንኳን ማባከን አጭር ለሆነች ዕድሜ ትልቅ ኪሣራ ነው:: በህይወት ጎዳና



የምትጓዘው አንዴ ብቻ፤ የምትዘምረውም አንዷን የሕይወት ዝማሬ ብቻ ነው:: በዘመንህ ሁሉ ያለማቋረጥ ትዘራት ዘንድ የተለጠችህ አንዲት ሕይወት ብቻ ናት:: ልትጨርላት ባለች በዚህ እድሜህ የተቻለህን ለማድረግ ከቶውንም ቸል አትበል::

ዘመኖችህ ምናልባትም እየባከኑ ይሆናሉና፤ የእግዚአብሔርን ምሪት ልትጠይቅ ይገባሃል፤ እቅዶችህን ወደፊቱ በማቅረብ የሚያስከፍሉትን ዋጋ ሁሉ ልትቆጥር ያስፈልግሃል:: እግዚአብሔር የእርሱ የሆነውን ፍቃድ እንድትመርጥና ሥራውንም ለመሥራት ፈጥነህ እንድትታጠቅ ይረዳሃል:: የአጭሯ ሕይወትህ ቀናት እንዲባክኑ አትፍቀድ፤ ሕይወት በከንቱ ልታሣልፋት የማይገባ፤ የምታሣሣና አጭር ናት::

ዊስሌይ ዱዌል

## 4

# እጆች የሚመዝን አምላክ

እርግጥ ነው፤ እግዚአብሔር የሚመዝን አምላክ ነው። ይህ በቃሉ ውስጥ በተደጋጋሚ ተገልጧል። እርሱ አስቀድሞ ላሉት ዘመናት ሁሉ የሚያቅድና እጅግ ጥቃቅን የተባሉትን ነገሮች እንኳን መዝግቦ የሚያስቀምጥ ነው።

እግዚአብሔር ነገሮችን የሚቆጥር አምላክ ነው። "እግዚአብሔር የከዋክብትን ብዛት ይቆጥራል፤ ሁሉንም በየስማቸው ይጠራቸዋል" (መዝ 147፥4)። "የእናንተ የራሳችሁ ጠጉር እንኳን ተቆጥሯል" (ማቴ 10፥30)። የእስራኤልን ልጆች ቁጥር በሚመለከት እግዚአብሔር ለሙሴ ተጨማሪ ትእዛዝ ሰጥቶት ነበር። የመገናኛው ድንኳን በተሠራበት ጊዜም ሙሴ ትክክለኛውን ልኬት እንዲጠቀም እግዚአብሔር አዞታል። በራዕይ መጽሐፍ ውስጥ እንደምንመለከተውም የአዲሲቱ ኢየሩሳሌም ልኬት በትክክል ተመዝግቧል።

እግዚአብሔር በልኬት ስርዓቱ ፍጹም የሆነ አምላክ ባይሆን ኖሮ፤ የዚህ ጽንፈ ዓለም ፈጣሪ ሊሆን ባልቻለም ነበር። ብዙውን ጊዜ አስትሮኖሚ የተሰኘው የስነ ከዋክብት ምርምር ሣይንስ እንደ ሂሳብ አንድ ዘርፍ ተደርጎ ይወሰዳል፤ የዚህ ምክንያት ደግሞ ይህ የጥናት ዘርፍ በማያቋርጥ መልኩ ከፍ ካለና ፍጹማዊ በሆነ የልኬት ሂሳብ ላይ የተመሠረተ በመሆኑ ነው። ሣይንቲስቶችም በፍጥረት ረቂቅነት ተደንቀው እግዚአብሔር የሂሳብ ሊቅ መሆን አለበት ያሉበት ጊዜ ነበር። በእርግጥም ደግሞ ነው። እርሱ እኮ የሂሳብ



ፈጣሪውም ነው። ማንም ሰው ቢሆን የእግዚአብሔርን እጅግ ረቂቅና ፍጹም ትክክለኛ ከሆነ የሂሳብ ስልት ሊመጣጠን (ሊወዳደር) አይችልም። ስለዚህም ነው የሰዓት አቆጣጠራችንን ሥርዓት ከከዋክብት እንቅስቃሴ ጋር አጣቅሰን ለማስተካከል የምንችለው።

ነገር ግን እግዚአብሔር ከሂሳብ ሊቅም በላይ ነው። በመሆኑም አግዚአብሔር ሁሉን የሚያውቅ አምላክ መሆኑና የእርሱ መላእክትም ደግሞ ሰዎችን ሁሉ የሚመለከቱና በፍጥረተ ዓለም ሁሉ ላይ የሚከናወነውን እያንዳንዱን ነገር ማወቃቸው እጅግም አያስደንቀንም። ያስተውላሉ፤ ይረዳሉ እናም ሁሉን ነገር መዝግበው ይይዛሉ።

ዳዊት እንዲህ ሲል ጽፏል፤ "አቤቱ መረመርኸኝ (መመርመር የሚለው ቃል በዕብራይስጡ ቋንቋ ጥንቃቄ የተሞላበትን ፍተሻ፣ ምርምራና ፍሰጋ እንዲሁም ዝርዝር ነገሮችን አገላብጦ መመልከትን የሚያካትት ነው) አወቅኸኝም። አንተ መቀመጤንና መነሣቴን አወቅህ፤ አሣቤን ሁሉ ከሩቅ አስተዋልክ … መንገዶቼን ሁሉ ቀድመህ አወቅህ፤ የአመጻ ቃል በአንደበቴ እንደ ሌለ። አቤቱ አንተ የቀድሞውንና የኋላውን አወቅህ" (መዝ 139፥1-4)።

እርግጥ ነው፤ በሰማይም ሆነ በምድር እንዲህ ያለውን ዝርዝር ዘገባ የእግዚአብሔርን ያህል ሊያውቅ የሚችል አንድ እንኳን የለም። እስከአሁን ድረስ በምድር ላይ ስለኖሩት ሰዎች ዝርዝር ዘገባ በእግዚአብሔር ዘንድ ይገኛል። ምድርን ሁሉ ለሚፈርዳት ለእግዚአብሐር እንዲህ ዓይነቱ ዘገባ እጅግ ያስፈልገዋል (ዘፍ 18፥25)። በእኛ ላይ የመጨረሻውን ፍርድ ለመስጠት ከእግዚአብሔር በቀር ማንም ብቃት የለውም። የአስተሳሰባችንን፣

የመሻታችን፣ የችግሮቻችን፣ የልዩ ልዩ ልምምዶቻችን፣ የምርጫዎቻችን፣ የፍርሃቶቻችን፣ የተስፋዎቻችንና የፀሎቶቻችንን ታሪክ አጠቃልሎ የሚያውቅ እግዚአብሔር ብቻ ነው። በማንም ላይ ጽድቅ የተሞላበትን ትክክለኛ ፍርድ ከመስጠቱ በፊት ሁሉን አቀፍ በሆነው እውቀቱ ፍጹም መሆን አለበት።

ሀጢያተኛ ለሆነ ሰው ይህ አስደንጋጭ ሀሳብ ነው። እግዚአብሔር እያንዳንዱን በሀጢያት የተሞላ አሳብ፣ መሻት፣ ሰበበ ነገር ያውቀዋል። ስለ ቁጣችን፣ ጠንካራ ስለሆነ ስጋዊ ፍላጎታችን፣ ስለጥላቻችንና ሁለገብ እንቅስቃሴዎቻችን ሁሉ ያውቃል። እግዚአብሔር የአንድ ሰው ንግግር፣ ድርጊትና ምላሴነት በሌሎች ላይ ያላደረውን ተከታታይ ተጽእኖ አጣርቶ ያውቃል። እግዚአብሔር ብቻ ሁሉን ያያል፣ ሁሉን ያውቃል፣ ሁሉን መዝግቦ ይይዛል በመሆኑም ሀጢያተኛው ለዘለዓለም የሚቆይበትን አጠቃላይና ተገቢ ቅጣት ለማስተላለፍ ይችላል።

ክርስቲያን ለሆነ ሰው፤ እንዲህ ያለ ሁሉን የሚያውቅ፣ ሁሉን የሚያይ፣ ሁሉን የሚገነዘብ፣ ሁሉን መዝግቦ የሚይዝና ለሁሉ ነገር ሽልማትን የሚሰጥ አምላክ ያለው መሆኑ እንደምን የሚያጽናና፣ የሚባርክና ታላቅ ተስፋ የሚሰጥ ነው! አምላካችን አባትም ፈራጅም ነው። በጽድቅ ሊሰጠን ያዘጋጀውን ሽልማት ሁሉ ስንቀበል በማየት ይደሰታል። የእርሱ ሽልማቶች በቂ በሆነ ምክንያት ላይ የተመሠረቱ ናቸው። በዚህም ላቢያ በሽልማቶቻችን ላይ ተጨማሪ ሽልማት የሚያመጡ የህይወታችንን ማናቸውንም እንቅስቃሴዎች ትኩረት ሰጥቶ የሚመለከተው በታላቅ ጉጉት ነው።

በደቡብ ህንድ የመጀመሪያው ሚሲዮናዊ በሆነው ሰው ቤት እኔና ባለቤቴ በእንግድነት ተጋብዘን በሄድንበት ጊዜ የዚያው አገር



ዜጋ የሆነ ሰው ሊቀበለን መጣ። በሚስዮናዊው ቤት ግድግዳ ላይ ክርስቲያናዊ እምነቱን የሚገልጽ አንድ ጥቅስ እንዲህ ይላል፦

እግዚአብሔር ያያል

እግዚአብሔር ይሰማል

እግዚአብሔር ያውቃል

በመጀመሪያ እንዳየሁት፣ "እንዲህ ያለው ግልጽ የሆነ እውነታ ለምን እንደ እምነት መግለጫ ሆኖ ሊቀመጥ ቻለ?" ስል ራሴን ጠየቅኩ። ፈጥኜ ግን ይህ እውነት በህንድ ውስጥ ለውጥ አምጭ እንደሆነ ተገነዘብኩ።

ይህ ታላቅ ሰው ሊቀበለን ወደ ሳሎኑ ሊወርድ፣ ተቀመጠና እነኛን ቃላት ተመለከታቸው። ከዚያም፣ "እግዚአብሔር ያያል፣ እግዚአብሔር ይሰማል፤ እግዚአብሔር ያውቃል!" በማለት በመደነቅ ተናገረ። ታውቃላችሁ ይህ ሰው ከዚያ በቀደመው ዘመኑ ማየት፣ መስማትና ሁሉን ማወቅ የሚችል አምላክ እንዳለ በጭራሽ አያውቅም ነበር።

እግዚአብሔር እያንዳንዱን ሀሳብ፣ መሻት፣ ቃልና ተግባር ማወቁ እንዴት ድንቅ እንደሆነ ተገንዝበሃልን? "ሳይጠሩኝ እመልስላቸዋለሁ፤ ገናም ሲናገሩ እሰማለሁ" (ኢሳ 65፥24) በማለት እግዚአብሔር ቃል የገባልን ለዚህ ነው። ለዳንኤልም ይህ እውነት ነበር፤ "እኔም ገና ስናገርና ስፀልይ . . . ገናም በፀሎት ስናገር የእግዚአብሔር መልአክ መጣ" (ዳን 9፥20-21)። ዳንኤል ገና ፀሎቱን ከመጨረሱ በፊት መልአኩ ገብርኤል የፀሎቱን መልስ ይዞ መጥቶ ነበር።

እግዚአብሔር ፀሎትህን እንደሚሰማና እንደሚያውቅ፣ የተቀደሰ ሃሳብህን እንደሚወደው፤ በጊዜህ፣ በጉብዝናህ ወይም በልዩ ተሰጥኦህ ስለ ክርስቶስ ኢየሱስ ብለህ የምታደርገውን ማንኛውንም ድርጊት ከማወቁ በላይ አንድ አስደናቂ ነገር ቢኖር፤ ኢየሱስ ስለእያንዳንዱ እንቅስቃሴህ ዝርዝር ጉዳይ የያዘ ዘገባ በመንግስተ ስማይ ያለው መሆኑ ነው፡፡ ኢየሱስ ስለእያንዳንዱ ፍቅር የተሞላበት መሻትህ፣ ስለ ፀሎትህ፣ አስበህ ስላደረከው ፍቅር የተሞላበት ድርጊትህ፣ ንግግርህና ተግባርህ ሁሉ ሊሸልምህ እቅድ አለው፡፡ ማንም ልትሆን ትችላለህ፤ ሽማግሌ ወይም ወጣት፤ በግል ቤትህ ውስጥ የምትኖር ወይም ተከራይ፤ ለመንግስተ ሰማይ ሽልማት ራስህን ልታዘጋጅ ትችላለህ፡፡ ስለ አንተ እየተዘገበ ያለው ነገር ምን እንደሆነ ተገንዝበሃልን?

ፍለጋ በሌለው የእግዚአብሔር እውቀት በተጨማሪ መላእክቱ የሚሰበስቡት መረጃና የአዘጋገብ ሥርዓቱ ሲታከልበት እግዚአብሔር፤ ያስማቋረጥ መረጃን መቀበልና ያለማቋረጥ ፍላጎትህን መመለስ ይችላል፡፡ በተጨማሪም እነዚህን ሀሣቦቻችንና ድርጊቶቻችንን ሁሉ ካካተቱ ብዛት ያላቸው ዘገባዎች መካከል በዘላለም ህይወት ሽልማታችን አንዳቸውም ቸል ተብለው የሚታለፉ አይደሉም፡፡

እግዚአብሔር ያለ አንዳች ማቋረጥ ይመለከታል፣ ያውቃል፣ ይገመግማል፣ ይመዝናል፣ እናም ይረዳል፡፡ የተሰበሰቡት መረጃዎች ዘገባ ፍጹም ትክክልና ወቅታዊ ይሆን ዘንድ መላዕክቱ ሁልጊዜ ያለ አረፍት ተግተው ይሠራሉ፡፡ ይሁንና እግዚአብሔር ያለማቋረጥ መረጃዎችን የሚያደራጀው፣ የሚገመግመው፣ የሚዘግበው እናም መረጃዎቹ በጥቅም ላይ እንዲውሉ የሚያመቻቸውና ወቅታዊ



እንዲሆኑ የሚያደርገው እንዴት ነው? መቼስ መንግስተ ሰማይ የኮምፒዩተር ሥርዓት እንደማያስፈልገው የታወቀ ነው፡፡ እግዚአብሔር ሰዎች እስከ አሁን ድረስ ሊያውቁትና ሊፈጥሩትም ከቻሉት የላቀና እጅግ ከፍ ያለ ፍለጋው የማይደረስበት መንገድ አለው፡፡

አዎ፤ እግዚአብሔር ያያል፣ ይመዝናል እናም ሁሉን ያውቃል፡፡ እግዚአብሔር የአንተንና የእኔን ህይወት የሚመዝንበት ሥርዓት፣ ፍለጋው ሊደረስበት በማይችል መልኩ ከማንኛውም ሰው ሰራሽ ከሆነ የምዘና ሥርዓትና ግምገማ ይልቅ የበለጠ የተሟላና ፍጹም የሆነ ነው፡፡

ይህ ሁሉ ፍቅርን በተሞላው በእግዚአብሔር ልብ ግንዛቤን የያዘ ነው፡፡ እግዚአብሔር የተዘጋጀልህን አስደናቂ ሽልማት የምትቀበልበትን ቀን በጉጉት ይጠብቃል፡፡

እግዚአብሔር ምን እንደሚመዝን፣ በዚህ ምዘናው በእርሱ ዘንድ ጠቃሚ የሆነው ነገር ምን እንደሆነ፤ ይህንን አስደናቂ ሽልማት ሊሰጠን ያቀደው በምን ሁኔታዎች ላይ ተመስርቶ እንደሆነ መገንዘብ ያስፈልገናል፡፡ የዚህ መጽሐፍ አላማም ይሄው ነው፡፡ እግዚአብሔር ሕይወትህን የሚገመግምባቸውን አስራ ስምንት ሁኔታዎች ይዘረዝራል፡፡ ስለነዚህ እግዚአብሔር ህይጠትህን ስለሚመዝንባቸው ነጥቦች ለአንድ ቀን ያህል እንኳን ያለ እውቀት እንዳትሆን ወይም ቸል እንዳትላቸው ያስፈልጋል፡፡ ህይወትህን በእግዚአብሔር ሚዛን ደረጃ መዝን! የተዘጋጀልህን ሽልማት አትጣለው!

## ጌታ ሆይ! ለእግዚአብሔር ቀድሰን

ጌታ ሆይ፤ ዛሬ ወደ ቤተክርስቲያንህ መጥተህ ለእግዚአብሔር ትቀድሰን ዘንድ እንፀልያለን፡፡ ለዚህ ዘመን ብቁ ሰዎች እንድንሆን፤ የሃይልህም መገለጫዎች እንድንሆን አድርግ፡፡ መሆን የሚገባንን ያህል መሆን ችለን መላው ህልውናህ በእኛ እንዲታይ ዘንድ እብቃን፡፡

ጌታ ሆይ፤ እባክህን እጆችህን ዳግም በላያችን ጫን፤ መልካም ሰዎች መሆን እንድንችል ቀባን፡፡ በሙላትህ ሁሉ ሙላን፤ ልባችንንም አቀጣጥለው፤ ለስምህም ክብር አድርገን፡፡ አንፃን በመንፈስህም ሙላን፤ ያኔ ፈቃድህን ልናደርግ ብቃትን እናገኛለን፡፡

ጌታ ሆይ፤ የፍላጎታችንን ያህል ከፍ አድርገን፤ በእያንዳንዷ ቃልህና ባሣየኸው ድርጊት ቀባን፡፡ በእያንዳንዷ ቅጽበት ከትእዛዝህ ሥር እንድንውል፣ እጆችህም እንዲመሩን ፍቀድ፡፡ በእያንዳንዷ ሰዓት አዘጋጀን፣ ተጠቀምብን፡፡ በመንፈስህና በሃይልህም አትመን፡፡

ጌታ ሆይ፤ ፈጽመህ ለእግዚአብሔር ቀድሰን፤ ፈጣን በሆነ ጉብኝትህም ተገናኘን፡፡ በምንም ላይ ለመተማመን እንችልም፤ አንተው የቅድስናህን ሃይል ስጠን፡፡ ለዘላለም ህይወት፣ እውነት ላለበትና እጅግ ለላቀው ነገር በእያንዳንዷ ቅጽበት ዘራችንን እንድንዘራ አንተው እግዘን፡፡

ዊስሌይ ዱዌል



# 5

## ሕይወትህን በፍቅርህ መዝነው

በሕይወትህ ውስጥ ለእግዚአብሔር የፍቅርህን ያህል ዋጋ የሚሰጠው ሌላ ጠቃሚ ነገር የለም፡፡ አንተ ማለት የምታፈቅረውን ያንን ነገር ማለት ነህ፡፡ አንተ የምትወደውን ነገር ያህል ትልቅ ነህ፤ ከእርሱ በላይ ግን ትልቅ አይደለህም፡፡ ሰይጣን፣ ፍቅርህ በእግዚአብሔር ዘንደ እጅግ ጠቃሚ የሆነ ነገር መሆኑን እንድትዘነጋው ይፈልጋል፡፡ ከሰው ዘር መነሻ ዘመን ጀምሮ እግዚአብሔር ፍቅርን ሊያስተምረን ሞክሯል፡፡

በኤድን ገነት ከአዳምና ከሄዋን ጋር የተመላለሰውና የተነጋገረው ጀሆቫ-ኤሎሂም፤ በቅድመ ተሰግኦ የነበረው ኢየሱስ፣ አማኑኤል (እግዚአብሔር ከእኛ ጋር) እንጂ ሌላ አልነበረም፡፡ ወደ እነርሱ የመጣው ለምን ነበር? እጅግ ይወዳቸው ስለነበር ነው፡፡ ለእርሱ የነበራቸው ፍቅርና ከእርሱም ጋር ያላቸው ህብረት እንዲያድግ ነው፡፡ እግዚአብሔር ፍቅር ነው፤ ዘላለማዊ ፍቅር ነው (1ዮሐ 4፥8፤16)፡፡

ከሁሉም በላይ እግዚአብሔር ከእኛ የሚፈልገው ምንድን ነው? ፍቅራችንን ነው፡፡ ሙሴ ከመሞቱ በፊት፤ እግዚአብሔር የተናገራቸውን ታላላቅ ነገሮች ለእስራኤል ልጆች በክለሳ መልክ ሲገልጽላቸው እስርቱን ትእዛዘ-ቃላት እንደገና ከነገራቸው በኋላ፤ እግዚአብሔር ምን እንደተናገረው ተረከላቸው፤ "... እንዲፈሩኝ ሁልጊዜም ትእዛዜን ሁሉ እንዲጠብቁ እንዲህ ያለ ልብ ምነው በሆነላቸው" (ዘዳ 5፥29)፡፡ በመጨረሻም ሙሴ እንዲህ ሲል

ደመደመ፤ "እስራኤል ሆይ፥ ስማ፤ አምላካችን እግዚአብሔር አንድ እግዚአብሔር ነው፤ አንተም አምላክህን እግዚአብሔርን በፍጹም ልብህ፣ በፍጹም ነፍስህ፣ በፍጹምም ሃይልህ ውደድ" (ዘዳ 6፥4-5)።

አይሁዳውያን ለብዙ መቶ አመታት በመቅደስ አምልኳቸውና በምኩራቦቻቸው፣ በየቤታቸውም በቀን ሁለት ጊዜ ጠዋትና ማታ ቁጥር አራትን ደጋግመው ያውጁታል። ብዙውን ጊዜ ግን ከዚህ ጥቅስ ጋር አብሮ የሚሄደውን ቁጥር አምስትን ግን ዘለውት ያልፉት። እግዚአብሔርን መውደድ እንደሚገባ የሚያዘውን ጥቅስም በየቀኑ ሁለት ጊዜ ሊደግሙት ይገባ ነበር። በቤታቸው ተቀምጠው ከቤተሰቦቻቸው ጋር በሚነጋገሩበት ጊዜ፣ በጎዳናው በሚመላለሱበት ጊዜ፣ በምሽት ወደ መኝታቸው በሚሄዱበት ጊዜና ማለዳ ከእንቅልፋቸው በተነሱ ጊዜ ሁሉ ደግመው ደጋግመው ለልጆቻቸው መንገር ነበረባቸው (ዘዳ 6፥5-9)። በሙሉ ልባቸው፣ በሙሉ ነፍሳቸውና በሙሉ ሃይላቸው እግዚአብሔርን ይወዱ ዘንድ ራሳቸውን ደጋግመው ማስታወስ ያስፈልጋቸዋል።

ኢየሱስ ክርስቶስ በአዲስ ኪዳን ለዚህ ጉዳይ አጽንኦት ሰጥቶት ነበር። ከህግ ትልቁ የትኛው እንደሆነ በተጠየቀ ጊዜ፤ መልስ የሰጠው ከሁሉቱም ከቁጥር አራትና አምስት በመጥቀስ ነው። እግዚአብሔር አንድ እንደሆነ ማመን ብቻውን በቂ አይደለም። እጅግ ከፍ ባለ ፍቅር ልንወደው ይገባል። በዚህም ላይ በመጨመር ሁለተኛው ትእዛዝ ባልንጀራችንን እንደራሳችን መውደድ መሆኑን በመናገር የቁጥር አምስትን አስፈላጊነት አጽንቶታል (ማር 12፥29-31)። ይህ የብሉይ ኪዳንም ይሁን የአዲስ ኪዳን ሃይማኖቶች እምብርት ነው። እግዚአብሔርን እጅግ ከፍ ባለ ፍቅር ውደድ፤ ባልንጀራህንም እንደ ራስህ አድርገህ ውደድ።



ለእግዚአብሔር ያለህን ፍቅር መዝን

እግዚአብሔር ሕይወታችንን የሚመዝነው ለእርሱ ባለን ፍቅር ነው። በእግዚአብሔር እይታ የማንኛውም ሰው ህይወት ታላቅ የሚሆነው፤ እግዚአብሔርን ከፍ ባለ ሁኔታ በመውደዱ ነው። ብዙውን ጊዜ ህፃናት የአዋቂ ሰዎችን ያህል ወይም ከዚያ በላይ መውደድ ይችላሉ። ይህ እድሜን፣ ጾታን፣ የሀብት ሁኔታን፣ ትምህርትን ወይም ስልጣንን የሚመለከት ነገር አይደለም። አንዲት ትሁት የሆነች መበለት፣ ድሃ የሆነ ተራ ሰው፣ በሁሉም ሰው የተረሳ አንድ ክርስቲያን፤ ልክ በቤተ ክርስቲያን ታዋቂ የሆነውን መሪ ያህል እግዚአብሔርን በጥልቀት ሊወዱ ይችላሉ። እግዚአብሔር ፍቅር ቀዳሚ ነገርህ እንዲሆን ይፈልጋል። የመጀመሪያውን ፍቅርህን ስትተው ደግሞ እርሱ እጅግ ያዝናል።

ሄኖክ ታላቅ የሆነው ለእግዚአብሔር የነበረው ፍቅር ትልቅ ስለሆነ ነው። ዳዊትን እግዚአብሔር እንደልቤ ያለው ሰው ነበር (ሐዋ 13፥22)፤ ምክንያቱም እግዚአብሔርን የሚፈልግ ልብ የነበረውና ከምንም ነገር በላይ ከእግዚአብሔር ጋር መሆን በእርሱ መገኘት ውስጥ መኖርን የሚናፍቅ ሰው ነበር። የማርያም ታላቅነት የተመሠረተው በ ፍቅሯ ታላቅነት ላይ ነው። ዮሐንስ ይበልጥ ተወዳጅ የሆነው ታላቅ በሆነው ፍቅሩ ምክንያት ነው። የክሌርቫክሱ የስነመለኮት ሰውና ባለቅኔ የነበረው በርናርድ እንዲህ አለ፤ "እግዚአብሔርን የምናውቀው እርሱን በወደድንበት መጠን ብቻ ነው።" ህጻን ወይም አዋቂ፤ ወንድ ወይም ሴት፤ አዲስ ጌታን የተቀበለ ወይም የበሰለ ክርስቲያን ሊሆን ይችላል፣ እግዚአብሔርን እጅግ አብዝቶ የሚወድ ያ ሰው በእግዚአብሔር መንግስት ከሁሉም ትልቅ የሆነው እርሱ ነው።

ለእርሱ ያለህን ፍቅር የምትመዝነው እንዴት ነው? የምትመዝነው በህይወትህ በሚከናወኑ ተግባራዊ ነገሮች ነው።

1. *በቀን ውስጥ ምን ያህል ጊዜ ፍቅር በተሞላበት ሁኔታ ኢየሱስን እንዳሰብከው በመቁጠር ሕይወትህንና ፍቅርህን መዝን።* እንዲህ ሲባል አንድ ሁለት እያልክ ቁጠር ማለት አይደለም። ነገር ግን በሰዓታት መካከል ባሉ ጊዜዎችህ በየቀኑ ደግመህ ደጋግመህ "ኢየሱስ ሆይ እወድሃለሁ" በማለት ፍቅርህን ግለጽ። ኢየሱስን የሚገባውን ያህል የምትወደው ከሆነ አእምሮህ ለቅጽበት ያህል እንኳን እረፍትን ባገኘ ጊዜ "ኢየሱስ ሆይ እወድሃለሁ!" የምትለውን ቃል መተንፈስህን ልማድ ታደርገዋለህ።

ከአንድ ክፍል ወደሌላው ስትሄድ፣ መኪናህን ስታሽከረክር፣ የትራፊክ መብራት ባስቆመህ ጊዜ ወይም የቅጽበት እፎይታ ባገኘህ ጊዜ ሁሉ ኢየሱስን እንደምትወደው ንገረው። ይህ እግባብነት ያለው ካልመሰለህ፤ ለኢየሱስ ያለህ ፍቅር የሚጠበቀውን ያህል ገና ጥልቀት የለውም ማለት ነው።

ማለዳ ከእንቅልፍህ ስትነቃ ከመጀመሪያዎቹ ሀሣቦችህ መካከል፤ በምሽት ስትተኛም በመጨረሻዎቹ ሀሳቦችህ መካከል፤ ኢየሱስን እንደምትወደው ንገረው። ምግብ ከመብላትህ በፊት በፀጥታ ልብህን ዝቅ ስታደርግ፤ የዕለቱን የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባብ ለማንበብ መጽሐፍ ቅዱስህን ስታነሳ፣ ወደ ቤተክርስቲያንህ በምትጓዝበት ጊዜ፣ የተፈጥሮን አንድ አስደናቂ ነገር በተመለከትክ ጊዜ፣ እጆችህን ለመታጠብ ወይም ፀጉርህን ለማበጠር ጥቂት የእፎይታ ጊዜ ስታገኝ፤ ደግመህ ደጋግመህ ኢየሱስን እንደምትወደው መናገርህን አትርሳ። በየዕለቱ እየደጋገምክ እነኝህን ነፃ ቅጽበቶች ፈልግ። ፊቱን በአምነት እየተመለከትክ ወደደው።



2. *ፍቅርህን፤ ቃሉን ለማንበብ ባለህ የርሃብ መጠን መዝነው።* የእግዚአብሔርን ቃል ለማንበብ ለይተህ በመደብከው ጊዜና መጽሐፉን በእጅህ ይዘህ ከእርሱ ጋር ብቻህን በሆንክ ሰዓት በማስማህ ደስታ ፍቅርህን መመዘን ትችላለህ። አብዝተህ በወደድከው መጠን፤ የእርሱ ቃል ለአንተ እጅግ የከበረ ነገር ይሆናል። ፍቅርህን፤ የእግዚአብሔርን ቃል ለማንበብ ጊዜ ለማትረፍ ብለህ ያለማቋረጥ ተግተህ በሠራሃቸው ሥራዎች፣ ከዕለቱ የጋዜጣ ምንባብህ ዘልለሃቸው በሄድካቸው አምዶች እና ሳትከታተል በተውካቸው የቴሌቪዥን ፕሮግራሞች ልትለካው ትችላለህ።

3. *ለክርስቶስ ያለህን ፍቅር፣ እርሱን ለማስደሰት ብለህ በህይወትህ ባደረግሃቸው አንዳንድ የማስተካከያ እርምጃዎች መዝን።* ገንዘብህን የምትጠቀመው እንዴት ነው? የክርስቶስን መንግስት ለማስፋት አስተዋጽኦ ለማድረግ ስትል እንዴት ነው ቁጠባ የምታደርገው? ስለ ክርስቶስ ብለህ ራስህን በመካድህ እንዴት ነው ሃሴት የምታደርገው? እርሱን ለመውደድ ብለህ ለመዝናናት የተረፈህን ጊዜ እንዴት ነው የምትጠቀምበት? ስለ ክርስቶስ ካለህ ፍቅር የተነሳ ቅድሚያ ስለምትሰጣቸው ነገሮች አንዳንድ ማስተካከያዎችን ያደረግኸው እንዴት ነው?

4. *ስለ ክርስቶስ ፍቅር ብለህ ሌሎችን ለመባረክ የሞከርካቸው ትንንሽ መንገዶች ምንድን ናቸው? ምን ያህል ጊዜ ደጋገምህ።* "እግዚአብሔር ይባርክህ" ትላለህ? ስለ ክርስቶስ ፍቅር ብለህ ምን ያህል ጊዜ አስበህበት ለሌሎች ፈገግታን ታሳያለህ? ምን ያህል ጊዜስ ስለ ክርስቶስ ፍቅር ብለህ፤ በቤተክርስቲያን ውስጥ ገብተህ በተቀመጥክ ጊዜ፣ በጎዳናው ላይ መኪናህን እያሽከረከርክ ስትጓዝ

ወይም አስቤዛ ስትሸምት ስትመላለስ በፊትህ ላይ ያለውን ፈገግታ ጠብቀህ ትቆያለህ?

5. *ለክርስቶስ ያለህን ፍቅር ለማሣየት ዛሬ ምን ተጨማሪ ነገር ማድረግ ትችላለህ?* ከዚህ ቀደም ከነበረህ ይልቅ ፍቅርህ እውነተኛ ይሁን፤ የበለጠ ተግባራዊ፣ በበለጠ ሁኔታ ደስታ የተሞላውና ይበልጥ ቀጣይነት ያለው ይሁን:: ታላቅ የክርስቶስ አፍቃሪ ሁን::

## ለሌሎች ክርስቲያኖች ባለህ ፍቅር ሕይወትህን መዝን

ለሌሎች ክርስቲያኖች ባለህ ፍቅር እግዚአብሔር ፍቅርህን ይመዝናል:: እንዲያው ለስም ብቻ የሆነ ወይስ ህይወት ያለውና በልብህ ውስጥ የሚቃጠል ፍቅር አለ? በእርግጥ ተግባራዊ ነው? ሌሎቹን ልጆቹን ሳትወድ እግዚአብሔርን ልትወድ አትችልም:: በእውነተኛ መንገድ ሌሎች አማኞችን የማትወድ ከሆነ፤ እርሱን እንደማትወድ እግዚአብሔር ያውቃል::

“ወዳጆች ሆይ ፍቅር ከእግዚአብሔር ስለሆነ፤ የሚወደውም ሁሉ ከእግዚአብሔር ስለተወለደ እግዚአብሔርንም ስለሚያውቅ፤ እርስ በእርሳችን እንዋደድ:: ፍቅር የሌለው እግዚአብሔርን አያውቅም እግዚአብሔር ፍቅር ነውና:: . . . ወዳጆች ሆይ እግዚአብሔር እንዲህ አድርጎ ከወደደን እኛ ደግሞ እርስ በእርሳችን ልንዋደድ ይገባናል ... እርስ በርሳችን ብንዋደድ እግዚአብሔር በእኛ ይኖራል፤ ፍቅሩም በእኛ ፍጹም ሆኖአል::” (1ኛ ዮሐ 4፥7-8፤11-12):: “ማንም እግዚአብሔርን እወዳለሁ እያለ፤ ወንድሙን ቢጠላ ሃሰተኛ ነው:: ያየውን ወንድሙን የማይወድ ያላየውን እግዚአብሔርን እንዴት ሊወደው ይችላል? እግዚአብሔርን የሚወድ ወንድሙን ደግሞ እንዲወድ ይህች ትእዛዝ ከእርሱ አለችን” (1ዮሐ 4፥20-21)::



እግዚአብሔርን የምትወድ ከሆነ እግዚአብሔር ለሌሎች ያለውን ፍቅር ፈጥነህ ትገነዘባለህ:: ለሌሎች አማኞች ያለን ፍቅር ከእነርሱ ከሚለየን ነገር ይልቅ አልፎ የሚሄድና በላጭ ነው:: የትኛ ውንም የልዩነት አጥር ይሰብራል:: ሁሉንም አይነት መሰናክሎች ያቀልጣል:: በየትኛውም አይነት ተግባራዊ እንቅስቃሴና ስፍራ ተገልጦ ሊታይ ይችላል:: እውነትነት የሌለውን ልዩነትና ከዘር ጥላቻ፤ ከብሄረተኝነት፤ ከዘረኝነት ከኑሮ ሁኔታ፣ ከስልጣን፣ ከትምህርትና ከልማድ በላይ ዘሎ የሚሻገር ነው::

ፍቅር እውነታዊ ነው:: ልዩነቶችን ይገነዘባል፤ ለእነርሱም ቦታ ይሰጣል:: ይሁን እንጂ ከልዩነቶች በላይ አልፎ ይሄዳል:: ለሌሎች ክርስቲያኖች ያለህ ፍቅር ዐይኖችህንና ልብህንም የሚከፍት ነው:: በሌሎች ላይ በጭፍን መፍረድን፣ አለመግባባትንና ጥርጥርን ያስወግዳል:: ክርስቲያናዊ ፍቅር የተጎዳን ልብና ጥልቅ የሆነውን ቁስል እንኳን ይፈውሳል:: እርስ በእርስ መዋደድ ክርስቲያኖችን የሚያቀራርብና እርስ በእርስ የሚያስተሳስር ነው:: ክርስቲያኖችን አብዝተህ በወደድክ መጠን እግዚአብሔር አብዝቶ ፍቅሩን በአንተ ልብ ውስጥ ያፈስሣል:: ክርስቲያን አማኞችን አብዝተህ በልብህ በተቀበልክ ቁጥር፤ እግዚአብሔርም አብዝቶ አንተን ወደ ልቡ ያስጠጋሃል::

ሙሴ ታላቅ ሰው የነበረው ለእግዚአብሔር ህዝብ በነበረው ታላቅ ፍቅር ምክንያት ነው:: ተችተውታል፣ አልተቀበሉትምም ነበር፤ ይሁን እንጂ በዚህ ሁኔታቸውም ውስጥ ይወዳቸው ነበር:: ለእነርሱ ያለውን ፍቅር ጠብቆ ለመቆየትና በታማኝነቱም ፀንቶ ለመቆም ታላቅ ዋጋ ለመክፈል ፈቃደኛ ነበር:: ነህምያ፣ ዳንኤልና ሆሴዕ ታላላቆች የሆኑት ለእግዚአብሔር ህዝብ በነበራቸው ታላቅ

ፍቅር ምክንያት ነው። ራሳቸውን ከህዝቡ እንደ አንዱ ቆጥረው ነበርና፤ ስለ እነርሱ ያለቅሱ ነበር፤ በፀሎታቸው የህዝቡን ሀጢያት ራሳቸው እንደሰሩት አድርገው ይማልዱ ነበር።

ከላይ ባነበብነው የመጽሀፍ ቅዱስ ጥቅስ፤ የመልዕክቱ ፀሐፊ ዮሐንስ፣ በእግዚአብሔር እይታ እንድ ሰው ታላቅ የመሆኑ ጉዳይ ወንድሙን በመውደዱ ላይ የተመሠረተ እንደሆነ አሣይቶናል። በተጨማሪም ማንም ሰው ለሌሎች ታላቅ ፍቅር ከሌለው በስተቀር ለእግዚአብሔር ታላቅ ፍቅር ሊኖረው በጭራሽ እንደማይችል አሣይቶናል። ጳውሎስ ፍቅርን እያወዳደሰ በፃፈው ቅኔ (1ቆሮ 13) የተናገረው ስለዚህ የክርስቲያን ወንድሞችና እህቶች ፍቅር ነው። የጳውሎስ የራሱ ህይወትም ለዘመረለት ለዚህ የፍቅር ቅኔ ምሳሌ መሆን ይችላል። ቀንና ሌሊት ስለአማኞች ይፀልይ ነበር። ያለማቋረጥ ስለ እነርሱ ይኖር ነበር። ሕይወቱን ለእነርሱ ለማፍሰስም ዝግጁ ነበር።

ለክርስቲያን ወገኖችህና ኢየሱስ ለሞተላት ቤተክርስቲያን ባለህ ፍቅር፤ እንዴት እድርገህ ነው ፍቅርህን መመዘን የምትችለው?

1. *ፍቅርህን፤ በክርስቶስ ኢየሱስ ያሉ ክርስቲያን ወንድሞችህንና እህቶችህን በማሰብ ባለህ ደስታ መዝን።* አብዝተህ ታስባቸዋለህ? ትፀልይላቸዋለህስ? በደስታቸው ደስ መሰኘት ትችላለህ? ለሁሉም ክርስቲያን ወገኖችህ መቆርቆር ትችላለህ? በቤተክርስቲያን አገልግሎቶች ለመሣተፍና ከሌሎች አማኞች ጋር ለመቀላቀልስ ትናፍቃለህን?
2. *ፍቅርህን፤ የወንድሞችህንና የእህቶችህን ውድቀት፣ ስህተት፣ ድክመትና ጉድለት ችል ብሎ ለማለፍ ባለህ ፈቃድ መዝን።* ሰዎች በረሱህ፣ በናቁህና ችል ባሉህ ጊዜ የሰሩትን ስህተት ይቅርታ በማድረግ ጉዳዬ ብለህ ባለመያዝ ብቃትህ ፍቅርህን መዝነው። ፈጽመህ ይቅር ማለት ትችላለህ? እነርሱን ባገኘሃቸው ጊዜ የልብ መክበድና ጥርጥርስ አይሰማህም?
3. *ፍቅርህን፤ በክርስቲያን ወገኖችህ ላይ የሚሰነዘረውን ሀሜት፤ እርግጠኛ የሆነ ማስረጃ ሳይኖረውና ቢኖረውም እንኳን ያ መረጃ የግድ ለሌሎች መተላለፉ አስፈላጊ ሆኖ ካልተገኘ በስተቀር፤ ሀሜትን ተቀብሎ ለማስተላለፍ ፈቃደኛ ባለመሆንህ መዝን።* ከወገኖችህ መካከል አንዱ ሲሰናከል ወይም ሀጢያትን ሲያደርግ በእውነት ታዝናለህ? በዚህ ሁኔታ ውስጥ እያሉ እንኳን ትወዳቸዋለህ? ትጸልይላቸዋለህስ?
4. *ፍቅርህን፤ አማኝ ወገኖች እንዲባረኩ ጥረት በማድረግህ መዝን።* ሌሎችን ደስ ለማሰኘትና ለመባረክ ተጨማሪ ጥቂት ነገሮችን በማድረግህ በሚሰማህ ደስታ ፍቅርህን መዝን። እንዲያውም የሚቻልህ ቢሆን ደግነትና ፍቅር የተሞላበትን መልካም ሥራ የሠራላቸው ማን እንደሆነ እንዳያውቁም አድርግ።

ፍቅርን የተሞላ እንዲህ ዐይነቱ ሕይወት በእግዚአብሔር እይታ ያለ ምንም ጥርጥር ታላቅ ሕይወት ነው። ለእግዚአብሔር ያለህ ፍቅር ቀዳሚውን ስፍራ ሊይዝ ይገባዋል፤ ይሁን እንጂ ለእግዚአብሔር ህዝብ ያለህ ፍቅር ለእርሱ ካለህ ፍቅር ጋር የተሣሰረ ነው። ለሰዎች ያለህ ፍቅር እግዚአብሔርን እንደምታፈቅር ዋስትና አይሰጥም፤ ነገር ግን እግዚአብሔርን መውደድ ለሰዎች ፍቅር እንዲኖርህ ያደርጋል።

## ሳልዳኑት ባለህ ፍቅር፤ ፍቅርህን መዝን

እግዚአብሔር ያልዳኑትን ሰዎች እጅግ ከመውደዱ የተነሣ የቀኑን ብርሃንና የወቅቱንም ዝናብ፣ ጤንነትንና የረዥም እድሜን ባርኮት ለዳኑት እንደሰጠ ሁሉ ላልዳኑትም ደግሞ ሰጥቷል:: ልክ አንተን እንደወደደህ ሁሉ ፍሰጋ በሌለው ፍቅሩ ሁሉንም ሀጢያተኞች ይወዳል:: እውነት ነው፤ ሀያል የሆነ ፍቅሩንና ወዳጅነቱን ምላሽ ለማይሰጡ ለእነርሱ ሊገልጽላቸው አይችልም፤ ይሁን እንጂ ይወዳቸዋል፤ ይህንንም ያሣያቸዋል:: እርሱ ፍቅር በመሆኑ ብቻ እነርሱን በመባረክ ይደሰታል:: በዚህ ረገድ የአንተ ፍቅር ምን ያህል ርቀት ይጓዛል?

ሀጢያትን በግልጽና በግድ የለሽነት የሚለማመዱትን መውደድ እጅግ አስቸጋሪ ነገር ነውን? የሚያስቆጡንን፣ ችግር የሚፈጥሩብንንና የሚያንገላቱንን ለመውደድ የእግዚአብሔር ፀጋ ያስፈልገናል:: ፍቅር በማንገላታት፣ በማንቋሸሽና በስደትም ላይ አሸናፊ ነው:: ፍቅርህን ከክርስቶስ ኢየሱስ ፍቅር ጋር በማስተያየት ለካው:: ተስፋ በማይታይባቸው ሁኔታዎች ውስጥ በመጽናት ፍቅርህን ለካው:: ፍቅርህን በቀራኒዮ መስቀል ሚዛን ለካው::

ፍቅር፣ ማንኛውንም ቋንቋ፣ ሁሉንም መሰናክሎች፣ የትኛውንም ርቀት ተሻግሮ የሚሄድ ቋንቋ አለው:: ፍቅር ተስፋን፣ እምቅ ሀይልንና በእግዚአብሔር ፀጋ ሀጢያተኞች ምን ሊሆኑ እንደሚችሉ የሚያይበት አይን አለው:: ፍቅር ለማየትና ለመገንዘብ አይን አለው:: ከተናጋሪው የቁጣ ቃል ይልቅ የተናጋሪውን ልብ የሚያዳምጥበት ሰሚ ጆሮ አለው:: ፍቅር፤ ሰውጥን ለማምጣትና ተአምራዊ መንካት ለመንካት እጆች አሉት:: ሕይወትህን በፍቅርህ መዝነው!



1. ፍቅርህን! ላልዳኑት ሰዎች ድነት ባለህ ረሃብ መዝነው

ኢየሱስ ስለ ኢየሩሳሌም ይጨነቅና ያለቅስ ነበር (ሉቃ 13፥34):: በቤተሰብህ ውስጥ ላሉ ጌታን ለማይከተሉ ሰዎች ረሃብና ጥማት አለህ? በምትኖርበት ማህበረሰብና በሀገርህ ውስጥ ላሉትስ? እኔ በሀጢያት ስተሞላች አንዲት ትልቅ የአሜሪካ ከተማና በውስጧ ለሚኖሩ ጠጭዎች፣ ወንጀለኞችና የሀጢያት ባሪያዎች ለሆኑ ሰዎች፤ ቀንና ሌሊት የሚማልድና የሚያነባ የአንድ ወጣት ክርስቲያን የከበረ ትዝታ አለኝ:: ይህ ወጣት ከሚኖርበት ቤት ትይዩ የሆነች ክፍል ይገዬ ነበር:: እናም በእያንዳንዱ ምሽት ሲፀልይና ሲያለቅስ እሰማው ነበር:: በጥልቀት የምታነባላቸው፣ ለድነታቸውም ረሃብ የሚሰማህ ያልዳኑ ሰዎች የትኞቹ ናቸው?

ጳውሎስ ስላልዳኑት ወገኖቹ ድነት በፀለየ ጊዜ፤ በልቡ ታላቅ ሃዘንና የማያቋርጥ ጭንቀት እንዳለ በፍርሃት ገልጸ ነበር (ሮሜ 9፥1-3):: እንዲያው ከልምድህ ጳውሎስ የፃፈውን ይህን ነገር በተግባር ተሰማምጸኸው ታውቃለህ? በአካባቢህ ያሉ ሰዎች በሀጢያታቸው እየኖሩ ከነሀጢያታቸው ሲሞቱ ያለ ምንም የልብ ስብራት ይህንን እያየህ መኖር ችለሃልን? ገና ላልዳኑት ባለህ ፍቅር መንፈሳዊ ህይወትህን መዝነው:: አንተ ለምትኖርባት ዓለም ኢየሱስ ያለውን ሸክም ትሸከምለታለህ? ይህን የምታደርገው ከሆነ ወደ እግዚአብሔር ልብ የምታመጣው ደስታ ታላቅ ነው:: የአንተም ሽልማት እንዲሁ ታላቅ ይሆናል::

*2. ፍቅርህን፣ ያልዳኑ ሰዎች ድነትን ያገኙ ዘንድ በምታደርገው ጥረት መጠን መዝነው።*

አባታዊ የሆነው የእግዚአብሔር ልብ ለጠፉት ወንድ ወይም ሴት ልጆቹ ሁሉ ፍቅርን መስጠት ይፈልጋል። የሰው ልጅ ወደ ምድር የመጣው የጠፉትን ሲፈልግና ሲያድን ነው። መንፈስ ቅዱስ እነዚያን በአመጸኝነትና በጥላቻ ተሞልተው ሀጢያትን የሚያደርጉትን ጽኑ በሆነ ፍቅር ይፈልጋቸዋል። የጠፋው በግ ሲገኝ የሚችልበት ብቸኛው መንገድ የሚፈልገው አንድ ሰው ሲኖር ብቻ ነው። እግዚአብሔር ሀጢያተኞችን ወደ እርሱ ለማምጣት የጠፉትን በሚፈልግ ፍቅሩ ሁሉንም ርቀት ይጓዟል።

እንደ ክርስቲያን እግዚአብሔርን አብዝተህ በወደድክ መጠን የጠፉትን አብዝተህ ትወዳለህ። ልብህም በእግዚአብሔር የመዋጀት ፍቅር ይሞላል። የማይወደዱትን ለመውደድ፣ የቆሰሉትን ለማከም፣ የተቅበዘበዙትን ለመምራት፣ የወደቁትን ለማንሣት፣ የተሰበሩትን ለመጠገን፣ ረዳት ያጡትን ለመርዳት፣ በሀጢያት የታሰሩትን ነጻ ለማውጣት፣ መጽናናት ያቃታቸውን ለማጽናናት፣ ሀጢያተኞች ድነትን እንዲያገኙና በእግዚአብሔር ፍቅር እንዲሰወጡ ለማድረግ ወደ ፊት መራመድ ትጀምራለህ።

አንድን ሀጢያተኛ ለክርስቶስ ለመማረክ ዝግጅትህ ምን ያህል ነው? የወደቀውን ለማንሣት ዝቅ ለማለት ምን ያህል ፈቃደኛ ነህ? የክርስቶስን ፍቅር ያልዳኑ ሰዎች በእርግጠኝነት ያውቁ ዘንድ መክፈል የሚገባህን መራራ ዋጋ ለመክፈል ምን ያህል ዝግጁ ነህ? ሕይወትህን፣ የጠፉትን በሚፈልግ ፍቅርህ መዝነው። የማንኛውም የጠፋ ሰው ድነት ጉዳይ ስአንተ ዋጋ ያለው ነገር ነውን?



በምትችልበት ሁኔታ ውስጥ ስለ ክርስቶስ ስትል ያንን ሰው ልታድን ትገባለህን?

ፍቅር ለማሣየት ያደረግሃቸው ጥረቶች ሁሉ ተቀባይነት ሲያጡና ሲንኳሰሱ ፈጥነህ ትዝላለህን? ብዙውን ጊዜ እጅግ ተቃዋሚዎችና ልበ ጠንካራ የሆኑ ሰዎች ድነትን ካገኙ በኋላ ከሌሎች ክርስቲያኖች ይልቅ ጠንካሮች ሆነው የሚገኙ ናቸው። መንፈሳዊ ፍቅርህን፣ ተስፋ ሁሉ ፈጽሞ የጨለመ በሚመስልበት ሁኔታ ውስጥ በፍቅር ለመቀጠል ባለህ ፈቃደኝነት መዝነው።

ፍቅር ፈጽሞ ተስፋ አይቆርጥም። ፍቅር በማንም ተስፋ አይቆርጥም። የዓለም ዓቀፍ አ.ኤም.ኤስ መስራች የሆነው ቻርልስ ካውማን እንደዚያ ዐይነት ፍቅር ነበረው። ታላቅ ሚስዮናዊ ከመሆኑ በፊት ትልቅ ፍቅር ነበረው። በንግዱ ዓለም የተሳካለት የነበረው ይህ ሰው፣ የመጀመሪያ ተልዕኮው የስምሪት መስክ ያደረጋት "ትንሿ ሲኦል" ተብላ የምትጠራውን የችካጎ አካባቢ ነበር። እዚያ ያሉት ሰዎች ሌሎች ተስፋ የቆረጡባቸውና እጅግ ክፉ ሰዎች ቢሆኑም ይወዳቸው ነበር። በሌሊት ክስካራሞች፣ ከቁማርተኞች፣ በህይወታቸው ብዙ ነገር ደግመው ደጋግመው ሞክረው ካልተሳካላቸው ተስፋ የቆረጡ ሰዎች ጋር ይፀልያል። የካውማንስ ፍቅር ሌሎች ሰዎች ታማኞች መሆን ባልቻሉ ጊዜ የታመነ ነበር። አ.ኤም.ኤስ በተመሠረተባቸው የመጀመሪያ ዓመታት ውስጥ ፍቅር የተሞላውን ድጋፍ ያገኝ የነበረው ከእነዚህ በህይወት ፍልሚያ ተዘርረው ከወደቁ፣ በኋላ ግን ጌታን አግኝተው ከተለወጡ ሰዎች ነበር። እንደ ፍቅር ያለ ድል አድራጊ የለም። ሁሉ ነገር ሲወድቅ ፍቅር አሸናፊ ነው። ሕይወትህን በፍቅርህ መዝን!

3. ላልዳኑ ለሰዎች ያለህን ፍቅር ለእነርሱ ባለህ ምልጃ መዝነው:: ኢየሱስ ክርስቶስ ለሀጢያተኞች ያለው ፍቅር የተመዘነው፤ ሰዎች ድነትን እንዲያገኙ ባደረገው በጌቴሴማኒ ምልጃው ነው:: እንዲሁ ደግሞ በመስቀል ላይ ሆኖ ምህረት እንዲያገኙ በፀለየው ፀሎት ጭምር ነው:: ስላልዳኑ ሰዎች ያለህ ፍቅር እንዲያው ንድፈ ሃሳባዊ የሆነ ወይስ በጌቴሴማኒ እንደተገለጠው ፍቅር ያለ ነው? መንፈሳዊ ፍቅርህን በጌቴሴማኒ ፍቅር መዝነው::

የፀሎት መዝገብህን ስትመለከት፤ ለለጠፉት ላለህ ፍቅር የሚሰጠው ምን ምስክርነት አለ? በየዕለቱ የፀሎት ዝርዝርህ ውስጥ ስንት ያልዳኑ ሰዎች ስም አለ? በመዝገብህ ካሰፈርካቸው ውስጥ ስንት ያልዳኑ ሰዎች ስም አለ? በመዝገብህ ካሰፈርካቸው ውስጥ ለድነታቸው ርሃብ ያለህና ያለማቋረጥ የምትማልድላቸው ስንቶች ናቸው? በመዝገብህ ከተካተቱት ውስጥ ጾም ይዘህ የፀለይክላቸው አሉ? ፍቅርህ እውነተኛ የሆነ የምልጃ ፍቅር ነውን? ፍቅርህን ነፍስህ በምታደርገው ምልጃ መዝን::

ለጠፉት ሰዎች እውነተኛ የሆነ የፀሎት ሸክም አለህን? በሌሎች ሰዎች ህይወት ላይ ሀጢያት በሚያደርሰው አውዳሚ ተጽእኖ ሀዘን ይሰማሃልን? ሰዎችን ባሪያ የሚያደርግበት የኅጢአት ሀይል እየጨመረ መምጣቱን የሚያሳዩ ምልክቶች ባየህ ጊዜ ታዝናለህን? በህይወቱ ውድቀት ላጋጠመው ሀጢያተኛ ታዝናለህን? ፍቅርህን፤ ለጠፉት ሰዎች ባለህ የፀሎት ሸክም ጥልቀት መዝነው::

መንፈሳዊ ሕይወትህን በፍቅርህ መዝነው:: ለክርስቶስ ባለህ ጠንካራ፣ ደስታ በተሞላውና በሚቀጣጠል ፍቅርህ ለካው:: ሕይወትህን ለቤተክርስቲያንና ለክርስቲያን ወንድሞችህና እህቶችህ ባለህ ፍቅር መዝነው:: ይህ ማለት በጣት ለሚቆጠሩ ለተለዩ ጓደኞችህ ማለት ላይሆን በክርስቶስ ላሉ ለሁሉም ወንድሞችህና



እህቶችህ ማለት ነው:: መንፈሳዊ ሕይወትህን የጠፉትን ለመፈለግ ክርስቶስን በሚመስል መሻትህ መዝነው:: ችግሮች በማያቆሙት ፍቅርህና ለጠፉት በምታደርገው የጌቴሴሜኒ አይነት የምልጃ ፍቅር መዝነው:: የመንፈሳዊ ሕይወትህን መጠን በፍቅርህ መዝነው::

እግዚአብሔር ሕይወታችንን የሚመዝነው በፍቅር ነው:: ሁሉንም አይነት እውቀትና ችሎታ ኖሮን ፍቅር ግን ባይኖረን ምንም የለንም:: ምንም አይነት መስዋእትነት ብንከፍል ነገር ግን ለእግዚአብሔር፣ ለወንድሞችና ለእህቶቻችን እውነተኛ የሆነ የሚቀጣጠል ፍቅር ከሌለን ምንም ነገር የለንም:: እጅግ ብዙ ሰዎችን ብንወድ፤ የማንወዳቸው ሌሎች ሰዎች ቢኖሩ ግን ፍቅራችን ምንም ማለት አይደለም:: በቀራንዮ መስቀል ብርሃንና በዘላለም ህይወት ብርሃን ህይወትህ የሚመዘነው እንዴት ነው? ስለ አንተ፤ "እንዴት ይወደው እንደነበር እዩ" ይባል ይሆን? (ዮሐ 11፥36)

## ከእነዚህ የሚበልጠው ፍቅር ነው

ተራራን የሚያንቀሳቅስ እምነት በእውነት ትልቅ ነው፤ የማይናወጥ ተስፋም በእርግጥ ትልቅ ነው፡፡ በመንፈስ የተፈተነ የህይወት ፍሬም ትልቅ ነው፤ ከእነዚህ ሁሉ ግን የሚበልጠው ፍቅር ነው፡፡

እግዚአብሔር ታማኝነትን ከህይወትህ ራሱ ማየት ይፈልጋል፤ በእርሱ ላይ ብቻ የተደገፈ እምነትህን ማየትም ይሻል፤ አገልግሎትህም እርሱ የሚከብርበት እንዲሆን ይወዳል፡፡ ከዚህ ሁሉ ግን ከሕይወትህ አብልጦ የሚፈልገው ፍቅርን ነው፡፡

እግዚአብሔር አምነን እንቀበለው ዘንድ መንፈሳዊ እውነታዎችን አስቀምጦልናል፤ በደለኝነታችንን ተቀብለን ንስሀ የምንገባባቸውን ሁኔታዎች አስታውቆናል፡፡ ባህሪያችንንም በቅድስናችን ውስጥ ይፈትሸዋል፤ ከዚህ ሁሉ በላይ ግን ፍቅራችንን ማየት ይፈልጋል፡፡

የእግዚአብሔር መንፈስ ሆይ! በህዝብህ መካከል ውረድ፤ በታላላቆችና በታናናሾች ሁሉ ላይ በሙላትህ ተገሰጥ፡፡ እባክህ ና፤ በሁላችን ውስጥ በሙላትህ ኑር፤ ከዚህም በላይ ግን እባክህ ፍቅርን ስጠን!

ዊስሌይ ዱዌል



# 6
# ከእግዚአብሔር ጋር ባለህ ህብረት፤ ህይወትህን መዝን

እግዚአብሔር ህይወትህን የሚመዝነው እንዴት ነው? ባለፈው ምዕራፍ ውስጥ እግዚአብሔር ህይወታችንን በፍቅራችን እንዴት እንደሚመዝን ጠቅሰናል፡፡ ነገር ግን ሌሎች መመዘኛዎችም አሉ፡፡ አስኪ አሁን ደግሞ፤ ፍቅርህን ለክርስቶስ ኢየሱስ ስትገልጽ በሚኖርህ ግንኙነት ሕይወትህ እንዴት እንደምትመዘን እንመልከት፡፡

የማንም ሰው ህይወት ከፀሎቱ አይበልጥም፡፡ ማንም ሰው የሚያሳድረው ተጽእኖ ከፀሎቱ ይልቅ የሰፋ አይደለም፡፡ የማንም ሰው መንፈሳዊ ህይል ከጸሎቱ በላይ አይደሰም፡፡ ጸሎት ሁለት ዋነኛ ገጽታዎች አሉት፡፡ ግንኙነትና ምልጃ፡፡ ሁለቱም በእግዚአብሔር ይመዘናሉ፡፡ በዘላለም ውስጥ እጅግ ታላላቅ የሆኑ ህይወቶች የሚመዘኑት በኖሩበት ዘመን ልክ፣ በስልጣን ወይም በዝነኛነት አይደሰም፡፡ እንደነዚያ ያሉ ህይወቶች፤ ለእግዚአብሔር እጅግ የከበሩና ታላቅ የሚሆኑት በፀሎት በሚሆን የተቀደሰ ግንኙነትና ለሌሎች በሚደረግ የተቀደሰ ጠንካራ ምልጃ የሚገለጡ በመሆናቸው ነው፡፡

ሕይወትህን ከእግዚአብሔር ጋር ባለህ ግንኙነት መዝነው፡፡ እንደዚያ ያለ ህይወት በእግዚአብሔር ፊት እጅግ ታላቅ ነው፡፡ ይህ ማለት ደግሞ ለእግዚአብሔር እጅግ የከበረ ነው፡፡ እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር የቀረበ ህብረት ማድረግ ለምታውቅ ሕይወት ትልቅ ዋጋ ይሰጣታል፡፡ በእግዚአብሔር ዘንድ ያለህ ጠቃሚነት፤ በእጅህ በገባው ስልጣን ምክንያት ምን ያህል በሌሎች ላይ ተፅእኖ ማሳደር

በመቻልህ ወይም ከሰዎች በምትቀበለው የምስጋና ብዛት አይመዘንም።

በመስበኪያው ምስባክ ላይ በርቱእ እንደበታቸው በሺህ የሚቆጠሩትን መማረክ ከቻሉ ክብዙ ዝነኛ ተናጋሪዎች ይልቅ፤ የእልጋ ቁራኛ የሆኑ የተደበቁ ቅዱሳን ከእግዚአብሔር ጋር የበለጠ ወዳጅነትን ማድረጋቸው ምንም ጥርጥር የለውም። ወደ እግዚአብሔር ለመጠጋት ፈቃደኛ የሆነ ማንም ቢሆን፤ የእግዚአብሔር የቅርብ ወዳጅ መሆን ይችላል።

ነገር ግን ከእግዚአብሔር ጋር ግንኙነትን ለማድረግ ጊዜን የሚወስድ ማነው? ለእግዚአብሔር የሚሰጡትን አገልግሎት የበለጠ ፍጹም ለማድረግ ተጨማሪ ሰዓቶችን ከሚሠሩ ሰዎች ይልቅ፤ ከእግዚአብሔር ጋር ፍቅር የተሞላበትን ግንኙነት ለማድረግ ጊዜን መስጠት ጠቃሚ እንደሆነ በእውነት የሚያምኑ እነማን ናቸው? እነማንስ ኢየሱስን ለመውደድ ጊዜን መውሰድ ጠቃሚ እንደሆነ በእውነት ያምናሉ? ቤተሰቦቻችንን እንደምንወድ ለማሳየት ጊዜ እንሰጣቸዋለን። ወዳጅነታችንን ለማሳየት ከጓደኞቻችን ጋር ጊዜ እናሳልፋለን። ታዲያ ከእርሱ አንዳች ካልፈለግን በቀር፤ ለምንድን ነው አልፎ አልፎ ብቻ ወደ እግዚአብሔር የምንቀርበው? የፀሎታችንስ አብዛኛው ክፍል ጥያቄ ብቻ የሚሆነው ለምንድነው? በየዕለቱ ለኢየሱስ የሚገባውን የግል ፍቅራችንን ለማሣየት ለምን ቸልተኞች ሆንን?

እግዚአብሔርን አብልጠን በወደድነው መጠን፣ ከእርሱ ጋር በመሆናችን ይበልጥ ደስተኞች እንሆናለን። አብዝተን በወደድነው መጠን፣ ከእርሱ ጋር ብቻችንን መሆን የምንችልባቸውን መንገዶች በታላቅ ጉጉት እንፈልጋለን። ከእግዚአብሔር ይልቅ ብዙውን



ጊዜያችንን የምንሰጠው አንድ ሰው እንኳን ያለ እንደሆነ፤ በህይወታችን እግዚአብሔር ቀዳሚውን ሥፍራ ይዟል ማለት አንችልም። በታላቅ ጉጉት ሆነን ደስታችንን፣ ህሣባችንንና ዕለታዊ እንቅስቃሴዎቻችንን የምናካፍለው አንድ ሰው ቢኖር እንኳን ያ ሰው ከእግዚአብሔር ይልቅ በእኛ ህይወት የላቀውን ስፍራ ይዟል።

እግዚአብሔር አንተን ወደ ልጅነት ህብረት ያመጣህ ለአንተ የበለጠ ክብር ለመስጠት አይደለም፤ ይልቁንም ከእርሱ ጋር እጅግ የቀረበ ህብረት ማድረግ እንድትችል ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ አንተን የሙሽራይቱ አንድ አካል እንድትሆን መርጦሃል፤ እናም ፍቅሩንና መልካምነቱን የሚያሳይህ፣ ለእርሱ እጅግ አብልጠህ እንድትሠራ ሳይሆን ይልቁንም አንተን ፍቅር ወደ ተሞላበት የቅርብ ግንኙነት ለማምጣት ነው። የእርሱ እቅድ ብዙውን ጊዜህን በአገልግሎት ላይ እንድታውለው ሳይሆን ብዙውን ጊዜህን ከእርሱ ጋር ላለህ ግንኙነት እንድታውለው ነው። ከበዛው መስዋእትህ ይልቅ እርሱ የሚሻው ለእርሱ ያለህን በፍቅር የተሞላ ህሣብህንና ቃልህን ነው። ኢየሱስ የማርታን ታማኝነትና በፍቅር የተሞላ አገልግሎቷን አድንቋል። ነገር ግን ወደ እርሱ አብልጣ የቀረበችው ማርያም ነበረች (ሉቃ 10፥38-42)።

የክርስቲያናዊ አምልኮ ቀዳማይ አላማ ስለ እግዚአብሔር እንዲነገረን አይደለም። ነገር ግን ከእርሱ ጋር ህብረት ለማድረግ ነው። በአዲስ ኪዳን የጌታ እራት ሥርዓት ተደጋግሞ የሚሰጥበት ብቸኛው ቀዳሚ አላማ፤ ያለማቋረጥ ወደ ጌታ ገበታ መጥተህ ቅርበት ያለው መንፈሳዊ ህብረት ከእርሱ ጋር ማድረግ እንድትችል ነው። በየቀኑ ቤትህን የሚጎበኝበት ቀዳሚ ዓላማውም የአንተን ማጉረምረም ወይም ጥያቄዎችህን እንኳን ለመስማት አይደለም።

አንተ ሳትጠይቀው በፊት የሚያስፈልግህን ያውቃል:: "በጌታ ደስ ይበልህ፤ የልብህንም መሻት ይሰጥሃል" (መዝ 37፥4):: በየዕለቱ በአንተ ዘንድ የመገኘቱ ቀዳሚ አላማም፤ ከእግሮቹ ሥር እንድትቀመጥና፣ እጅግ የቀረበ ወዳጅህ፣ የተወደደ መታመኛህ፣ ለማያዊ ሙሽራህም ታደርገው ዘንድ ነው::

እግዚአብሔር ፍቅር ነውና፤ ለውን የፈጠረበት ዋነኛው ምክንያት ህብረትን ፈልጐ ነበር:: እግዚአብሔር በኤድን ገነት ከአዳምና ከሄዋን ጋር በመጀመሪያ ያደረገው ግንኙነት ህብረት ነበር:: እግዚአብሔር ከሄኖክ ጋር የነበረው ግንኙነት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በአጭሩ ነው የተጠቀሰው:: በጥቂት ቃላት ነው:: ነገር ግን ሄኖክ ከእግዚአብሔር ጋር የነበረው ህብረት ያልተለመደ ዓይነት መሆን አለበት:: እግዚአብሔር ከአዳምና ከሄዋን ጋር ህብረት ማድረግን ጀምሮ ነበር፤ እነርሱ ግን በሙሉ ልባቸው ምላሽ አልሰጡትም:: መያዝ የሚገባቸውን ያህል አክብረው አልያዙትም::

ከእግዚአብሔር ጋር እውነተኛውን ህብረት ያደረገ የመጀመሪያው ሰው ሄኖክ ነበር:: መጽሐፍ ቅዱስ የነገረን ብቸኛው ነገር ለሦስት መቶ አመታት ያህል ሄኖክ አካሄዱን ከእግዚአብሔር ጋር እንዳደረገ ነው:: አም እግዚአብሔር በመጨረሻው እውነተኛ ህብረትና ወዳጅነትን አገኘ:: እስኪ አስበው፤ የሦስት መቶ አመታት የልብ ከልብ መቀራረብ! የሚያወሩት ምን ነበር? እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር የሚካፈለው ምን ነበር? በእርግጠኝነት ሄኖክ በታሪክ ውስጥ ካለፉት ሰዎች ሁሉ ይልቅ በእግዚአብሔር ፊት እጅግ ታላቁ ሰው ነው:: እግዚአብሔር በመካከላቸው የነበረውን ግንኙነት ልክ እንደምስጢራዊ ዘገባ አድርጎ እንደ ከበረ ሀብቱ በመቁጠር በሚስጥር አስቀምጦታል::



ክርስቶስ በስጋ በተገለጠ ጊዜ፣ ህብረት የሚያደርግባቸውን ቤቶች ይፈልግ ነበር:: ጴጥሮስን፣ ያዕቆብንና ዮሐንስን ከእርሱ ጋር ሲወስዳቸው የነበረውም ከእርሱ ጋር ቅርበትና ህብረት ስለነበራቸው ነው:: ከማርታ አገልግሎት ይልቅ የማርያምን ህብረት መርጧል:: ድነት የተሰጠንም ከእግዚአብሔር ጋር የነበረን ህብረት እንዲታደስ ነው:: እግዚአብሔር ወደ ዘላለማዊው ቤቱ የሚወስደን፣ ዘላለማዊ የሆነ ህብረት ከእርሱ ጋር እንድናደርግ አቅዶ ነው:: መንግስተ ሰማይ የእውነተኛ ህብረት ሥፍራ ናት::

ሕይወትህ እንዴት ናት? ሕይወትህ ለእግዚአብሔር ምን ያህል ጠቃሚ ናት? በየዕለቱ ለእግዚአብሔር የምታመጣው የተቀደሰ እርካታ ምንድነው? አገልግሎትህ ለእግዚአብሔር ጠቃሚ ነው፤ ነገር ግን ከእርሱ ጋር ያለህ ህብረት የበለጠ ጠቃሚ ነው:: ከእግዚአብሔር ጋር ከሚደረግ ልባዊ ህብረትን ተከትሎ ቀጥሎ የሚደረግ አገልግሎት ታላቅ የሆነ ሀይል አለው፤ በእግዚአብሔር ፊትም እጅግን ውጤታማ ነው::

እግዚአብሔር በታላቅ ጉጉት ሊያገለግሉት የሚፈልጉ ሺህ ሺዎችን በቀላሉ ማግኘት ይችላል:: ከእርሱ ጋር ህብረት ለማድረግ ታላቅ ረሃብ ያለውን ሰው የሚያገኘው ግን ከሺህ አንድ ብቻ ይመስላል:: ከእግዚአብሔር ጋር ህብረት ማድረግህ ብቸኛ አያደርግህም:: ከእግዚአብሔር ጋር ያለህ ህብረት ሥራ-ፈት ወይም ሌሎችን በጥቂቱ ብቻ የምትጠቅም ሰው አያደርግህም:: ይልቁንም የእግዚአብሔርን ህልውና እንድትሸከምና መላውን ሕይወትህ ለሌሎች የተቀደሰና ጣፋጭ መአዛ ያለው ባርከት ይሆን ዘንድ ብቃት ይሰጥሃል::

ከእግዚአብሔር ጋር ህብረትን የምታደርግበት ጊዜህ የባከነ አይደለም! ይልቁን በእግዚአብሔር ልብ ውስጥ እየዘራኸው ነው። በፍጥረተ ዓለሙ ሁሉ ላይ ህላዊ አምላክ ከሆነው ጋር እየዘራኸው ነው። በእውነት ከእግዚአብሔር ጋር ህብረት እያደረግህ ከሆነ፤ በምድር ላይ እጅግ እድለኞች ከሆኑት እንደ አንዱ የተቆጠርክ ነህ። በየዕለቱ በእውነት ከእግዚአብሔር ጋር ህብረት ለማድረግ ራስህን ከሰጠህ በዘላለም ሕይወት ከልዑላኑ አንዱ ትሆናለህ።

ከእግዚአብሔር ጋር ህብረትን ማድረግ የለመደ ልብ፤ ሣያውቀው የምልጃ ልብ ይሆናል። ለምን? ምክንያቱም ኅብረትህ ከኢየሱስ ጋር ነው፤ እርሱ ደግሞ ታላቁ ሊቀ ካህን (ማላጅ) ነው። ስለዚህ ከኢየሱስ ጋር ህብረት ስታደርግ፣ ቅዱስ የሆነውን የልቡን አሳብና ለመላው ዓለም ያለውን ረሃብ ያካፍልሃል። የጸሎት ጊዜህን በምልጃ ስትጀምር፣ አንዳንድ ጊዜ ከእግዚአብሐር ጋር በቅድስተ ቅዱሳን ውስጥ መሆንህን እስከትረዳ የሆነ ጊዜ ይወስድብህ ይሆናል። ነገር ግን ከእግዚአብሔር ጋር ያለህን ጊዜ ያለ ምንም ጥድፊያ፤ እጅግ በከበረ ህብረት ስትጀምረው ራስህን በመንግስተ ሰማይ በዙፋኑ ፊት ታገኘዋለህ። ከሱራፌልና ከመላእክታቱ ጋር ተባብረህ፤ አብን፣ ወልድንና መንፈስ ቅዱስን ስታመልክ፣ ስታመሰግን፣ ፍቅርንና አክብሮትን ስትሰጥ ራስህን ታገኘዋለህ።

ህብረት በምታደርግበት፤ ጊዜ እውነተኛ ግንኙነት በምታደርግበት ጊዜ፣ ህይወትህ በተቀደሰ መሠረት ላይ ይቆማል። ብዙውን ጊዜ ራስህን ታላቅ በሆነው በእግዚአብሔር ህልውና ውስጥ ታገኘዋለህ። በእውነትም በእግዚአብሔር ዘንድ የተወደድክ ትሆናለህ። ንጉሱ የወርቅ ዘንጉን ወደ አንተ ዘርግቶ "አንተ የእኔ ውድ፤ የምትሻውን ጠይቅ" ሲልህ ልታይ ትችላለህ።



ከተሃድሶ በፊት በነበሩት የመንፈሳዊ ጨለማ ዓመታት በፊት ማዳም ጉዮን የምትባል የፈረንሣይ ቤግነት የነበራት ልጂ የተራበ ካቶሊካዊት፤ ከጌታ ጋር በፍቅርና በእምነት መመላለስ ተለማምዳ ነበር። ታላቅ ስደት በተቀጣጠለበት ወቅት አስር ዓመት በእስር፣ እንደገና ደግሞ ሌላ ሰባት ዓመት ከሀገሯ ውጭ እንድትሰደድ ተደረገች። በዚያ ጊዜ ውስጥ እግዚአብሔር ከእርሷ ጋር በነበራት ህብረት ለእርሷ ታላላቅ የሆኑትን መንፈሳዊ እውነታዎችን አስተማራት። የተማረቻቸውን መንፈሳዊ ነገሮችም በጽሑፍ አቀረበቻቸው፣ እነዚያም ጽሑፎች ዛሬም ድረስ ታዋቂ ናቸው።

የኖረችው ህይወት ጣፋጭ ህብረት የነበረው ህይወት ነበር። ኢየሱስ የነፍሷ ውድ ነበር። "የእርሱ አሠራር እጅግ ሀያል፣ በጣም ጣፋጭና የተቀደሰ ነው። ይህም ሁሉ ሆኖ እገልፀው ዘንድ አቅም የለኝም። አ! እንደምን ሊተረክ የማይችል ህብረት ነው የተለማመድኩት።" "የእስር ቤቱ ድንጋዮች ልክ የሚያንጸባርቁ የከበሩ ድንጋዮች ሆነው ነበር የሚታዩኝ"።

የኢየሱስን ፍቅር የሚገልጹ ረጃጅም የሆኑ ጣፋጭ ግጥሞችና ቅኔዎች እንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ማብራሪያን ጨምሮ ስድሣ መጻሕፍትን ብትጽፍም፣ በማያቋርጥ የፀሎት ህብረት ለኢየሱስ ምስጋናንና ፍቅርን በማቅረብ ነው የኖረችው። ብዙዎችን በእምነት ወደሚገኝ ድነትና በመንፈስ ወደ ተሞላ የከበረ ህይወት መርታለች። የትኛውንም ስፍራ ብትጎበኝ፣ መንፈሳዊ መነቃቃት ይመጣል። ከእግዚአብሔር ጋር ያላትን ህብረት የምትገልጸውም "ሙሉ ቅድስና የተሞላ፣ ሰማያዊና ሊነገር የማይችል" በማለት ነው።

ወይዘሪት አልታ ጃኮብዝ፣ የደቡብ አፍሪካ የወጣት ሴቶች ክርስቲያናዊ ማህበር (ወሴክማ) አማካሪ፣ እ.ኤ.አ በ1938 በበልግ ወቅት ወደ ኮሪያ መጣች፡፡ አመጣጧ ወደ ጌታ እንዲመጡ ከረዳቻቸው ሰዎች መካከል አንዷ የሆነችውን ወይዘሪት ኢዮኒስ ማሪኢስን (በዚያን ጊዜ የአሰም ዓቀፍ ኦ.ኤም.ኤስ ሚስዮናዊት ነበረች) ለመጎብኘት ነበር፡፡ ወይዘሪት ጃኮብዝ በኔዘርላንድስ ተሃድሶን የተቀበለች፤ ከኢየሱስ ጋር አስደናቂ የሆነ ህብረት የነበራት ሴት ነች፡፡ ኢየሱስ ማለት ለእርሷ አብሯት እንደሚኖር ባልንጀራ ነው፡፡ ላገኘችው ለማንኛውም ሰው የምትናገረው ስለ ኢየሱስና ለእርሱ ስላላት ፍቅር ነው፡፡

ያላትን ትርፍ ጊዜዋን ሁሉ ከምትወደው ጌታዋ ጋር ህብረትን በማድረግ ታሳልፋለች፡፡ ብዙም ሳይቆይ አካሄዷን ከኢየሱስ ጋር ስለማድረጓ በሚሲዮናውያን መካከል ወሬ መሠራጨት ጀመረ፡፡ ወሬው የተሰራጨው በኦ.ኤም.ኤስ ብቻ ሳይሆን በሁሉም ቤተእምነቶች መካከል ነበር፡፡ በዚያን ጊዜ ሚስዮናውያኑ ሁሉ ለእረፍታቸው ዋጂንፓ በምትባል ኮረብታ ላይ ነበሩ፡፡ ከጸሎት ቀኖቻቸው በአንዱ፣ ጥልቀት ያለው መንፈሳዊ ሕይወትን በሚመለከት ከዕለታዊ የፀሎት ጉባኤያቸው መካከል አንዱን እንድትመራ ተጠየቀች፡፡

ለክርስቶስ ኢየሱስ ያላት የነደደ ፍቅር የሁሉንም ቤተእምነት ሚስዮናውያን ከእርሷ ጋር አብሮ ለማውራትና ለመጸለይ ጉጉት አሳድሮባቸው ነበር፡፡ የአንድ ሳምንት ጉባኤም እንድትመራ ተጠየቀች፡፡ በደረሰችበት ሥፍራ ሁሉ መንፈሳዊ መነቃቃት ይቀጣጠል ነበር፡፡ ፕርስቢተሪያኖች፣ ሜቶዲስቶችና የኦ.ኤም.ኤስ ሰዎችን ጨምሮ ብዙዎች በተልእኮ ስፍራዎቻቸው ላይ እንድትገኝ



ጋበዟት፡፡ በአገልግሎቷ ቢያንስ የ110 ሚስዮናውያን ሕይወት ተለወጠ፡፡ እኔ በግል ከማውቃቸው መካከል አብዛኞቹ ለዘለቄታው ተባረኩ! ተለወጡ እናም በመንፈስ ቅዱስ ተሞሉ፡፡

የዚህ ሁሉ መሠረት ከእግዚአብሔር ጋር ያለ አስደናቂ ህብረት ነበር፡፡ በመጀመሪያ ይህች ሴት ወንጌል ሰባኪ ወይም አስተማሪ አልነበረችም፤ ነገር ግን በጥቂት ወራት ውስጥ በመቶዎች በሚቆጠሩ ሰዎች ህይወት ውስጥ መንፈሳዊ መነቃቃትና ሃይል እንዲለቀቅ እግዚአብሔር ተጠቀመባት፡፡ ለህብረት የነበራት ፍቅርና በክርስቶስ ኢየሱስ የነበራት አንፀባራቂ ደስታ ብዙዎች ለእግዚአብሔር ያላቸው ፍቅር እንዲቀጣጠል አደረገ፡፡ በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ወቅት በሰላሳ ሦስት ዓመቷ ህይወቷ በባህር ላይ ያለፈ ሲሆን፣ በዚህም ከውዷ ጋር ለዘላለም ፊት ለፊት ለመተያየት ሄዳለች፡፡

አ! ህይወትህን በቅድስተ ቅዱሳን ውስጥ በምታጠፋው ጊዜ መዝነው፡፡ ለሰዚህ ነገር ለሌሎች አብዝተህ መናገር አያስፈልግህም፡፡ ያ የአንተ የተቀደሰና የብቻህ ከአብና ከመንፈስ ቅዱስ ጋር በተለይም ከኢየሱስ ጋር ህብረት የምታደርግበት ጊዜ ነው፡፡ አብዝተህ የምትናገር ከሆነ ግንኙነቱን ልታጣው ትችላለህ፡፡ ነገር ግን ቅድሱን ወዳጅህን በውበቱና በክብሩ እስከታገኘው ድረስ ፈልገው፡፡

ሕይወትህን፤ ከኢየሱስ ጋር ባለህ ህብረትህ ቅርበት መዝነው፡፡ በእግዚአብሐር ልብ ውስጥ በቅርበት በመኖርህ፤ በእግዚአብሔር አይኖች ፊት ታላቅ ልትሆን ትችላለህ፡፡ እግዚአብሔር በወዳጁ በአብርሃም፣ በእረኛው በዳዊት፣ ፍቅር የተሞላ ልብ በላት በማርያምና በተወዳጁ ዮሐንስ የተደሰተው በዚህ ምክንያት ነበር፡፡ ከማንኛውም ሌላ መንገድ ይልቅ ከእግዚአብሔር

ጋር ህብረትን በማድረግህ በእግዚአብሔር ልብ ውስጥ ተጨማሪ ደስታን ልታመጣ ትችላለህ። ሕይወትህን፣ ከእግዚአብሔር ጋር ባለህ በቀረበ፣ ደስታን በተሞላና በከበረ ግንኙነትህና ህብረትህ መዝነው።

እሁን ይህን ውብ የሆነ ዝማሬ ከእኔ ጋር እንዘምረው። ይህንን መዝሙር የፃፈችው አንዲት ህንዳዊት እህት ስትሆን፣ የኖረችው እኛ በህንድ ለሃያ አምስት አመታት በሚስዮናዊነት ካገለገልንበት አላሃባድ ተብሎ ከሚጠራው ስፍራ አንድ ኪሎ ሜትር ያህል ወረድ ብሎ ነው። አብረን እንዘምረው።

*በህልውናው ሚስጥር ውስጥ መሰወርን፣ ነፍሴ እንዴት ትናፍቃለች!*
*በኢየሱስ እግር ስር ተቀምጬ የተማርኳቸው ትምህርቶችስ እንደምን ውድ ናቸው!*
*ምድራዊ ነገሮች ልቤን አያሳዝኑም፣ ፈተናም ቁልቁል እንዳዘግም አያደርገኝም፣*
*ሰይጣን ሲፈትነኝ በተገለጠ ጊዜ ፈጥኜ ወደ ሚስጢራዊው ስፍራዬ እሄዳለሁ።*
*ህይወቴ በደከመችና በተጠማች ጊዜ፣ ወደ ስንፎቹ ጥላ እጠጋለሁ፣*
*በዚያ ቀዝቀዝ የሚያደርግ አስደሳች መጠለያ፣ ንጹህና የጠራ ምንጭ አለ።*
*አዳኜንም አጠገቤ እየዋለሁ። ጣፋጭ የሆነውን ቅዱስ ህብረት ስናደርግም ብደክም እንኳን አልቃትትም።*
*እኔ የማውቀው አንድ ነገር፣ ለእርሱ መናገሬን ብቻ ነው። ጥርጣሬዬን፣ ሀዘኔንና ፍርሃቴን።*
*አ! ምንኛ በጥሞና ነው የሚያደምጠው! የወደቀችውን ነፍሴን አጽናናት!*
*ሳይገስፀኝ ግን የተወኝ ይመስሎችኋል? እንዲያ ቢሆንማ እውነተኛ እንዳልሆነ ወዳጅ በሆነ ነበር፣*
*እውነተኛ ያልሆነ ወዳጅ በእኔ ላይ ያየውን ሀጢያት ገልጦ አይናገርም።*



*በእውነት የጌታን ጣፋጭነት ምስጢር ማወቅ ትፈልጋላችሁ?*
*ሄዳችሁ ከጥላዎቹ በታች ተሸሸጉ፣ ሽልማታችሁም ይሄው ይሆናል። ከዚህ ከአስደሳች ፀጥታ ከነገሰበት የመገናኛ ስፍራ ስትወጡ፣*
*የጌታን መልክ በፊታችሁ ላይ እያብለጨለጫችሁ ትወጣላችሁ።*

ኢ.ኤል.ጎእር

### ዛሬ ከእግሮችህ ሥር ልቀመጥ

አፍቃሪ ጌታዬ ሆይ፤ እግሮችህ ስር መቀመጥን ምንኛ ተርቤያለሁ:: ከአንተ ጋር የሚደረግ ጣፋጭና ውድ የሆነውን ህብረት ለመካፈል ተጠምቻለሁ:: አ! ይህ ባርኮት ነው፤ ከአንተ ጋር መሆን በመንግስተ ሰማይ እንደ መቀመጥ ነው:: ዛሬ ከእግሮችህ ሥር ልቀመጥ::

አፍቃሪ ጌታዬ ሆይ፤ ያንን ውብ ድምፅህን እባክህ ላድምጥ፤ መላእክትም ይሁኑ ሰዎች ከቶውን አድምጠውት የማያውቁትን ጣፋጭ ድምፅህን ልስማው:: ልቤ እስኪቀልጥና እስኪነቃቃ ድረስ ላድምጠው:: ዛሬ ከእግሮችህ ሥር ልቀመጥ::

ውድ ጌታዬ፤ ድምጽህን ለሰዓታት ያህል ልስማው፤ ነፍሴን ምንኛ ያስደስታታል! ምንኛስ በደስታ ይሞላኛል! ከምንም በላይ ይህ ታላቁ ምርጫዬ ነው:: ዛሬ ከእግርህ ሥር ልቀመጥ::

ፊትህን አተኩሬ ስመለከት፤ እባክህ ፍቅርህን ልጎንጭ፤ ፍቅርህን፣ ውበትህንና ጸጋህን ሁሉ ልየው:: ቀኑን ሁሉ ከአንተ ጋር አጣበቅ ዘንድ፤ እባክህን ይህንን ስፍራ ስጠኝ:: ዛሬ ከእግርህ ሥር ልቀመጥ::

ዌስሌይ ዱዌል



# 7

## ሕይወትህን በምልጃ ፀሎትህ መዝን

እግዚአብሔር ህይወትህን ከሚመዝንባቸው ዋነኛ መንገዶች አንዱ የምልጃ ፀሎትህ መሆኑን ተገንዝበሃልን? የምር የሆነ ፀሎትህ ልትደርስባቸው ከምትችላቸው ከማንኛውም አይነት ድንበሮች በላይ አብዝቶ ሕይወትህን ሊያሰፋ ይችላል:: ሕይወትህን፣ ለክርስቶስ መንግስትና ሌሎች ወገኖች በምታደርገው ወቅታዊ የሆነ ጠንካራ ጸሎትህ መዝነው:: በመንግስተ ሰማይ በሚኖር የምስክርነት ጊዜ፣ ሰዎች ስለ ጸሎትህ ሲያመሰግኑህ፣ ጠንካራ የምልጃ ጸሎትህና የተቀደሰ ህይወትህ ስላስከተሰው ተጽእኖ እግዚአብሔርን ለማመስገን ስንቶች ይነሱ ይሆን? የህይወትህን ስፋት፣ ጥልቀት፣ ከፍታ እና ርዝመቱንም በምልጃ ህይወትህ መዝነው::

### የህይወትህን ስፋት በምልጃ ጸሎትህ መዝን

የህይወትህን ስፋት መዝን:: ይህን በምልጃ ጸሎትህ ልትመዝነው ትችላለህ:: በመንፈሳዊ ሕይወትህ የደረስክበትን ደረጃ ጠንካራ በሆነ ፀሎትህ መዝነው:: የምልጃ ፀሎትህ የምትኖርበትን ማህበረሰብ እስከሚያካትት ድረስ በቂ ስፋት አለውን? በአካባቢህ ላሉ ባለስልጣኖች ምን ያህል ሳታቋርጥ ትጸልያለህ? ባለህበት አካባቢ ለሚገኙት አብያተክርስቲያናት እየማለድክ ትጸልያለህ? ለመጋቢዎቻቸውስ? ጸሎትህ በአካባቢው ያሉትን ትምህርት ቤቶች ይጨምራል? በምትኖርበት አቅራቢያ ላሉ ወጣቶችስ የጸሎት ሸክም አለህ?

ላለህባት ቤተክርስቲያን መንፈሳዊ ዘብ (ጉበኛ) ሆነህ ቆመሃልን? ለከተማህስ? የእግዚአብሔር ጉበኞች ለማየትና አይቶም ለመጸለይ ሃላፊነት አለባቸው። "ኢየሩሳሌም ሆይ ጉበኞችን በቅጥርሽ ላይ አቁሜአለሁ፤ ቀንና ሌሊት ከቶ ዝም አይሉም፣ እናንተ እግዚአብሔርን የምታሳስቡ፣ ኢየሩሳሌምን እስኪያፀና በምድርም ላይ ምስጋና እስኪያደርጋት ድረስ አትረፉ፤ ለእርሱም እረፍት አትስጡ" (ኢሣ 62፥6-7)። ለእኔና ለአንተ የእግዚአብሔር ጥሪ ይሄ ነው። ለቤተ ክርስቲያናችን፣ ለከተማችን አልፎም ለሀገራችን ዘቦች (ጉበኞች) ልንሆን ተጠርተናል። ንቁ ሆነን ልንቀጥልና ልንጸልይ ይገባል።

የምልጃ ፀሎትህ የሀገርህን መንግስት እስኪጠቀልል ድረስ ሰፊ ነውን? ለገዢዎች፣ ለምክር ቤት ተመራጮችና ለሸንጎ አባላት ትጸልያለህ? መንግስትህ ስለሚያወጣቸው ሕጎች ትጸልያለህ? ጸሎትህስ ህዝቦችን ሁሉ እስኪያጠቃልል ድረስ በቂ ነውን? ለሀገርህ እንድትጸልይ ጳውሎስ እንዲህ ሲል ይመክርሃል! "እንግዲህ እግዚአብሔርን በመምሰልና በጭምትነትም ሁሉ ፀጥና ዝግ ብለን እንድንኖር ልመናና ጸሎት ምልጃም፤ ምስጋናም ስለ ሰዎች ሁሉ ስለ ነገስታትና ስለ መኳንንትም ሁሉ እንዲደረግ ከሁሉ በፊት እመክራለሁ" (1ጢሞ 2፥1-2)። እነዚህ ሁሉ ፀሎትህን ይፈልጋሉ። እግዚአብሔር ይህን ትእዛዝ በመፈፀምህ መታዘዝህን ይመዝናል። በእውነት ለመንግሥት የማትፀልይ ከሆነ መንግስትን መተቸት የለብህም። በሌላ አባባል ህይወትህን በጸሎት መዝገብህ ላይ በያዝካቸው የፀሎት ርዕሶችና ለመጸለይ በምትወስደውም ጊዜ መዝነው።



በሌላው የዓለም ክፍል የሚገኙ ሀገሮችን ስም እየጠራህ ትጸልያለህን? ለእስም መሪዎችስ? እለምን ስላጨናነቁ ችግሮችስ?

በህንድ አገር አንድ ማህበራዊ ተግባር በምናከናውንበት ጊዜ ስልሣ የምንሆን ሰዎች ከጠቅላይ ሚኒስትር ኔህሩ ጋር መገናኘት ችለን ነበር። በድንገትም ጠ/ሚኒስትሩ እያንዳንዳችንን መጨበጥ እንደሚፈልጉ ተነገረን። መስመር ይዘን ተሰለፍን፤ ጠቅላይ ሚኒስትሩ እየቀረቡን በመጡ ጊዜ፣ ከእርሳቸው ጋር በሚኖረኝ አጭር ቅጽበት፣ እግዚአብሔር ምን ልናገራቸው እንደሚፈልግ ማሰብ ጀመርኩ። ፊታቸውን እየተመለከትኩ፣ "ጠቅላይ ሚኒስትር ኔህሩ፤ በየቀኑ እፀልይልዎታለሁ" አልኩ። በድንገት አይኖቼን ትኩር ብለው ሲመለከቱ ቆዩና ስሜታቸው ተነክቶ "አመሰግናለሁ" አሉኝ። የህይወትህን ስፋት በምልጃ ጸሎትህ ስፋት መዝነው። ዓለም ዓቀፋዊ ክርስቲያን ሁን።

## የሕይወትህን ጥልቀት፤ በምልጃ ፀሎትህ መዝነው

ብዙ ሰዎች የሚኖሩት ጥልቀት የሌለው ህይወት ነው። ስለ ቤተሰቦቻቸው ደስተኞች ናቸው፤ ነገር ግን ስለ ቤተሰቦቻቸው የምር የሆነ መንፈሳዊ ሃላፊነትን አይወስዱም። በቤተሰቦቻቸው ላይ የፀሎት ዘር አይዘሩም። እንደዚሁ ደግሞ በቤተክርስቲያን ያላቸውም ህይወት ላይ ላዩን ብቻ ነው። የቤተክርስቲያን ፕሮግራሞችን በመከታተላቸውና ለስም ያህል አንዳንድ አስተዋጽኦ በማድረጋቸው ይረካሉ። ለቤተክርስቲያንና በውስጧም ላሉ አባሎቿ ሕይወትና ምስክርነት በጭራሽ መንፈሳዊ ሸክም የላቸውም። በጸሎታቸው ውስጥ እንዲያው ለይምሰል አልፎ አልፎ ብቻ ቤተክርስቲያናቸውን ጠቀስ አድርገው ያልፋሉ። በፀሎት አያለቅሱላቸውም፣ እናም

በፆምና በፀሎት በእግዚአብሔር ፊት ይዘዋቸው ስመቅረብ ያን ያህል ግድ የላቸውም። ሰቤተክርስቲያንህ የምታደርገው የጸሎት ምልጃ ምን ያህል ነው?

ስማንኛውም ሰውና ስምንም ነገር ይሁን የምልጃ ጸሎትህ ምን ያህል ጥልቀት አለው? እንዲያው ከህይወት ልምድህ የጸሎት ሸክም ምን እንደሆነ ታውቃለህ? ቀጣይነት ባለው የምልጃ ጸሎት ልትሸከመው ለማንም ሰው ይሁን ለምንም ነገር በቂ የሆነ ፍቅር አለህ? የህይወትህን ጥልቀት በምልጃ ጸሎትህ ብቃት መዝነው።

በምትማልድበት ጊዜ የሚያነባ ልብ እንዲኖርህ የሚያስችል ያህል ፍቅር አለህን? ስራስ በማዘን የሚፈስ እንባ ተራ እንባ ነው። ብዙውን ጊዜም ስጋዊ ነው። ስሌሎች የፀሎት ሸክም ተሰምቶህ የምታፈሰው የፍቅር እንባ ግን በእግዚአብሔር አይን ፊት የከበረና ሃያል ነው። እንዲህ አይነቱ እንባ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ነው።

ዳዊት ስለ ህዝቡ እጅግ ትልቅ መንፈሳዊ ሃላፊነት ነበረበት። ጠላቶቻቸው እየከበቡ ጠራርገው ሊያጠፏቸው ይፈልጉ ነበር። ስህዝቡ በጸለያቸው ጸሎቶች በአንዱ እንዲህ ይላል፤ "በቀንና በሌሊት እንባዬ ምግቤ ሆነልኝ . . . ነፍሴንም አፈሰስኳት" (መዝ 42፥3-4)። እግዚአብሔር የፀሎትን እንባ እንደሚመዝን ያውቅ ነበር፤ "አምላክ ሆይ ህይወቴን ነገርኩህ፤ እንባየን እንደ ትእዛዝህ በፊትህ አኖርህ" (መዝ 56፥8)። ዘማሪው፤ "ህግህን አልጠበቅሁምና የውሃ ፈሳሽ ከአይኖቼ ፈሰሰ" (መዝ 119፥136) ሲል ጽፏል። ስህዝብህ እንደዚያ ያለ የፀሎት ሸክም ይኖርሃልን?

እስራኤል እንደ አገር ጸንታ እንድትቆምና በመጽሐፍ ቅዱስ የትንቢት ቃል መሠረት ኢየሱስ ከአይሁድ ቤተሰብ ሊወለድ



የቻለው፣ ዳዊት፣ ኢሣያስ፣ እዝራ፣ ነህምያ፣ ኤርምያስ እና ሌሎች በእግዚአብሔር ዘንድ እውቅና ያገኙ ሰዎች ስዚያች ምድር በማያቋርጥ የምልጃ ጸሎት ወደ እግዚአብሔር በመጮሃቸው ነው። ከአንተ የምልጃ ጸሎት የተነሳ በምን በምን መንገድ ነው የእግዚአብሔር መንግስት እየሰፋ ያለው?

ጳውሎስ ስቤተክርስቲያንና ስእስራኤል በነበረው ታላቅ ሸክም ምክንያት ያነባ ነበር። እንደታየው ኢየሱስ ክርስቶስ በሚፀልይበት ጊዜም በተደጋጋሚ ያለቅስ ነበር (ዕብ 5፥7)። አንተስ ስጠፉት ነፍሳትና ስምድርህ በእንባ በመፀለይ ጉዳይ ክርስቶስን ምን ያህል ትመስለዋለህ? መማለድን የሚናፍቅ የሚያነባ ልብ ከእግዚአብሔር ዘንድ እንዲሰጥህ ፈልግ።

## የሕይወትህን ከፍታ በጸሎትህ ለካው

የህይወትህን ከፍታ፤ በምልጃ ጸሎትህ በርግጥ ምን ያህል ጊዜ የሰማይን ደጅ እንዳንኳኳህ በማወቅ ለካው። ቆርኖሊዮስ ከአህዛብ ወገን ቢሆንም በጸሎት ልማዱ ታማኝ የሆነ ሰው ነበር። ፀሎቱም እስከ ክርስቶስ ዙፋን ዘልቆ ተሰምቶስታል። እግዚአብሔር ህይወትህን በመደበኛ ዕለታዊ ጸሎትህ መጠንና ጥራት እንዲመዝን ትፈልጋለህን? ያደርገዋል። ጸሎቱ እንደ ተሰማ ስቆርኖሊዮስ እንዲያረጋግጥስት እግዚአብሔር መልአክን ልኮስታል (ሐዋ 10፥4፤ 30-31)።

የዳንኤል ጸሎት ሰማይ ደርሶ ነበር። ይህንንም እንዲያረጋግጥስት ስሦስት ጊዜያት ያህል እግዚአብሔር መልአኩን ገብርኤልን ልኮ ነበረ (ዳን 8፥15-18፤ 9፥20-23፤ 10፥10-14፤ 18-19)። ጸሎትህ ወደ እግዚአብሔር ዙፋን እንደደረሰ መንፈስ ቅዱስ

የሚያረጋግጥባቸው እነዚያ ጊዜያት እንዴት የከበሩ ናቸው! መላእክቱ፤ በምልጃ ጸሎታቸው አዘውትረው ወደ መንግስተ ሰማይ ከሚቀርቡት ሰዎች መካከል አንተን አንዱ መሆንህን ያውቁ ይሆን? በመላእክቱ መካከል በደንብ የታወቅህ ነህ? ህይወትህን፣ በምልጃ ጸሎትህ ከፍታ ለካው።

የተወደደው ሀዋርያ ዮሐንስ በጌታ ቀን በመንፈስ ነበር (ራዕ 1፥10)። የሮም መንግስት ፍጥሞ ወደምትባል አለታማ ደሴት በግዞት ልኮት ነበር። በዚህ ምክንያት በኤፌሶን የነበረችው ቤተክርስቲያን መጋቢነቱን መቀጠል ሊሆንለት አልቻለም፤ ነገር ግን ሊማልድላት ይችል ነበር። ምናልባትም ዮሐንስ በመንፈስ ሆኖ ይፀልይ የነበረው በቤተክርስቲያኑ የአምልኮ ሰዓት ሊሆን ይችላል፤ እና ምናልባትም መጋቢ ለሆነላቸው በኤፌሶን ቤተክርስቲያን ለሚገኙ ወንድሞችና እህቶች እየጸለየላቸው ይሆናል። ዮሐንስ በትክክል በጸሎቱ ሰማይን ነክቷል፤ ራዕዩንም በራዕይ መጽሐፍ ላይ በሚመዘግብበት ወቅት ከሰማያት ጋር ተገናኝቷል።

ሕይወትህን፤ በጸለይክ ጊዜ ምን ያህል ከሰማይ የሆነ መነካት እንደተነካህ በማወቅ መዝን። በጸሎትህ ወቅት የእግዚአብሔርን ክብር መገኘት ተለማምደሃልን? የፀሎት ግንኙነትህን ከክርስቶስ ጋር ብቻህን በሆንክ ጊዜ በሚሰማህ ሊገለጽ በማይችል ክቡር ደስታህ መዝነው። ህይወትህን፤ የጌታን ፊት በተመለከትክ ጊዜ ባለህ የግንኙነት ከፍታ መዝነው። እንዲህ ደግሞ ጌታ በሚማልድበት ጊዜ ከእርሱ ጋር በመተባበርህና ለመንግስቱ አብረህ በማለድከው የፀሎት ከፍታህ ለካው (ሮሜ 8፥34፤ ኤፌ 2፥6)።



<u>የሕይወትህን ርዝመት በምልጃ ፀሎትህ ለካው</u>

በምልጃ የሚተጉ ሰዎች ፀሎት ዘላቂ ውጤት ይኖረዋል። እስከ አሁን ድረስ እንኳን ዳዊት፣ ኢሣይያስ፣ ጳውሎስና ኢየሱስ የፀለዩአቸውን ጸሎቶች አዝመራ እያጨድን ነው። አሁንም ድረስ ሉተር፣ ዊስሌይ፣ ቻርልስ፣ ፊኒና ኢ.ኤም ቦንድስ የጸለዩዋቸውን ጸሎቶች ፍሬ እያጨድን ነው። ብዙውን ጊዜ በመንፈስ የሚጸለዩ ፀሎቶች ጣምራ የሆኑ መልሶች አላቸው፤ ተደጋጋሚ ውጤትም ያመጣሉ። የአንዳንዶቹ ፀሎቶች መልስ ልክ በሕዝቅኤል 47 እንዳለው ወንዝ ነው። በአመታት መካከል እየሰፉና ጥልቀት እየጨመረ ይሄዳል። የቀደመውን ዘመን ጸሎት ከራሳቸው ጸሎት ጋር በመጨመር ተግተው በሚጸልዩ የኢየሱስ ክርስቶስ የጸሎት አርበኞች ሕይወት መልስ ፍሰጋ ሳያቋርጥ ይፈስሳል። በኢየሱስ ክርስቶስ የፍርድ ዙፋን ፊት በምንቆምበት ጊዜ፣ በምድር ላይ ታላቅ የተቀደሰ ተጽእኖ የሚያስከትል ወንዝ ይፈላል። እነዚያ የምልጃ ጸሎቶች ይመለሳሉ፤ ደግመው ደጋግመው ያስተጋባሉ፤ ጸሎቶቹ ተቀባይ ማግኘታቸውም ደግሞ ደጋግሞ ይረጋገጣል።

ለዘመናት ጸንቶ የሚኖር የማያቋርጥ ጸሎት ታቀርባለህን? ለመንግስቱ መስፋት፣ በቤተ ክርስቲያኑ ውስጥ መነቃቃት እንዲመጣና የእግዚአብሔር ባርኮት እንዲፈስ፣ ስለምድር የመከር ዘመን፣ በእግዚአብሔር መስክ ላይ የመከሩ ሠራተኞች እንዲበዙ፣ ስለ ጠፉት ነፍሣትና በሚያሰቅቅ ሁኔታ በብዙ ጉድለት ላለችው ዓለም፣ በመንፈስ የሚጸለየው ማናቸውም አይነት ጸሎት በሰማያዊ ዙፋኑ ላይ ሆኖ በሚማልደው በኢየሱስ ክርስቶስ የሚሰማና የሚታሰብ ነው (ራዕይ 5፥7)። መንፈስ ቅዱስ በምትጸልይበት ጊዜ ይህን ሸክም መሸከም እንድትችል ልብህን ያሰፋልሃል። ኢየሱስ

ክርስቶስ ለጸሎትህ ከሰማይ የሆነ አሜን ነው (ራዕይ 3+14)፡፡ ያ ጸሎትህ መቼም ቢሆን መች አይሞትም፡፡ እስከ ዘላለም ድረስ እየሰፋና ውጤታማ እየሆነ ይዘልቃል፡፡

በእግዚአብሔር ዘንድ በመንግስተ ሰማይ መዝገብ ከተጠራቀሙት የቅዱሳን ጸሎቶች መካከል ታላቅና ወቅታዊ የሆኑ ጸሎቶችህ ምን ያህል ናቸው? እስከ እሁን ድረስ ያልተመለሱ ነገር ግን በመንፈስ ቅዱስ አነሳሽነትና በመንፈስ ቅዱስ መሪነት የተጸለዩ ጸሎቶች ሁሉ በጭራሽ ጠፍተው አይቀሩም፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስ ታላቁን አሜንታ ሰጥቷቸዋል (ራዕይ 3+14)፡፡ በሰማይ ያለው የጸሎቱ እጣን ጭስ ከአንተ ጸሎት ጋር ይጨመራል፤ እናም በምድር ላይ ውጤታማ ይሆናል (ራዕይ 8+1-5)፡፡ የክርስቶስንም መንግስት ያፋጥነዋል፡፡ እግዚአብሔር ይመስገን!

በኮርያ የሚገኙ የማንኛውም ቤተ እምነት ክርስቲያኖች በየዕለቱ ከሰሊቱ 10:30-11:00 የሚዘልቅ ጸሎት ለማድረግ በየቤተ ክርስቲያኖቻቸው የመሰብሰብ ልምድ አላቸው፡፡ በኢኤም.ኤስ አለም ዓቀፍ አማካኝነት ከተመሰረተችው ከኮሪያ ቅዱሳን ወንጌላዊ ቤተ ክርስቲያን በቁጥር 600,000 ከሆኑት አማኞች መካከል ሲሶ ያህሉ በዚህ ጸሎት ይሳተፋሉ፡፡ እዚህ ጋ አንድ ነገር ልብ በል፤ ቤት ለመጠበቅ ሲባል ከአንድ ቤት አንድ አዋቂ ሰው ሁል ጊዜም ከቤት ይቀራል፡፡ በጸሎት ስብሰባቸው ወቅት ትልቁን የፀሎት ክፍልና ትኩረት የሚሰጡት ለምልጃ ጸሎት ነው፡፡

የህይወትህን ርዝመት፤ በሰማይ ባከማቸኸውና ገናም የእግዚአብሔርን ታላቅ ሙሉ መልስ በሚያገኘው የምልጃ ጸሎትህ ለካው፡፡ ማንኛውም ክርስቲያንና እያንዳንዱ ክርስቲያን ከክርስቶስ ቅዱስ ምልጃ ጋር በመቀላቀል፣ የክርስቶስም የፀሎት አጋር



በመሆን፣ ለመጸለይም በመንፈስ ቅዱስ በመቀባት (ሮሜ 8+26)፤ እንደ አንድ ታማኝ ጉበኛ በእግዚአብሔር ዙፋን ፊት ጸሎትን በማቅረብ (ኢሣ 62+6-7) የህይወቱን ስፋት፣ ጥልቀት፣ ከፍታና ርዝመት ሊጨምር ይችላል፡፡

ከሌላ ከማንኛውም መንገድ ይልቅ በጉልበትህ በመንበርከክ ዓለምን ለእግዚአብሔር ማንቀሳቀስ ትችላለህ፡፡ በሌላ በማኛቸውም መንገድ ማድረግ ከምትችለው ሁሉ በላይ በምልጃ ፀሎትህ ለብዙዎች ባርኮት መሆን ትችላለህ፡፡ ለእግዚአብሔር ልትሠራ የምትችለው ታላቁ ሥራ እንደ ፊቃዱ በመማለድ መፀለይ ነው፡፡ በማንኛውም ክርስቲያናዊ አገልግሎት ማድረግ ከምትችለው በላይ ከእግዚአብሔር እቅድና አላማ ጋር ራስህን ማሰለፍ የምትችለው በፀሎት ነው፡፡ በማንኛውም አይነት መንገድ ማድረግ ከምትችለው በላይ ታላቅ የሆነውን የእግዚአብሔርን የፍቅር ልብ ምት በቅርበት ልታደምጥ የምትችለው በምልጃ ጸሎትህ ነው፡፡

ከማንኛውም እንቅስቃሴህ ይልቅ የእርዳታ እጅህን በፍጥነት መዘርጋት የምትችለው በጸሎት ነው፡፡ ከማናቸውም ሌላ መንገዶች ይልቅ ከባድ የሆኑ ሸክሞችን ማስወገድ የምትችለው በፀሎት ነው፡፡ አዎን ከማንኛውም ሌላ መንገድ በተሻለ ሁኔታ ክርስቲያናዊ በሆነ ፍቅር ፍጥረትን ለማጽናናት እጆችህን መዘርጋት የምትችለው በጸሎት ነው፡፡ በሀዘን ካሉ ሰዎች አይን ላይ ብዙ እንባ ማበስ ትችላለህ፤ እጅግ በርካታ በሆኑ ህፃናት የራስ ላይ የባርኮት እጆችህን መጫን ትችላለህ፤ ብዙ ወጣቶችን ለመምራት እጆችህን ልትለጣቸው ትችላለህ፤ ከማንኛውም ሌላ መንገድ ይልቅ የብዙ ክርስቲያን የወንጌል ሠራተኞችን እጅ በጸሎት ለማጽናት ትችላለህ፡፡ ይህ የሚሆነው ግን በእግዚአብሔር ፊት የምር የሆነ ፀሎትና

ምልጃህን ያቀረብክ እንደሆነ ብቻ ነው። ጸሎት አንተ የምታደርጋቸውን ማንኛቸውንም አይነት ድርጊቶች የሚተካ አይደለም፤ ይልቁንም ለምታደርገው ማንኛውም ነገር ማስሪያ ነው። ፀሎት በምታደርጋቸው ነገሮች ሁሉ ላይ ሃይልን ይጨምራል። ይህም ብቻ አይደለም፤ ነገር ግን በሌላ በማናቸውም መንገድ ልትባርካቸው የማትችላቸውን ሰዎች በጸሎትህ ልትደርሳቸውና ልትረዳቸው ትችላለህ።

ይሁንና በእርግጥ ትማልዳለህ? ለስ ሌሎች ሰዎች በእግዚአብሔር ፊት ልመናን ማቅረብ ምን እንደሆነ ታውቃለህ? ሐዋርያው ጳውሎስ (ኤፌ 6፥12 እንደ ግሪኩ ቃል ትርጉምና ቆላ 4፥12) ከዚህ ጨለማ ዓለም መንፈሳዊ ገዢዎች ጋር በጸሎት መጋደል ብሎ የሚጠቅሰውን አዘውትረህ በህይወትህ እየተለማመድከው ነውን? ኢየሱስ ክርስቶስ በዚህ ዘመን የእርሱ ተከታዮች የሆኑ ስለሚያሳዩት ባህሪ ሲገልጽ፣ "በዚያን ጊዜ ይጾማሉ" (ማቴ 9፥15) ብሎ የተናገረውን ትፈጽም ዘንድ አዘውትረህ ራስን በመካድ ትጸልያለህን? በእርግጥ ጸሎትህ ሃይል ያለውና ውጤታማስ ነው (ያዕ 5፥16)?

ሕይወትህን፤ በምልጃ ጸሎትህ መዝነው። በራስህ የህይወት ልምምድ ነገሮችን ወደ እግዚአብሔር ህልውና ማቅረብ የሚቻልበትን ምስጢር ምን ያህል ታውቃለህ? ኢየሱስ ክርስቶስ ለደቀ መዛሙርቱ እንዲህ አለ፤ "ለአንድ ሰዓት ያህል እንኳን ልትተጉ አልቻላችሁምን?" (ማቴ 26፥40)። ዛሬም ኢየሱስ በፊቱ በፀሎት የምታሳልፈውን ሰዓት ይቆጥር ይሆን? እንደዚያ ከሆነ ሕይወትህ ግን በብዙ መልካም ነገሮች የተሞላ ቢሆንም ኢየሱስ



በራሱ ሕይወት ቅድሚያ የሰጠውን ነገር ቸል በማለትህ፤ ራስህን ምን ያህል በህፍረት ዝቅ ታደርግ ይሆን?

ሕይወትህን በምታደርገው የምልጃ ጸሎት የምትመዝን ከሆነ፣ በጸሎት የምታሣልፈውን ጊዜ በጥንቃቄ ልትመዝነው የግድ ነው። ሕይወትህን፣ የጸሎት ሸክምን በምትሸከምበት አቅም መዝነው። ሕይወትህን፤ መንፈስ ቅዱስ ለግለሰቦች ወይም ለአንዳንድ ሁኔታዎች በሰጠህ የተለየ የጸሎት ሸክም ብዛት መዝነው። ሕይወትህን፣ ጸሎቶችህ ወደ ምስጋና እስኪቀየሩና አሸናፊነትን በእምነት እስክታውጅ ድረስ በጸሎት ጸንተህ በመቆየትህ መዝነው።

ሕይወትህን፣ በፀሎት በምታምጥላቸው ያልዳኑ ሰዎች ቁጥር፣ በጸሎትህ አገልግሎታቸውን በምታግዛቸው ክርስቲያን የወንጌል አገልጋዮች፣ በመደበኛነት በምትጸልይላቸው የክርስቲያን ማሰልጠኛ ተቋሞች፣ የክርስቲያን ስነ ጽሑፍ ድርጅቶች፣ የክርስቲያን የሬዲዮ ፕሮግራሞችና በሌሎች ክርስቲያናዊ ድርጅቶች ቁጥር መዝነው። ሕይወትህን፤ በጸሎት ርእሶችህ ዝርዝር ርዝመት፣ በመላው አለም ለሚገኙ ህገሮችና ህዝቦች ሁሉ በመፀለይ ጉልበትህ መዝነው።

በኒውዚላንድ አገር በሰሜን ፓልመርስቶን ነዋሪ የሆኑትና ታማኝ የሆነ ባል ያላቸው ወ/ሮ ናይት የተባሉ ሴት በየጠዋቱ ከሌሊቱ 10:00 ሰዓት ጀምሮ ለአገልግሎቱ እንደሚጸልዩ ነገሩኝ። በዚሁ በኒውዚላንድ ላይኛው ሁት በተባለው ክልል ነዋሪ የሆኑት አቶ ራይት ደግሞ የፀሎት ክፍላቸውንና ገጾቹ እየተገባደዱ ያሉትን በአገራት ካርታዎች፣ የእኔን ጨምሮ በተሰያዩ ክርስቲያን አገልጋዮች ፎቶግራፎች የተሞላ የጸሎት መዝገባቸውን አሣዩኝ። አሁን

በጡረታ ላይ ባሉበት ጊዜ በዓለም ዙሪያ ላሉ አገልጋዮች በየቀኑ ምን ያህል ሰዓት እንደሚማልዱም አጫወቱኝ:: በጡረታ የተገለሉ አድሚያቸው ወደ ሰማኒያዎቹ የተጠጋ ሁለት የአውስትራሊያ ዜግነት ያላቸው ባልና ሚስት፣ ለአመታት የእኔን አገልግሎት አስመልክቶ ከሌሊቱ 10:00 ሰዓት ጀምሮ እንደሚፀልዩ ነግረውኛል::

እነዚህን ሰዎች በግል አውቃቸዋለሁ፤ ነገር ግን በመንግስተ ሰማይ ያለው መዝገብ የሚያውቃቸው፣ የጸሎት ልማዳቸው የእኛን አንገት በሀፍረት የሚያስደፋ በሚሊዮን የሚቆጠሩ የእግዚአብሔር ቅዱሳን ለመኖራቸው ምንም ጥርጥር የለውም:: እነርሱ የእግዚአብሔር ድብቅ የፀሎት ባለሥልጣናት፣ በዓለም ያልታወቁ የክርስቶስ መንግስት ጀግኖች ናቸው:: በክርስቶስ ኢየሱስ የፍርድ ዙፋን ፊት መላው አለም እያየና እየሰማ ክብርን ይቀበላሉ:: እኔና አንተም ሕይወታችንን በምልጃ ጸሎታችን ልንመዝነው ይገባል::

ሕይወትህን በስደት ላይ ላሉ ክርስቲያኖች፣ በእምነታቸው ምክንያት ለታሠሩና ከሀገራቸው ለተባረሩ ቅዱሳን፣ ለምስክርነትና ወንጌል እንዲሮጥ ለማድረግ ቤታቸውንና የሚወዷቸውን ቤተሰቦች ተለይተው ለወጡ አገልጋዮች በታማኝነት በመጸለይህ መዝነው:: ሕይወትህን፤ ለገዥዎችና በምትኖርበት ምድር ላሉ ባለስልጣናት ሁሉ በታማኝነት በመጸለይህ መዝነው (1ጢሞ 2፥1-2)::

ሕይወትህን፣ ለጸሎት ጊዜ ለማትረፍ ብለህ ሌሎች ነገሮችን ወደ ጎን ማድረግ በመቻል ባለመቻልህ መዝነው:: ሕይወትህን ከእግዚአብሔር ጋር በፀሎት ብቻህን ለመሆን ባለህ ርሃብ መዝነው:: ሕይወትህን፣ መላው ህይወትህ በጸሎት በመሞላቱና ያለማቋረጥ በመጸለይህ መዝነው (1ተሰ 5፥17):: ለእግዚአብሔር ታላቅ፣ ጠቃሚ እና በፊቱም ሃያል የሚያደርግህ ከጸሎትህ በላይ ምንም



የለም:: በሰማይ ሕይወትህ የሚመዘነው በጸሎትህ ነው:: በዚህ ረገድ የህይወትህን ልኬት ስትመለከት ምን አገኘህ?

### በፀሎት ግፋ

ሰጠፉት ሰዎች በመማለድ ምን ያህል ቀንበራቸውን ትሸከማለህ? ምን ያህል ርህራሄስ ስለእነርሱ ይሰማሃል? ወይስ ዋጋ መክፈል ባለመፈለግህ ሆን ብለህ ቸል ብለሃል? ለጸሎት ያለህ አመለካከትስ ምንድን ነው? ቶሎ ፈጥኖ እንደሚያልፍ ደስታ ያለበት መዝናኛ ሆኖ ይሰማህ ይሆን? ወይስ ለሰው ነፍስ የልብ ሸክም ተሰምቶህ እየማለድህ ትጸልያለህ?

ያለመርካትና እረፍትን ያለመፈለግ ርሃብ እየተሰማህ፣ መልስህ እስኪመጣ ድረስ ተግተህ የምትጸልየው ምን ያህል ጊዜ ነው? ያለመዘግየት እየተጋደልክ፣ የጊዜውና የሰዓቱ መንጐድ ሳይታወቅህ በጸሎት ውስጥ ሰጥመህ የምትጠፋው፣ ከገሀነም ሃይላት ድልን የምትቀማው ምን ያህል ጊዜ ነው?

የፀሎት ሸክምን ተሸክመህ ሳለህ፣ ያልጠበቅከውና የሚያቃጥል የእንባ ጅረት ፊትህን እያቃጠለ የሚወርደው ምን ያህል ጊዜ ነው? አዎ ያን ጊዜ ነው ወደ ገነቱ ገብተህ፣ ከክርስቶስ ጋር የደም ላቡን የምትጋራው። የጠፉትን ነፍሣት ወደ ይቅርታ የምትመራው፤ ወደ እግዚአብሔርም ልብ ደስታን የምታመጣው ያን ጊዜ ነው።

የእግዚአብሔር ቅዱሳን ሆይ፤ መጸለያችሁን፣ መለመናችሁን ቀጥሉ፤ ፀልዩ፣ አልቅሱ፣ እመኑ



እናም ጽኑ። ለፍርሃት እጅ አትስጡ፣ በመማለድ ትጉ፤ ለረዥሙም ጊዜ የጠበቃችሁት መልስ በመጨረሻው የእግዚአብሔር ሃይል ሰዓት ይገለጣል። ነፍሳት ይድናሉ፣ ሰይጣን ሙሉ ለሙሉ ይሸነፋል።

ዊስሌይ ዱዌል

# 8
# በውስጣዊ ደስታህ ህይወትህን መዝን

ከመንፈስ ፍሬዎች ሁስተኛው ደስታ ነው (ገላ 5፥22)። ታዲያ ከፍቅርህ በመቀጠል፣ ደስታህ በሕይወትህ የመንፈስ ቅዱስ ሙላት ስመኖሩ እጅግ አስተማማኝና ኃያል ምስክር መሆን ይችላልን? መንፈስ ቅዱስ በህይወትህ ቅድሚያ እንዲኖራቸው የሚፈልገው ሁለት ነገሮች ፍቅር እና ደስታ ናቸው። ከፍቅር ቀጥሎ በየዕለቱ ህይወትህ ውስጥ ደስታ ሃይለኛ የሆነው መንፈሳዊ ጉልበትህ መሆን ችሏልን? ፍቅር በፀሎትህ ላይ መንፈሳዊ ሃይል ይጨምራል። ደስታም እንዲሁ ጸሎትህን በሃይል ይሰውጠዋልን?

የአዲስ ኪዳን ክርስትና ህይወትን የሚለውጥ ደስታ ነው። የተቀደሰ ሰው የሚደሰት (ሀሴት የሚያደርግ) ሰው ነው። መንግስተ ሰማይ በቅድስናና በክብር የተሞላች እንደሆነች ሁሉ በደስታም የተሞላች ናት። በመንግስተ ሰማይ እጅግ ደስተኛው ሰው ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ከሌሎች ይልቅ የሚለየው በደስታ ዘይት እግዚአብሔር የቀባው በመሆኑ ነው (መዝ 45፥7)።

እርካታ በአጭር ጊዜ ውስጥ የሚያበቃና በነገሮች ላይ የተመሠረተ ነው። ይሁን እንጂ ደስታ ዘላቂ ሊሆን ይችላል። ደስታ የክርስቲያናዊ ባህርይ አንድ ክፍል ነው። የማጉረምረም፣ የመነጫነጭና አሉታዊ የሆነ አዝማሚያ የማሣየት ልማድህ ስለ መንፈሳዊ ህይወትህ ደረጃ የሚናገረው ነገር አለ። መንፈስ ቅዱስ በህይወትህ የሠራውን ሥራ! ከሁኔታዎች በላይ ሆኖ ወደ ሕይወትህ ዘልቆ በገባው ደስታ መዝነው።



እግዚአብሔር አብ ኢየሱስን ወደ ምድር በላከው ጊዜ ስተለያዩ የአገልግሎቶች መንፈስ ቅዱስ ቀብቶት ነበር። ይህ ቅባት ኢየሱስ ለድሆች መልካም የምስራችን እንዲነግር፣ ለታሠሩት መፈታትን እንዲሰጥ፣ በጨለማ ያሉትን ወደ ብርሃን እንዲገልጥ ብቻ አልነበረም። በተጨማሪ ደግሞ "በአመድ ፈንታ አክሊልን . . . የደስታን ዘይት . . . የምስጋናን መጎናፀፊያ" (ኢሳ 61፥3) ሊሰጥ ተቀብቷል። ኢየሱስ ክርስቶስ እኛን በደስታ ይቀባን ዘንድ የመጣው፣ እርሱ ራሱ በደስታ ዘይት ቅባት አብዝቶ በመባረኩ ነው። በመንፈስ የተሞሉ ክርስቲያኖች ከእግዚአብሔር ባገኙት የደስታ ቅባት ተለይተው ሊታወቁ ይገባቸዋል። ሕይወትህን! በመንፈስ ቅዱስ ደስታ መዝነው። መንፈስ ቅዱስ ያተመው ደስታ ያስማቋረጥ በአንተ ላይ ይታያልን?

ከመንፈሳዊነት ጋር እጅግም ግንኙነት የሌላቸው ብዙ የእርካታና ጊዜያዊ የሀሴት አይነቶች አሉ። እውነተኛ የሆነ መንፈሳዊነት ቅዱስ ከሆነ ደስታ ጋር የተያያዘ ነው። ይህም የጌታ ደስታ ነው። እውነተኛ መንፈሳዊነት በጌታ ደስታ ጠንካራ ይሆናል (ነህ 8፥10)። የጌታ ደስታ በሌሎች ዘንድ ብርሃንህ ይበራ ዘንድ የሚያግዝ ቀልጣፋ መንገድ (ማቴ 5፥16)። በአንተ ያለው የጌታ ደስታ የእግዚአብሔር ህዝብ አንድነት እንዲጠናከር ያግዛል። በደስታ የተሞላና ደስታ የሚያንፀባርቅበት አንድ ክርስቲያን ወደ ክርስቲያኖች ህብረት በገባ ጊዜ ልክ የመንግስተ ሰማይ ንፋስ የነፈስ ያህል ነው።

በህይወትህ ያለውን የጌታ ደስታ መዝነው። በፊትህ ላይ ሁል ጊዜም ፈገግታ ይታያልን? ስምታገኛቸው ሰዎች ሁሉ የሚያጽናና ቃል መናገር የተለመደ መንፈሳዊ ተግባርህ ነውን?

አብዛኛውን ጊዜ የሁኔታዎችን በጐ ጎን በመመልከት ነው የምትታወቀው? አስቸጋሪ ሁኔታዎች በገጠሙህ ጊዜ ጠንካራ የእምነት መንፈስ ያለህ ሰው መሆንህ የታወቀ ነውን? ሁልጊዜ እንደሚዘምር ክርስቲያን ትታወቃለህን? ሌሎች መጽናናት በሚያስፈልጋቸው ጊዜ መዘመር ባትችል እንኳን የዝማሬ ቡድኖች ከሚዘምሩት ወይም ከምስጋና ቅኔዎች እየጠቀስክ በማጽናናትህ ትታወቃለህን?

በመንፈስ የተሞላ ሰው እውነታዊ የሆነ የሕይወት መርህን የሚከተል ነው:: መንፈሳዊ ጦርነትን ማድረግ ልማዱ ቢሆንም፣ ይህ ተግባሩ ግን መንፈሳዊ የሆነ ደስታውን እጥቦ የሚወስድበት አይደለም:: በመንፈስ ቅዱስ የተሞላ ሰው የሌሎችን ሸክም መሸከም ያስደስተዋል:: እንዲህ ሲያደርግ ግን የተስፋውን ቃላት በማካፈል፣ ጥቅሶችን በመጥቀስ፣ የእግዚአብሔርን ታማኝነት በመመስከር ፍርሃትና ጨለማ የከበበውን ሁኔታ ወደ እምነትና ወደ ተስፋ እየለወጠ ነው::

የክርስትና ህይወት ስሜታዊነት አይደለም:: የተቀበልነው ድነት ግን ጥልቅ የሆነ የእርካታ ስሜት ያመጣል:: ምህረትን፣ ሰላምን፣ መረጋጋትን፣ በሀጢያትና በፈተና ላይ ድልን እንዲሁም ከእግዚአብሔር ጋር ህብረት ማድረግን ተሰማምዶ ጥልቅ ደስታን ሳይሰማመድ የሚቀር ማንም አይኖርም:: አንድ ሰው፤ ሰይስሙላና በመጠኑ የሆነ ወይም ጥልቀት ባለው እውነታ ላይ የተመሠረተ ክርስቲያናዊ ሕይወት እንዳለው ሊታወቅ የሚችለው የእነዚህን ቃሎች ተግባራዊነትና የሚያመጡትን እርካታ በግልጽ በተረዳበት መጠን ነው:: እጅግ በርካታ የስም ክርስቲያኖች እውነተኛ የሆነ መንፈሳዊ ደስታ ምን እንደሆነ አያውቁም::



እግዚአብሔር የፈጠረን በቀልዶች ደስ እንድንሰኝ አድርጐ ነው:: መልካም የሆነ ቀልድ አብዛኛውን ጊዜ ትችት፣ ነጭናጫነት፣ ጨለምተኛነትና ተቃውሞ የሞላበትን ሁኔታ መልካምና ህይወት ወዳለው ሁኔታ ሊለውጥ ይችላል:: ይሁን እንጂ ወሰኑን ያለፈ ቀልድ ግን ዋዛ ፈዛዛ፣ ርካሽና ባዶ ነው:: ቀልድ ሲበዛ ባዶነት ይባባሳል:: ዛሬ ዛሬ የምንሰማቸው በርካታ ቀልዶች ጥሩ ጣእም የሌላቸውና ያልተቀደሱ ናቸው::

ሰዎችን እንደሚያዝናና አጫዋችና አንድም ቀን ቁም ነገር እንደማይናገር ኮሚክ ሰው ተደርገህ በሌሎች ዘንድ እንዳትታወቅ ተጠንቀቅ:: ወቅታቸውን ባልጠበቁና ያላግባብ በሚነገሩ ቀልዶች ሳቢያ፤ የእግዚአብሔርን ህልውና ከሕይወትህ አታርቅ:: አንድ ጊዜ እንዲህ ሆነ፤ በሰንደን የሚኖር አንድ የሥነ አእምሮ ሀኪም እጅግ በተደበተ አንድ ሰው ተጎበኘ:: የሥነ አእምሮ ሃኪሙ ሰውየውን እንዲህ ብሎ መከረው፤ "አንዳንድ ቦታዎች እየሄድክ የተለያዩ የቀልድ ዝግጅቶችን ብትካፈል ጥሩ ነው፤ ያንንም ያንንም መስማት . . . ለምሳሌ እገሌ ጋር ብትሄድ በማለት የአንድን ኮሜዲያን ስም ጠቅሶ ነገረው . . .":: ሰውየው የሃኪሙን ንግግር ሳያስጨርስ፤ "ያ ኮሜዲያን እኔ ነኝ" ሲል ጮኸ:: ክርስቲያናዊ ደስታ ግን እንዲህ ዓይነት ቀልድ አይደለም::

በንፁህና በምታምር ቤተክርስቲያን፣ የሚያነቃቃ የሙዚቃ ድምፅ ታዋቂና ተወዳጅ ቅኔና የህብረት ዝማሬ ባለበት አምልኮ ውስጥ ውበት ያለው ደስታ አለ:: ይህ ምናልባት መልካም የሆነ ደስታ ነው:: ነገር ግን መንፈሳዊ ደስታ ከዚያ በላይ ጥልቀት ያለው ነው:: በዝማሬ፣ በጸሎትና አንድ አይነት እምነት ባላቸው ክርስቲያኖች መካከል የሚፈጠር ህብረት ማህበራዊ ደስታን

ያመጣል:: መጽሐፍ ቅዱስ ሲነበብ መስማት ወይም በተወደዱ ዘመዶቻችን፣ መጋቢዎቻችን ወይም የማጽናናት ፀጋ ባላቸው ክርስቲያኖች የሚፀለየውን ጸሎት መስማት ታላቅ የስሜት መነቃቃትን ሊያስከትል ይችላል:: ይሁን እንጂ ምናልባትም ይህ እውነተኛ መንፈሳዊ ደስታ ሳይኖርም ሊከናወን ይችላል::

በፈተና፣ በችግርና በሀዘን ጊዜ የሚያጽናኑትን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ማንበብ ወይም መስማት፣ መተማመንን፣ መረጋጋትን ስሜታዊ እርካታንና ደስታን ያመጣል:: ይህ ማለት ግን የግድ የጌታ ደስታ ነው ማለት አይደለም:: ነፃ የሆነ ህብረትና አምልኮ ባላቸው አንዳንድ ቡድኖች ውስጥ እጅግ ብዙ የሆኑ የጉባኤው ተሳታፊዎች "አሜን" እና "ጌታ ይመስገን" ሲሉ ይደመጣል:: አብዛኛውን ጊዜ ግን ይህ እውነተኛ የሆነ መነቃቃት የሚሆነው በጥቂቱ ነው:: ከላይ የጠቀስናቸው የደስታ አይነቶች በሙሉ መንፈሳዊ ከሆነው ደስታ ጋር አይጠረሱም:: ምናልባትም መንፈሳዊ የሆነውን ደስታ ይገልጡም ይሆናል:: ነገር ግን ደስታ የሚሰውን ቃል ለመተካት በቂ አይደሱም::

1. ከእግዚአብሔር ጋር ያለህን ህብረት በጌታ ባለህ ደስታ መዝነው:: በግል ፀሎትህ በሚኖርህ ደስታ መዝነው:: በእውነት ጌታን የምትወድ ከሆነ፣ ከእርሱ ጋር ብቻህን መሆን ትልቁ ደስታህ ይሆናል:: የግል የፀሎት ሰዓትህ እጅግ የከበረ ከመሆኑ የተነሣ ሳታውቀው ግማሽም ሆነ አንድ ሰዓት ያህል እዚያው ልታሳልፍ ትችላለህ:: ያን ያህል ሰዓት በጸሎት ማሣለፍ አስቸጋሪ የሚሆንባቸው ክርስቲያኖች፣ ስለ እውነተኛ መንፈሳዊ ህብረትና በክርስቶስ ስላለው ደስታ የሚያውቁት በጥቂቱ ብቻ መሆኑን የሚያስረዳ ነው:: ያለምንም ጥርጥር ሌሎች ሰዎች የክርስትና



ሕይወት ልምምድህን በመንፈሳዊ ደስታህ እንደሚመዝኑ ጥርጥር የለውም:: ይህ ደስታ በሕይወትህ፣ በንግግርህና በገጽታህ እየተገለጸ ነው? ስማያዊው ደስታ በምድር የሚገኙትን መንፈሳዊ ሰዎች ገጽታና ሕይወት ውበት ይሰጣል::

2. መንፈሳዊ ህብረትህን ለጌታ በመዘመርህ መዝነው:: እያንዳንዱ ክርስቲያን ስለ ጌታ መዝሙር ጥሩ መሆኑን ያስባል:: አንተስ ለጌታ በመዘመር ደስ ትሰኛለህ? ሌሎች ሰዎች ብዙውን ጊዜ የሁለት የተለያዩ ሰዎችን ባልንጀርነት (ህብረት) የሚመዝኑት ባንድ ላይ ሆነው በሚያዩአቸው ጊዜ ምን ያህል ደስተኞች በመሆናቸው ነው::

ሁሉም ሰው ሶሎ ዘማሪ ሊሆን ወይም አንድ አዝማች እንኳን መዘመር ላይሆንለት ይችላል:: ነገር ግን ሁሉም ሰው ለጌታ መዘመር ይችላል:: ሙስሊም የሆነ አንድ የኮሌጅ ተማሪን ወደ ጌታ በማምጣቴ እደሰት ነበር:: መዝሙረ ዳዊትን አንብቦ አያውቅም:: እኔ የሰጠሁትን አዲስ ኪዳን ገና ማንበብ መጀመሩ ነበር:: ነገር ግን ከተሰወጠ በኋላ በይፋ ባደረገው የመጀመሪያው ፀሎቱ፣ "ኦ ጌታ ሆይ፣ በልቤ ዝማሬን ጨመርክ" ሲል ጸለየ:: አዝማች መዘመር እንኳን እንደማይችል በኋላ ማወቅ ችያለሁ:: ቢሆንም ድምጹ ባያምርም እንኳ ለጌታ መዘመር ችሏል:: ጌታም ይህን በመስማቱ ሀሴት እንደሚያደርግ እርግጠኛ ነኝ::

የአንዳንድ ሀይማኖት ተከታዮች የአምላካቸውን ስም በጩኸት ወይም በድግምት ይጠራሉ፣ እኛ ግን ኢየሱስ ክርስቶስን በዝማሬ ከፍ ከፍ እናደርገዋለን:: ለሌሎች ሀይማኖቶች ዝማሬ በአደባባይ ከሚደረጉ የአምልኮ ክፍሎች ዝማሬ እንደ አንዱ ተደርጎ አይቆጠርም:: በክርስትና ውስጥ ግን የተለመደ የአምልኮ ክፍል ነው:: በመሠረቱ መንፈሳዊ የሆነ ሀሴት በዝማሬ ነው የሚገለጸው::

3. መንፈሳዊ የሆነ ሃይልህን በደስታህ መዝነው:: የጌታ ደስታ መንፈሳዊ ጥንካሬን የሚያሣይና የዚህ ጥንካሬም መመዘኛ ነው፡ (ነህ 8፥10):: መንፈሳዊ ሃይል ማለት የእምነት ሃይል ሲሆን፣ እምነት ባለበት ቦታ ደስታም አብሮ ይኖራል:: ጥርጥርና ተስፋ መቁረጥ ግን ውድቀቶችና የድክመት መመዘኛዎች ናቸው:: መንፈሳዊ የሆነ ሀይል የመንፈስ ቅዱስ ሀይል ነው፤ እርሱም የደስታ መንፈስ ነው::

የእግዚአብሔር መንግስት በመንፈስ ቅዱስ በሆነ ደስታ እንጂ በምግብና በመጠጥ አትመዘንም ወይም ደግሞ መንፈሳዊ በሆኑ ተግባራት አፈጻፀም አትለካም (ሮሜ 14፥17):: ደስታ በሁኔታዎች ላይ የተመሠረተ ነው:: ውስጣዊ የሆነ ሀሴት ግን በማንኛውም ሁኔታ ውስጥ በእግዚአብሔር የበረታ ሕይወት መገለጫ ነው:: ኢየሱስ ይህን እርካታ ይሰጠናል (ዮሐ 17፥13)፤ በዚህም ደስታ የእርሱን በእኛ በሙላት መኖር፣ በውስጣችን ያኖረውን ሃይሉንና፣ በእኛ ዘንድ ያለውን የመንግስቱን ጥንካሬ ልንለካ እንችላለን::

4. በመንፈስ መሞላትህን በደስታህ መዝን፦ በመንፈስ ቅዱስ መሞላት ማለት በደስታ መሞላት ማለትም ጭምር ነው:: መንፈሳዊ ደስታ ማለት በመንፈስ ቅዱስ የሆነ ደስታ (ሮሜ 14፥17) ማለት ነው:: በመንፈስ በምትሞላበት ጊዜ ሀሴት ታደርጋለህ፤ ልብህም ለክርስቶስ ይዘምራል (ኤፌ 5፥18):: መጽሐፍ ቅዱስን ሳይጨምር ከየትኛዎቹም መጽሐፍት ይልቅ ሰዎችን ድል ነሺ ወደሆነ በመንፈስ የተሞላ ሕይወት የመራ ተብሎ የተነገረለት በሀና ዊቴል ስሚዝ የተጻፈው የክርስቲያኖች ደስተኛ ሕይወት ምስጢር የተባለው መጽሀፍ ነው:: በመንፈስ መሞላት ማለት በደስታ መሞላት ማለት ነው:: በመንፈስ ቅዱስ መሞላትህን ሀሴት በማድረግህ መዝነው::

ሀሴት የሌሎች ሰዎች አይኖች ማየት በማይችሉበት ሁኔታ ልብህ ውስጥ ጠልቆ ሊቀመጥ ይችላል:: ነገር ግን ሀሴት ሙሉ በሙሉ ተደብቆ አይኖርምና አፈትልኮ መውጣቱ አይቀርም:: ሰዎችም ሆኑ የሰማይ መላእክት ይመለከቱታል::

ሀሴት ማድረግህ በምትናገራቸው ቃላትና በንግግርህ ቅላጼ ይታወቃል:: ሀሴት ማድረግህ ሌሎችን ለመባረክ በምታከናውናቸው ጥቃቅን የፍቅር ተግባራት ውስጥ ደስ በመሰኘትህ ይገለጣል:: ሀሴት በዓላማህ ፀንተህ በመቆምህ ውስጥም ይገለጣል:: ነፍስህ ደስ በተሰኘ ች ጊዜ ፊትህ ደግሞ ደጋግሞ ደህንኑ ይመሰክራል::

በመንፈስ ቅዱስ የተሞሉ በርካታ ክርስቲያኖችን ሌሎች እንዲህ ሲሉ ይጠይቋቸዋል፤ "ለምንድን ነው ዘወትር እንዲህ ደስተኛ የምትሆነው? ሁልጊዜ ስመለከትህ እንደ ሌሎች ተደብረህና ልብህ እዝኖ አይቼህ አላውቅም? ያንተ ምስጢር ምንድን ነው?" እንዲህ አይነቱ ሁኔታ በክርስቶስ ያገኘኸውን ደስታ ለመመስከር እንዴት ያለ መልካም አጋጣሚ ነው! ህይወትህን በመንፈሳዊ ደስታህ መዝነው::

በተመለሰ ፀሎት ውስጥ ደስታ አለ፤ ከወንድሞችና ከክርስቲያን ወገኖች ጋር በሚኖር ህይወት ውስጥም ደስታ ይገኛል፤ በአምልኮ ውስጥ ደስታን መከፋፈል ይቻላል፤ በአገልግሎት ውስጥም ደስታ አለ:: ከሁሉም በላጭ የሚሆነው ደስታ ግን በክርስቶስ ደስ መሰኘት ነው:: ህይወትህን በክርስቶስ ደስ በተሰኘ ህበት ደስታ መዝን::

ብዙ ክርስቲያኖች እንደሚመሰክሩት፣ የመንፈሳዊ ሕይወታቸው ምስጢር በየቀኑ ሦስት ጊዜ ያህል በደስታ ተሞልተው ብቻቸውን ከእግዚአብሔር ጋር መቆየታቸው ነው። ወደ ውጭ ወጥተው ከህዝብ ጋር ከመቀላቀላቸው በፊት ደህን ማድረግ ይሞክራሉ። እናም ይህን በጥሞና ጊዜያቸው ያገኙትን ባርኮት የዕለት ተግባራቸውን ወደሚያከናውኑበት ቦታ ሁሉ ተሸክመው ሲወጡ ይችላሉ። በልጃቸው የኮምፒዮተር መሰዋወጫ ሱቅ ውስጥ ገንዘብ ተቀባይ ሆነው የሚሰሩ አንዲት ወይዘሮ አውቃለሁ። እርሳቸውም እንደሚመሰከሩት በስራ ገበታቸው ላይ ከህዝብ ጋር ከመገናኘታቸው በፊት በየዕለቱ የእግዚአብሔር ህልውናና ደስታ እስኪሰማቸው ድረስ ይፀልያሉ፤ ከዚያ በኋላ ነው የቀኑን ሥራቸውን የሚጀምሩት። መንፈሳዊ ሁኔታህን ዛሬ በጌታ ኢየሱስ በተደሰትከው ደስታ መዝነው። የእግዚአብሔርን "ፍስጋ የሌለውና የከበረ ደስታ" ልታውቅ ትችላለህ (1ጴጥ 1፥8)። ሕይወትህን በደስታህ መጠን ለካው።

ጆርጅ ሙለር የተባለው ሰው ከእግዚአብሔር የተማረው አንድ ነገር አለ፤ ይኸውም በቀኑ ውስጥ የመጀመሪያ ቅድሚያ የሚሰጠው መንፈሳዊ እንቅስቃሴ እስከ ክርስቶስ ሙሉ ደስታ ድረስ በመንፈስ መባረክ ነው። "የመጀመሪያውና ትልቁ ቅድሚያ የምሰጠው ዕለታዊ ተግባር፣ ነፍሴን በጌታ ደስ ማሰኘት ነው" ሲል መስክሯል። በደስታ የሚሰቀሰቅ ልብ፤ ባልዳኑት ሰዎች መካከል ይህም በክርስቶስ ስተቀበልከው ፀጋ ምስክር እንድትሆንና ከማናቸውም ክርስቲያናዊ የህይወትህ እንቅስቃሴዎችህ ይልቅ ዘላቂ ተጽእኖ ማምጣት የሚችል መስህብ ያለው ሰው ያደርግሃል። የራስህን የህይወት ምስክርነት በደስተኛነትህ መዝነው።



## የክርስቲያን ደስታ

ኦ! የተሰጠን ደስታ እንዴት ድንቅ ነው! ኢየሱስ ክርስቶስ የመንግስተ ሰማይን ደስታ አድሎናል! እውነተኛ የሆነውን ደስታ ሰጥቶናል፤ ያዳነን እርሱ የዕለት ዕለት ባርኮታችን ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ የሰጠንን ደስታ በምድር ላይ ከቶ ምንም ሊያጠፋው አይችልም።

ክርስቲያኖች ያገኘነውን ደስታ የሚወዳደር ምንም የለም! መንፈስ ቅዱስ በውስጣችን ሲሞላ ሰማያዊው ደስታ በውስጣችን ይቀጣጠላል። አስደናቂ በሆነ የፀጋ ተዓምራት፣ ምድር ራሷ እንደ ገነት ትሆናለች።

ደስታ፤ ጥንካሬን፣ ተስፋንና ሰላምን ያመጣል፤ ከፍርሃትና ከጥርጥር እስራት ይፈታል። ደስታ በህይወት መከራ ውስጥ መጽናናትን ያመጣል፤ ለህይወት መልካም መአዛን ይሰጣል። ደስታ፣ ደስተኛ ለሆነው ገጽታህ ሰማያዊ ጸጋን ያጎናጽፋል።

ኦ! ለክርስቲያኖች የተሰጠ ደስታ! ከእግዚአብሔር የተቸረ የመንግስተ ሰማይ ቅምሻ ነው! ይህ የማይነገር ፍስሃ፣ አንደበት መግለጽ ከሚችለው በላይ የላቀ ነው! ጌታችንን እንዲህ ስናውቀው፤ የምድር ኑሮ፣ የመንግስተ ሰማይ ኑሮ፣ ሕይወትም በባርኮት የተሞላች ትሆናለች።

ዊስሌይ ዱዌል